ነው። ያ በትክክል ከተጣለ ሙሉው ሕንጻ ትክክል ይሆናል። ሁለተኛ የማእዘን ራስ የሕንፃው ራስ ነበር፤ ምሶሶዎችንም በቦታቸው አጣምሮ ይይዛል። ሦስተኛ ቊልፍ የሆነው ድንጋይ በቅስቱ መካከል ላይ የሚቀመጥ የመጨረሻ ድንጋይ ነበር። ድንጋዩ በቦታው እንደ ተቀመጠ መረባርቦቹ ሁሉ ይወገዳሉ። እንግዲህ የማእዘን ድንጋይ ሐሳብ ከቊጥር 44 መጀመሪያ ክፍል ጋር በደንብ ይገጣጠማል፤ በዚህ ድንጋይ ላይ መውደቅ ህልውናህን ይወስነዋል። የማእዘን ራስ ወይም ቊልፍ የሆነው ድንጋይ ከቊጥር 44 ሁለተኛ ክፍል ጋር በደንብ ይገጣጠማል። ይህ ድንጋይ ቢወድቅብህ ያደቅሃል። ኢየሱስ መንታ እሳቤ ያለውን ዘይቤ ኢየሱስ በዚህ ሳያቅድ አልቀረም።

ይህ ዘይቤ የመጣው ከመዝሙር 118፥22 ሲሆን፣ ከመነሻው የሚያመለክተው የአይሁድን ሕዝብ ነበር። ሌሎች ሕዝቦች ቢያሰቃዩዋቸውም እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ውድ ሕዝቦች ነበሩ። እዚህ ላይ ኢየሱስ የሕዝቡ ተወካይ ወይም መላ ሕዝቡን በአካልነት የምወክል ነኝ ይላል።[27] በሕዝብነት በእስራኤል ላይ የደረሰው ሁሉ በግለሰብነቱና በመሲሕነቱ በኢየሱስ ላይም ደርሶአል። የመዝሙረ ዳዊት ክፍል መሲሓዊ ነው ማለታችን በእርግጥ ትክክል ነው። የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያንም ይህንኑ ማድረጓ እርግጥ ነው (ሐሥ 1፥11፤ ሮሜ 9፥33፤ 1ጴጥ 2፥7)። መዝሙር 118፥22ን በከበቡ ቊጥሮች «የድነት ንግግር»ን እናነባለን (ከ21:25 ጋር ያነ)። ቊጥር 26 ውስጥ «በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው»[28] በሚለው ቃል ወደ ኢየሱስ በድል መግባት ፊታችንን እናዞራለን።


[27] F.F. Bruce, "New Wine in Old Wine Skins: III. The Corner Stone," *ExPT* 84 (1972-73): 231-235.

[28] Blomberg (p. 325) እንደሚያሳስበው እስከ ሕፃንነት ትረካ ድረስ ማቴዎስ አያሌ ጥቅሶችን አንድ ምዕራፍ ውስጥ አላቀረበም (ምዕ 1-2)፤ በቀረው የወንጌሉ ክፍል ግን ከዳር እስከ ዳር ተሠራጭተው ይገኛሉ።



መዝሙር 118፥22 ውስጥ ስለ አለው ቃል አንድ የመጨረሻ ማስታወሻ ይህን ተከትለው 23-24 ውስጥ የመጡት ቃሎች ቀጥሎ ያሉት ያቸው፤ *«እግዚአብሔር ይህን አደረገ፤ ለዐይችንም ድንቅ ናት። እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት፤ በእርሷ ሐሤት እናድርግ፤ ደስም ይበለን።»* የኢየሱስ ሞት የእግዚአብሔርን ድርጊት ዘግናኝ ኢፍትሓዊነት ቢያስመስለውም እንኳ፣ የድነታችንም ምንጭ ነው። አስከፊ ቢሆንም እንንከባከበዋለን። እርግጥ ውበቱ በደም የተሸፈነ ነው።

**ማቴ 21፥43-46**
**ከማር 12፥12 ጋር**



[43]«ስለዚህ እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ከእናንተ ተወስዳ ፍሬዋን ለሚያፈራ ሕዝብ ትሰጣለች፤ [44]በዚህ ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ይሰባበራል፤ ድንጋዩ የሚወድቅበት ሰው ግን ይደቀቃል።»[ii]

[45]የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ምሳሌዎቹን በሰሙ ጊዜ፣ ስለ እነርሱ የሚናገር መሆኑን ዐወቁ። [46]ነገር ግን ይዘው ሊያስሩት ቢፈልጉም ሕዝቡ ኢየሱስን እንደ ነቢይ አድርጎ ይመለከት ስለ ነበር ፈሩ። (ነገር ግን ... ትተውት ሄዱ።[ማር])

*[ii]44 አንዳንድ ቅጆች ቁር 44 የላቸውም።*

የእግዚአብሔር የዕርሻ ቦታ ከእነዚህ ክፉ ዐራሾች ተወስዶ ለእግዚአብሔር ተገቢውን ክብር ለሚሰጡ ሰዎች ይሰጣል። ሲጀመር እነዚህ ዐራሾች ቀራጮችና አመንዝራዎች ሆነው እናገኛቸዋለን። ውሎ አድሮ ግን አሕዛብን ሳይቀር ያካትታሉ።[29] ኢየሱስን ለሚቀበሉት

[29] A.A. Milavec, "Mark's Parable of the Wicked Husbandmen as Reaffirming God's Predilection for Israel," *JES* 26/2 (1989): 289-312 በሚለው ላይ እንዲህ ይላል፤ በማር 12፥1-12 እና በኢሳ 5፥1-7 ክፍል መሠረት ይህ ምሳሌ የሚያመለክተው ስለ ኢየሱስና ስለ ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በቀጣይነት እስራኤልን ስለ መወደዱ ነው። የእርሱ ትንታኔ ፊር የያዘ ባይሆም እንኳ፣ ይህን ምሳሌ መሠረት በማድረግ ጸረ አይሁዳዊ (ጸረ ሴማያዊ) አቋም እንዳይኖር ሚላቬክ ያስጠነቅቃል። የማቴ 21፥43 ቀዳሚ ሐሳብ የአሕዛብ መጨመር ሳይሆን፣ እምነት በኢየሱስ ነው።


ታላላቅ በረከቶች ተቀምጦላቸዋል፤ ለማይቀበሉት ደግሞ አስፈሪ ውጤቶች አሉ:: ለማስወገድ በሞከሩት ድንጋይ ትቢያ እስከሚሆኑ ድረስ ይደቃሉ (ከኢሳ 8÷14፤ ከዳን 2÷35:44 ጋር ያነ)::

የዚህ ምሳሌ አንድምታዎች ፈሪሳውያን ሊቋቋሟቸው ከሚቻላቸው በላይ ናቸው:: እጅግ በከፋ ሁኔታ ኢየሱስን ለመያዝ ፈለጉ:: ሕዝቡ ግን የተናገረውን ቃል ሁሉ ተቀብለዋል:: ተሰድበዋል፤ ምንም እንደማይሠሩም ተቈጥረዋል፤ ሁለቱ ነገሮች መጥፎ ቍርኝቶች ናቸው::

## የሰርጉ ድግስ ምሳሌ

ይህ ምሳሌ ሉቃስ 14÷15-24 ውስጥ ከተነገረው ቃል ጋር ብዙ ተመሳሳይነቶች አሉት:: ቃላቱ የተነገሩት ግን በልዩ ልዩ ጊዜ፣ በልዩ ልዩ ዝርዝርና ለልዩ ልዩ ዐላማዎች ነው:: ከአንድ «ምንጭ» ፈልቀው በአሁኑ መልኩ ይወጡ ዘንድ አርትዖት ተደርጎባቸዋል ማለቱ ምክንያታዊ አይመስልም:: እርግጥ ነው ኢየሱስ በተለይ እንደ «ድግሱ» ካለ የታወቀና ብዙ ሐሳብ ሊያመነጭ ከሚችል አንድ ጭብጥ ሁለት ልዩ ምሳሌዎችን ሊፈጥር ይችላል::

ማቴ 22÷1-7



1ኢየሱስም እንደ ገና እንዲህ የሚል ምሳሌ
ነገራቸው፤ 2«መንግሥተ ሰማይ ለልጁ ሰርግ የደገሰ
ንጉሥ ትመስላለች፤ 3ንጉሡም የተጋበዙትን ሰዎች
እንዲጠሩ አገልጋዮቹን ላከ፤ እነርሱ ግን አንመጣም
አሉ::

4«እንደገናም ሌሎች አገልጋዮች ልኮ፣ 'የተጋበዙትን፣ እነሆ፣ በሬዎችንና
የሠቡ ከብቶቼን አርጄ ድግሱን አዘጋጅቻለሁ፤ ሁሉም ነገር ዝግጁ ስለሆነ ወደ ሰርጉ
ኑ በሏቸው' አለ::



5«ተጋባዦቹ ግን ጥሪውን ችላ ብለው፣ አንዱ ወደ እርሻው ሌላው ወደ
ንግዱ ሄዱ፤ 6የቀሩትም አገልጋዮቹን በመያዝ አጕሳቍለው ገደሏቸው:: 7ንጉሡም
በመቈጣት ሠራዊቱን ልኮ ገዳዮቻቸውን አጠፋ፤ ከተማቸውንም አቃጠለ::»

አዲሱ መደበኛ ትርጕም የቍጥር አንድን የመጀመሪያ ቃል አልተረጎመውም ኢየሱስ «መለሰ» [*አፓክሪቴስ - apokritheis*] ይላል:: ይህ አዲስ ውይይትን ከሚያስተዋውቀው ከጽሑፋዊ ቀመር ውጭ ላይሆን ይችላል:: እንደገናም ኢየሱስ ለአይሁድ አለቆች ምኞቶች፣ የፊት ገጽታ፣ ወይም እኛ እናውቅ ዘንድ ላልታደልናቸው ቃሎች መልስ እየሰጠ ሊሆን ይችላል::

የሰርግ ደግስ ለብዙ ቀናት ይቆያል:: ስለዚህ በሚመጣው በዓል ላይ ለመገኘት ዕቅድ ይይዙ ዘንድ ለማሳሰብ በሰርጉ ሰሞን የቅድሚያ መልእክተኞች ተልከው ነበር:: ድግሱ ሊጀመር ቀኑ እንደ ደረሰ የጧቱ ምግብ [አሪስቶን - ariston] ገበታ ላይ ተዘጋጅቶ ስለሚገኝ እንግዶች ወዲያውኑ እንዲመጡ ይነግሩ ዘንድ ንጉሡ፣ መልእክተኞችን በፍጥነት ላከ:: ድግስ በመሲሑና በሕዝብ መካከል ያለውን ኅብረት በተምሳሌትነት ለማሳየት ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ይውላል (ማቴ 8÷11፤ ሉቃ 13÷29፤ ራእ 19÷9):: መሲሑም ብዙ ጊዜ በሙሽራ እንደሚመስል ልብ ማለት ይኖርብናል (ማቴ 9÷15፤ 25÷1፤ ዮሐ 3÷29፤ ኤፌ 5÷25-32፤ ራእ 21÷2:9)::

ይሆናል ተብሎ ባልታሰበ ሁኔታ የተጋበዙት ለመምጣት ፈቃደኞች ሳይሆኑ ቀሩ:: እንደውም እምቢታቸውን በጽኑ ገለጹ (ኢፍጽም የሆነው ግስ እንደሚያመለክተው):: ስለዚህ ንጉሡ የተዘጋጀላቸውን ታላቅ ድግስ በመግለጽ ተጋባዦቹን ያባብሉአቸው ዘንድ ተጨማሪ መልእክተኞችን ላከ:: ነገር ግን መልእክተኞቹን «አባረሯቸው::» አንዳንዶች በማሳቸው ላይ ለመሥራት ሄዱ፤ ሌሎች ደግሞ ለሥራ ስብሰባ ሄዱ:: የቀሩት ደግሞ መልእክተኞችን ችላ ማለት

ብቻ ሳይሆን ደበደቧቸው፤ ገደሏቸውም:: ለዚህ የንጉሡ ቍጣና አፀፋ የታወቀ ነው:: የመጀመሪያው የእንግዶች ዝርዝር በንጉሡ ወታደሮች ተሠረዘ፤ ከተማቸውም ተቃጠለች:: ይህ የብሉይ ኪዳንን ምስያ በመጠቀም ፍርድ እንደሚመጣ የሚያሳይ ሥዕል ነው::

ማቴ 22፥8-14

[8]«ከዚያም አገልጋዮቹን እንዲህ አላቸው፤
የሰርጉ ድግስ ዝግጁ ነው፤ ነገር ግን የተጋበዙት
የሚገባቸው ሆነው አላልተገኙ፣ [9]ወደ መንገድ
መተላለፊያ ወጥታችሁ
ያገኛችሁትን ሁሉ ወደ ሰርጉ ድግስ ጥሩ:: [10]አገልጋዮቹም ወደ መንገድ ወጥተው
ያገኙትን መልካሙንም ክፉውንም ሁሉ ሰብስበው የሰርጉን አዳራሽ በእንግዶች
ሞሉት::
[11]«ንጉሡም የተጋበዙትን እንግዶች ለማየት ሲገባ፣ አንድ የሰርግ ልብስ
ያልለበሰ ሰው አየ፤ [12]እንዲህም አለው፤ 'ወዳጄ ሆይ፤ የሰርግ ልብስ ሳትለብስ
እንዴት እዚህ ልትገባ ቻልህ?' ሰውየው ግን የሚመልሰው ቃል አልነበረውም::
[13]ንጉሡም አገልጋዮቹን፣ 'እጅና እግሩን አስራችሁ
በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጥታችሁ ጣሉት፤ በዚያ
ልቅሶና ጥርስ ማፏጨት ይሆናል' አላቸው፤ [14]የተጠሩት
ብዙዎች፣ የተመረጡት ግን ጥቂቶች ናቸውና::»

ንጉሡ በብቀላ ብቻ አልረካም፣ ገና ሊሞላ የሚገባው የድግስ እ[illegible]ን አለው:: ልጁ ሊያገባ ነው፤ ለንጉሡ የሚመጥን ግብዣ እንዲደገስም ፈለገ:: ስለዚህ ጥሪው ለትልቁና ለትንሹ ሆኖ ግብዣው በመንግሥት ውስጥ ለሚገኙት ዜጎች ሁሉ ተላከ:: መልእክተኞቹም ሰዎች ወደሚገኙባቸው ወደ ማንኛውም መንገድና የመንገድ ጠርዝ ሄዱ [*ታስ ዴክሰደስ ቶን ሆደን - tas diexodous ton hodon*]:: ነገር ግን ከእንግዶቹ አንዱ ለድግሱ የሚሆነውን ልብስ አለበሰም ነበር:: በጥንት



ዘመን ነገሥታት ለእንግዶቻቸው የሰርግ ልብስ ያቀርቡ ነበር:: ከዚህ ላይ የሆነው ይህ ሆነም አልሆነ ሰውየው ወደ ንጉሡ ሲመጣ በደንብ አለመዘጋጀቱና ዝምታው በደሉን እንዲሁም ለግብዣው ክብር አለመስጠቱን ያሳያል::

ንጉሡ፣ «ወዳጄ ሆይ፤» ብሎ ሰውዬውን መጥራቱ እንኳን ተግሣጽ ነበር (ከማቴ 20፥13 ጋር ያነ):: እንዲህ ያለው ሰው ወደ ውጭ የተጣለው ወደ ድግሱ መግባት የማይገባው ስለሆነ አልነረበም፤ የተጋዙት ሁሉ መግባት የሚገባቸው አልነበሩምና:: የተጣለው እንደ መጀመሪያዎቹ ተጋባዦች ተገቢ በሆነ መንገድ ለመግባት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ነው::

ቍጥር ዐሥራ አራት ስለ እግዚአብሔር ሉዐላዊነት ብዙ እንድንረዳ ያግዙናል:: ብዙዎች[30] ተጠርተዋል፤ የተመረጡት ግን ጥቂት ናቸው ይላል:: እንዴት ተጠሩ? በምሳሌው ላይ የሚገኙት መልእክተኞች ተቀባይነት ያላገኙትንና የተገደሉትን ነቢያት ይወክላሉ:: ስብከታቸው ጥሪው ነበር:: እንዴት ነበር የተመረጡት? ለእግዚአብሔር ጥሪ (ይኸውም ስብከት) ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኞች በመሆናቸው ነው:: በዚህ ጽሑፍ መሠረት የእግዚአብሔር ጥሪ የማይጋፉት አይደለም:: የእግዚአብሔር ምርጫ የእኛንና የእርሱን አጸፋ ያካትታል::

**§ 133**
**ጥያቄ ቍጥር 1**
**ለቄሣር ግብር ስለ መክፈል በሄሮድሳውያን (በሄሮድስ ወገኖች) የቀረበ**
**(ማቴ 22፥15-22፤ ማር 12፥13-17፤ ሉቃ 20፥20-26)**

ቀጥሎ ባሉት ምንባቦች አራት ያህል ጥያቄዎችን እናነባለን:: የመጀመሪያዎቹ ሦስት ጥያቄዎች የቀረቡት በኢየሱስ ተቃዋሚዎች ነው:: እነዚህ ጥያቄዎችም በዘመኑ የነበሩትን ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ሦስት ዐበይት ጐራዎች (ፓርቲዎች) ይወክላሉ፤ እነዚህም

[30] በሴማዊ የቋንቋ አገባብ «ብዙዎች» የሚለው «ሁሉንም» ወይም «እያንዳንዱን ብዙውን» እንዲወክል ማድረጉ የተለመደ ነበር::

ሄሮድሳውያን፣ ሰዱቃውያንና ፈሪሳውያን ናቸው:: ተራ በተራ በዐይነቱ ልዩ በሆነ ጥያቄ ኢየሱስን ለማጥመድ
ሙከራ አደረጉ:: ኢየሱስ ሌላ ጥያቄ መጠየቅ እስከማይደፍሩ ድረስ ጥያቄያቸውን መመለስ ብቻ ሳይሆን፣ በሂደቱ ውስጥ ግብዝነታቸውንና የጥላቻ አነሣሽ ምክንያታቸውን ጨምሮ አጋለጠ:: በመጨረሻም ኢየሱስ ማንም ሊመልሰው ያልቻለውን የራሱን አስቸጋሪ ጥያቄ አቀረበ:: ይህም በርሱና በጠላቶቹ መካከል ያለውን እሰጥ አገባ ደመደመው:: ሊነጋገሩበት የሚገባና የቀረ ነገር አልነበረም:: እንግዲህ ራሳቸውን ለመታደግ የቀራቸው አማራጭ ግድያ ብቻ ነው::

15ከዚህ በኋላ ፈሪሳውያን በመሄድ በአፍ እላፊ
እንዴት እንደሚያጠምዱት ተማከሩ:: (ኢየሱስን
አሳልፈው ለገዢው ኀይልና ሥልጣን ለመስጠት፣[ሉቃ])
16ደቀ መዛሙርታቸውን ከሄሮድስ ወገኖች ጋር ወደ
እርሱ ልከው
(ጻድቃን መስለው የሚቀርቡ ሰላዮችን) እንዲህ አሉት፤ «መምህር ሆይ፤ አንተ እውነተኛና የእግዚአብሔርንም መንገድ በእውነት የምታስተምር እንደ ሆንህ፣ ለማንም ሳታዳላ ሁሉን በእኩልነት እንደምትመለከት እናውቃለን፤
17ንገረን፤ ምን ይመስልሃል? ለመሆኑ ለቄሳር ግብር መክፈል ይገባል ወይስ አይገባም?» (እኛስ እንክፈል ወይስ አንክፈል?»

**ማቴ 22÷15-17**
**ከሉቃ 20÷20፤**
**ከማር 12÷15 ጋር**

ኢየሱስን በልጦ ለመገኘት ሙከራ ያደረጉት በመጀመሪያ የፈሪሳውያንና የሄሮድሳውያን ወገኖች ናቸው:: በዘወትር አኗኗር እነዚህ ሁለት ወገኖች ጠላቶች ነበሩ:: ፈሪሳውያን የቀይ ክንፍን የሃይማኖት ወገን ይወክላሉ:: በሌላ በኩል ግን ሄሮድሳውያን ፓለስቲና ውስጥ ወደ ሰላምና ብልጽግና የሚያመራው መንገድ ከሮም ጋር



መተባበር ነው ብለው ያምኑ ነበር:: ከሄሮድስ ቤተ ሰብ ይልቅ የሠራ ስለሌለ በልዩ ልዩ የመንግሥት ኀላፊነታቸው ውስጥ የሄሮድሶች ደጋፊዎች ናቸው::

ከልባቸው መልስ እንደሚገልጉ ሆነው በመቅረብ በሽንገላ ቃላቸው ኢየሱስን እንዲህ አሉት:- (1) አንተ የእውነት ሰው ነህ፤ ስለዚህ በዚህ ረገድ አርአያነትህን ልንከተል እንችላለን፤ (2) የእግዚአብሔርን ፈቃድ በትክክል ታስተምራለህ፤ ስለዚህ ሐሳብህን እናምናለን፤ (3) በሰዎች አትመራም፤ ስለዚህ የምትሰጠው መልስ ሚዛናዊ ነው ብለን ለማመን እንችላለን::

በእነርሱ የሽንገላ ቃል ማንም አይታለልም፤ «ለቄሣር ግብር እንክፈል ወይስ አንክፈል?» የሚለው ግልጽ ጥያቄያቸው ኢየሱስን ለማጥመድ የታቀደ መሆኑ ግልጽ ነው:: «መክፈል አይገባም» ቢል ሕዝቡ በእርግጥ ደስ ይሰኛሉ:: ግብር መክፈልን ይጠላሉና:: ከዚህ ሌላ ሳንቲሙ ራሱ በላዩ ላይ አስቀያሚ የሆነ ጽሑፍ አለበት:- «የመለኮት አውስጦስ ልጅ ጢባርዮስ ቄሣር» የሚል:: በሌላው ገጹ ደግሞ፣ «ፖንቲፌክስ ማክሲመስ - *pontifex maximus* (እጅግ ከፍተኛ ሊቀ ካህናት») የሚል ይገኝበታል:: ኢየሱስ ቀረጥ እንዳይሰበሰብ ቢያደርግላቸው ሕዝቡ ቢወዱም ሄሮድሳውያን ግን እርሱ የሚያዝበትንና የሚገደልበትን ሁኔታ ያመቻቹ ነበር:: በሌላ በኩል ኢየሱስ፣ «አዎን ለቄሣር ግብር መክፈል አለብን» ቢል ኖሮ፣ በፈሪሳያን የሚደፋፈሩት ሰዎች እርሱን ከመከተል ያፈገፍጉ ነበር:: እንዲያውም የሮምን አገዛዝ ስንሰለት (በተለይ ግብርን) የማያስወገድ መሲሕ ድጋፍ የሚገባው አይደለም:: ኢየሱስ ወጥመድ ውስጥ ገባ!

18ኢየሱስ ግን ተንኰላቸውን በመረዳት እንዲህ
አላቸው፤ «እናንተ ግብዞች ለምን በነገር ልታጠምዱኝ
ትሻላችሁ? 19ለግብር የሚከፈለውን ገንዘብ እስቲ
አሳዩኝ»

**ማቴ 22÷18-22**

እነርሱም አንድ ዲናር አመጡለት:: [20]እርሱም፣ «በዚህ ገንዘብ ላይ የሚታየው መልክ
የማን ነው? ጽሕፈቱስ የማን ነው?» አላቸው::
[21]እነርሱም፣ «የቄሣር ነው» አሉት::
[22]እርሱም መልሶ፣ «እንግዲያውስ የቄሣርን ለቄሣር፣ የእግዚአብሔርንም
ለእግዚአብሔር ስጡ» አላቸው::

[26]ስለዚህ በተናገረው ቃል በሕዝቡ ፊት
ሊያጠምዱት አልቻሉም፤ በመልሱ ተገርመው ዝም አሉ::
(ትተውትም ሄዱ::[ማቴ])

***ሉቃ 20÷26 ከማቴ 22÷22 ጋር***

ኢየሱስ ግን ምን ዐላማ እንዳላቸው ዐውቋልና ወደ ዋናው ጉዳይ አመጣቸው:: በአደባባይ፣ «ግብዞች» ተብለው መዘለፋቸው ትልቅ ጉዳት ነው:: ሆኖም ዋናው ነጥብ ገና ሊመጣ ነው:: ኢየሱስ ሳንቲሙን አመጡልኝ አለ:: ኪሳቸው ውስጥ የሮም ዲናር መገኘቱ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የሮምን አገዛዝ መቀበላቸውን ያሳያል:: ግብር የመጣል ሥልጣኑን ሳይቀበሉ የመንግሥትን ሳንቲም ቀርጾ የማውጣት መብት ለመቀበል አይቻልም::

ኢየሱስ ሳንቲሙን ከፍ አድርጎ ይዞ፣ በሳንቲሙ ላይ ያለው ምስል የማን ነው በማለት ጠየቀ:: መልሱን ለመናገር የተነሣው እንደ መሆናቸው ጥያቄው ወዴት እንደሚያመራ ማስተዋል ነበረባቸው:: ተጠየቁ ግልጽና ጥልቅ ነበር:- ለቄሣር የቄሣርን ስጡ፤ ለእግዚአብሔርም የእግዚአብሔርን ስጡ ይላል:: «ስጡ» የሚለው ቃል በቁሙ ሲታይ «መልሳችሁ ስጡ» ማለት ነው:: ስለዚህ ኢየሱስ የምንከፍለው ግብር ግዴታ መሆኑን አመለከተ:: የመጋቢነታችን አንዱ አካል በመሆን ለእግዚአብሔር ገንዘብ የመክፈል ግዴታ እንዳለብን ሁሉ፣ የምንከፍለው ግብርም ከመንግሥት የተቀበልነው ዕዳ ነው::

ይህ ግዙፍ የሆኑ እንድምታዎች አሉት:: የመጀመሪያው አንድ መንግሥት ግብር የመጣል መብት አለው:: መክፈል የሚገባንን ግብር



ብናጭበረብር፣ እግዚአብሔር ለቀባው ሥልጣን አንገዛም ማለታችን ነው (ሮሜ 13÷1-7፤ 1ጴጥ 2÷13-17):: አንድን መንግሥት የምንታዘዘው የሚሠራውን ስለምንወድ፣ ኀላፊውን ስለምናከብር፣ ወይም የገንዘብ አጠቃቀሙን ስለምንወድ አይደለም:: እርግጥ ነው ለሕዝባዊ ዐመፅ ተገቢ ወቅቶች አሉ (ሐሥ 4÷19፤ 5÷29):: ይሁን እንጂ አመፁ እግዚአብሔር እንድንታዘዝ የጠየቀንን ወይም እንዳንፈጽመው ያዘዘንን እንድንተላለፍ መንግሥት በቀጥታ ወይም በግለሰብ ደረጃ ለሚጠይቀን ወቅት መቆጠብ ይኖርበታል::[31]

ሁለተኛ በሳንቲሙ ላይ ያለው ምስል የቄሣር (ጢባርዮስ) ነው:: እንደሚታወቀው ምስሉ በሳንቲሙ ላይ ካለ ገንዘቡ የእርሱ ነው ማለት ነው:: ነገር ግን ኢየሱስ ያዳምጥ የነበረውን ሰው ቀና ብሎ ሲመለከት ከእግዚአብሔር ምስል ጋር ምስላቸው የተቀረጸ ወንዶችና ሴቶችን አየ:: ሕይወታቸውን ለእርሱ የመስጠት ግዴታ አለባቸው:: አሁን ግን መሲሑ ኢየሱስ እፊታቸው ቆሞአል:: እግዚአብሔር ባቀደው መሠረት እርሱን በመከተል ፈንታ ሊያጠምዱት ጥረት ያደርጋሉ:: በአሁኑ ሰዓት ለእግዚአብሔር የሚገባውን በማስቀረት ላይ ናቸው::

ፈሪሳውያንና ሄሮድሳውያን ዕንቅፋት ሆነዋል:: ይህን «የማይበገር» ጥያቄ ለማቅረብ ብዙ ጥረዋል:: ዕቅዳቸው ግልጽ ነው:: ይሁን እንጂ ከዐሥራ አምስት ሰኮንድ በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ይህ ያልተማረ የገሊላ ሰው፣ ጥያቄያቸውን ከንቱ አደረገባቸው፤ አነሣሽ ምክንያታቸውን አጋለጠባቸው፤ ግብዝነታቸውንም ገለጠው:: ማድረግ የቻሉት ነገር ቢኖር በፍርሃትና በፍርሃት ተሸማቀው ወደ ኋላ ማፈግፈግ ነው:: በመጀመሪያው ምት - ሄሮድሳውያን ከትወና ውጭ ሆኑ፤ ሆኖም ፈሪሳውያን ለሁለተኛው በትር ዳግም ይመለሳሉ::

---

[31] ከA. Stock, "Render to Caesar," *BibT* 62 (1972): 929-934 ጋር ያነጻጽሩ::

**§ 134**
**ጥያቄ ቍጥር 2፣**
**በሰዱቃውያን ጋብቻ**
**በትንሣኤ**
**(ማቴ 22÷23-33፤**
**ማር 12÷18-27፤**
**ሉቃ 20÷27-40**

[ማር 12:18]ከዚህ በኋላ (በዚያኑ ቀን[ማቴ]) የሙታን ትንሣኤ የለም የሚሉ ሰዱቃውያን ወደ እርሱ መጥተው እንዲህ ሲሉ ጠየቁት፤ [19]«መምህር ሆይ፤ የአንድ ሰው ወንድም ሚስት አግብቶ ልጅ ሳይወልድ ቢሞት፣ ይህ ሰው ሴትዮዋን አግብቶ ለወንድሙ ዘር እንዲተካ ሙሴ ጽፎልናል:: ታዲያ (በእኛ ዘንድ[ማቴ]) ሰባት ወንድማማቾች ነበሩ፤ የመጀመሪያው አግብቷት ዘር ሳይተካ ሞተ፤ [21]ሁለተኛውም ሴትዮዋን አገባት፤ እርሱም ዘር ሳይተካ ሞተ፤ ሦስተኛውም እንዲሁ፤ [22]ሰባቱም አገቧት፤ ዘር ግን አልተኩም፤ በመጨረሻም ሴትዮዋ ሞተች:: [23]እንግዲህ ሰባቱም አግብተዋታልና በትንሣኤ ለማናቸው ሚስት ልትሆን ነው?» አሉት::

*[T]23 አንዳንድ ቅጆች በትንሣኤ ሰዎች ከሙታን ሲነሡ የሚል አላቸው::*

«ሁለተኛው ዙር» ከዚህ ላይ ይመጣል:- ሰዱቃውያን:: ይህ ቡድን በ70 ዓ.ም. ቤተ መቅደሱ ሲፈርስ ህልውናቸው አከተመ:: በመሆኑም ስለ እነርሱ በመጠኑ የምናውቀው ነገር የተገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ (በወንጌሎቹ ዐሥራ አራት ጊዜ የተጠቀሱትን ብቻ)፣ ከኢዮሳፍስና ከቀደምት ክርስቲያን ጸሐፊዎች የተገኘውን ነው:: እነዚህ ምንጮች ሁሉ የሰዱቃውያን «ጠላቶች» ስለሆኑ ያገኘነውን መረጃ በጥንቃቄ ማየት አለብን:: ሆኖም ሰዱቃውያን በመላክም ሆነ በመንፈስ አምሳል ማንኛውም ትንሣኤ ስለሚክዱ በግልጽ ሃይማኖታዊ «ሊብራሎች» ነበሩ (ሐሥ 12÷8፤ ከኢየሳፍስ *Ant* 18:1: 3-14 *Wars* 2.8.14 ጋር ያነ):: እንዲሁም አምስቱን የሙሴ መጻሕፍት ከቀረው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ አስበልጠው በአንደኛ ደረጃነት ያስቀምጡታል:: የፈሪሳውያንን ትውፊት ፋይዳንም ይክዳሉ:: በክህነት ውስጥ ወሳኝ



ኀይል የነበሩ ይመስላሉ፤ ከዚህም የተነሣ ቤተ መቅደሱን ለመቈጣጠር ሳይበቁ አልቀሩም::

እነርሱም ለስለስ ብለው፣ በፈላስፋዊ «ተጨባጭነትና» በሽንገላ ወደ ኢየሱስ መጡ:: ጥያቄያቸው በትንሣኤ እውን እንደሚሆን በማሰብ የዋርሳነት ጋብቻን የሚመለከት ነበር:: ሦስቱም ተመሳሳይ ወንጌላት ሰዱቃውያን በትንሣኤ እንደማያምኑ ግልጽ አድርገዋል:: ስለዚህ ዐላማቸው ኢየሱስን አጉል ውጥረት ውስጥ ማጥመድ ወይም ማናቸውንም መልስ ከእርሱ ማግኘት አልነበረም:: ይልቁንም የሌዋውያንን ጋብቻ በተመለከተ፣ (የተበላሸ የጋብቻ ታሪክ ክስተት)፣ (ዘዳ 25÷5 እና ዘፍ 38÷8ን በመጥቀስ)[32] ጉዳዩ ቂልነት ያለበት መሆኑን አሳይተው የትነሣኤን ፅንሰ ሐሳብ ይክድ ዘንድ ለማስገደድ ነበር:: ይህን በማድረግም የሚያሸንፉት ኢየሱስን ብቻ ሳይሆን ፈሪሳውያንንም ነበር:: የዋርሳ ጋብቻ አለ ቢባል እንኳ በኢየሱስ ዘመን የተለመደ ጉዳይ አልነበረም:: እንደ እውነቱ ከሆነ ብሉይ ኪዳን ውስጥ ተመዝግበው የሚገኙት ምሳሌዎች የትዕማርና (ዘፍጥረት 38) የሩት ብቻ ነበሩ (1÷11-13፤ 4÷1-22)::

የሆነው ሆኖ ወንድሞች ሁሉ ለወንድማቸው (ለወንድሞቻቸው) ወራሽ የመተካት ግዴታቸውን ለመወጣት ይህችን ሴት አግብተዋት ከሆነና ቀጥተኛ የአካል ትንሣኤ እውን ከሆነ፣ ለማን ትሆናለች? ይህስ በሰማይ «ቤተ ሰባዊ ጋብቻን» ግድ ይላልን? ይህን ሐሳብ በሁለት

[32] ኤደርሼም የተባለ ጸሐፊ ስለ ትንሣኤ የተሰጠው የአይሁድ መምህራን ግምት የቱን ያህል የሚያስቅ መሆኑን ለማሳየት አንዳንድ ምሳሌዎችን ያቀርባል:: ለምሳሌ፣ አንዳንዶች አንድ ሰው ራቁቱን ቢቀበር እንኳ እንደ ስንዴ ዛላ ልብስ ለብሶ ይነሣል ይላሉ:: ሌሎች ደግሞ የሳሙኤልን ምስል መነሣት መሠረት በማድረግ (1ሳሙ 28÷14) የትንሣኤ አካላችን ሙሉ በሙሉ የአሁኑን አካላችንን ይመስላል ይላሉ:: ሌሎች ወገኖች ደግሞ አይሁድ ሁሉ ከፓሊስትና ዐፈር ይነሣሉ ይላሉ:: ስለዚህ በባዕድ ምድር ለተቀበሩት ሰዎች ሬሳቸው ቅድስት ሀገር ተንከባልሎ እንዲደርስ የሚያስችሉ ቀዳዳዎች አሉ ይላሉ::

ወንድማማቾች ምሳሌነት ለማቅረብ ሲችሉ ሰባት ማድረጋቸው ጉዳዩን ይበልጥ ግልጽና ቂልነት የሞላበት ያደርገዋል::[33]

ማር 12፥24

[24]ኢየሱስም፣ እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ «የምትስቱት እኮ ቅዱሳት መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኀይል ስለማታውቁ ነው!»

ሉቃ 20፥34-36

[34]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ «የዚህ ዓለም ልጆች ያገባሉ፤ ይጋባሉም፤ [35]የሚመጣውን ዓለም የሙታን ትንሣኤ ማግኘት የሚገባቸው ግን አያገቡም፤ አይጋቡም:: [36]እንደ መላእክትም ስለሆኑ ከዚያ በኋላ አይሞቱም፤ የትንሣኤ ልጆች ስለሆኑም የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው::»

ኢየሱስ ለጥያቄያቸው ሁለት መልሶች ሊሰጥ ነው:: የመጀመሪያው ከእግዚአብሔር ኀይል ጋር የተገናኘ ሲሆን፣ ሁለተኛው ም ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር የተገናኘ ነው:: ሰዱቃውያን ሁለቱንም አያውቋቸውም:: በመጀመሪያ ትንሣኤ አሁን ያለውን የመሰለ አዲስ አካል ወሲባዊ ባሕርያትንም ጨምሮ እንዲኖር ግድ የሚል መሆኑን የሚያውቁ ይመስላል:: ሆኖም እግዚአብሔር ከጋብቻ ትስስር ውጭ የሆኑ አዲስ አካላትን ሊሰጠን ይችላል::

አሁን ባለንበት ዓለም ጋብቻ ውብ ሐሳብ ነው:: ለቤተ ሰብ ቡድን የቅርርብን፣ ዘር የመተካትና የክብካቤ ምንጭ ይሆናል:: ይሁን

---

[33] ይህ የሰባት ወንድማማቾች ትረካ (ወግ) በአዋልድ መጻሕፍት ውስጥ መጽሐፈ ጦቢት ላይ ከሚገኘው ታሪክ ምክንያት የተነሣ ሊሆን ይችላል (3፥8-9)፤ 6፥13-15፤ 7፥11):: ሣራ የተባለች ሴት ሰባቱም ባሎቿ በጋብቻዋ ዕለት የተገደሉ መሆናቸውን ይናገራል (ከP.G. Bolt, "What Were the Sadducees Reading? An Enquiry into the Literery Background of Mark 12:18-23," *TB* 45/2 [1994]: 369-394 ጋር ያነጻጽሩ)::



እንጂ ትንሣኤ ከእነዚህ ነገሮች አንዳቸውም አያስፈልጉትም:: አዲሲቷን ምድር የዘመናቱ ሁሉ ቅዱሳን ስለሚሞሏት ዘር መተካት ያለፈ ታሪክ ይሆናል:: ወይም ደግሞ በወሲብ አማካይነት እውን የሚሆን የቅርርብ ፍላጎት አይኖረንም:: በመንሥተ ሰማይ ቅናት ወይም ውድድር ሳይሆን የመቀራረብ ችሎታ ይኖረናል:: የቤተ ሰብ አሐድነትም አስፈላጊያችን አይሆንም፤ ምክንያቱም (1) የጥበቃ አስፈላጊነት አይኖርም፤ (2) ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረን የግንኙነት መዋቅር የማስተማር አገልግሎቱን የሚወጣ ይሆናል:: የወሲብ ብቸኛ ፋይዳ ሥጋዊ እርካታ ብቻ ይሆናል:: ይህ ቀላል ነገር አይደለም:: የመልካም ስጦታ ለጋሽ የሆነው እግዚአብሔር ወሲባዊ እርካታን በአካላችን ላይ በላቀ ስሜት የተካዋል ብሎ ማመን ተገቢ አይሆንም? ዋናው ነገር ወሲብ የሚያስፈልግ ወይም ቀረብኝ የሚባል ነገር አይሆንም::

እንግዲህ ኢየሱስ «እንደ መላእክትም ስለ ሆኑ» ሲል እነርሱ ያላቸውን ባሕርያት ሁሉ እንጋራለን ማለቱ አይደለም:: እንዲያውም ቀዳሚው ንጽጽር ከእንግዲህ አንሞትም የሚል ወይም መላእክት ወሲብ የመፈጸም ባሕርይ የሌለባቸው መሆኑን የሚያመለክት ይሆናል:: መላእክቱ መወሳታቸው ከሰዱቃውያን እምነት ጋር ይጋጫል:: ሰዱቃውያን የማያምኑት (የማይቀበሉት) የትንሣኤን ሐቅ ብቻ ሳይሆን የትንሣኤ አካላትን መልአካዊ ባሕርይም ነው (ሐሥ 23፥8)::

(«በሙሴ መጽሐፍ ... አላነበባችሁምን?»[ማር])

ሉቃ 20፥37-38
ከማር 12፥26-27
ጋር

[37]ሙሴ ስለ ቍጥቋጦ በተጻፈው ታሪክ ውስጥ ጌታን፣ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ በማለቱ ሙታን እንደሚነሡ ያሳያል፤ [38]ሁሉም በእርሱ ሕያዋን ስለ ሆኑ እርሱ የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አይደለም::» (ስለዚህ እጅግ ተሳስታችኋል[ማር])

33ሕዝቡም በሰሙ ጊዜ በትምህረቱ ተደነቁ። ማቴ 22÷33

39አንዳንድ ጸሐፍትም «መምህር ሆይ፤ መልካም ተናገርህ» አሉት። 40ከዚህ በኋላ አንድ ሰው እንኳ ሊጠይቀው አልደፈረም። ሉቃ 20÷39-40

ሁለተኛው የኢየሱስ መልስ የቅዱሳት መጻሕፍትን አተረጓጎም ይመለከታል። «አላነበባችሁምን?» የሚለው መልስ አዘል ጥያቄ ያለጥርጥር እንደ ታሰበው ተወስዶ ስድብ ነው ተባለ (ከማቴ 21÷42 ጋር ያነ)። ትንሣኤን የሚገልጹ ሁለት ምንባቦች ብሉይ ኪዳን ውስጥ ይገኛሉ (1ነገ 17÷22፤ 2ነገ 34÷35፤ 13÷21)፤ ስለዚሁ የሚናገሩ ጥቂት ምንባቦችም አሉ (ኢሳ 26÷19፤ ዳን 12÷2፤ ኢዮ 19÷25-27፤ እንዲሁም 2ሳሙ 12÷23፤ ኢሳ 53÷10-12፤ መክ 12÷7 ይመ)። መታመን ያለበት ነገር ግን የምንፈልገውን ያህል ግልጽ አለመሆኑ ነው። ጉዳዩን ውስብስብ የሚያደርገው ደግሞ ሰዱቃውያን ከሌሎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ይልቅ የሙሴን አምስቱን መጻሕፍት መምረጣቸው ይሆናል። ኢየሱስ እነርሱን ለማሳመን ከፈለገ፣ ካሉበት ወይም ከሚያውቁት ነገር መነሣት አለበት።

ኢየሱስ ከዘፀአት 3÷6 በመጥቀስ የታወቀውንና ተቀባይነት ያለውን የአይሁድ ትርጉም ተጠቅሟል።[34] ከግሱ አገባብ በመነሣት ትንሣኤ የግድ መሆን ያለበት ነገር መሆኑን አረጋገጠ። ከዚህም በላይ የእግዚአብሔር ኃያል ታላቅነት አገልጋዮቹ እርሱ ባለበት መነሣት ያለባቸው መሆኑን ይጠይቃል።[35] እግዚአብሔር የሕያዋን እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም። ጉዳዩ በትኩረት ሲታይ ግን ኢየሱስ የሚከራከረው ከነፍስ ኢመዋቲነት አንጻር ነው። አይሁድ ግን ከአካል ትንሣኤ ተለይቶ የነፍስን ኢመዋቲነት አያስተውሉም።

«በሚያሳዝን ሁኔታ ተሳስታችኋል» በማለት ኢየሱስ አጣጣላቸው። አንድ ሰው ኢየሱስ ለእነዚህ ሰዎች የንቀት ሁኔታ አሳይቷል ብሎ ሊያስብ ይችላል። ይሁን እንጂ ሰዎቹ ኢየሱስ ሊፈጽም ስላለው የመጨረሻና ታላቅ ነባራዊ ተአምር የተሣሣተ ግንዛቤ ነው የነበራቸው። ይህ ግንዛቤ ከሌላቸው ንስሓ ለመግባትና የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት ሌላ ተስፋ አይኖራቸውም። እርግጥ ነው

---

[34] መምህር ዲ. ኤም. ኮህን - ሼርቦክ የተባሉ ጸሐፊ በክርክራቸው የኢየሱስ ተጠየቅ በአይሁድ ሥነ ፍታቴ (logic) ተቀባይነት የለውም ይላሉ። የኢየሱስ ክርክር «ከራቢያዊ እይታ አንጻር» በሚያስደንቅ ሁኔታ ብቃት የለውም። ኢየሱስ እንዲህ ባለው ክርክር መጠቀም መቻሉ ሊያስደንቀን አይገባም። እንደ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ጮሌ የንግግር ሰው አለመሆኑን የሚገልጹትን ወንጌላት ሐቅ ያዘለ ነውና እስከ ማለት ደርሰዋል» ("Jesus' Defence of the Resurrection of the Dead," *JSNT* 11 [1981]: 64-73)። እርግጥ የኢየሱስ ክርክር ልዩ ነበር። ይህ የሆነው ያልሠለጠነ ገጠሬ በመሆኑ ሳይሆን፣ ብሩህ አእምሮ ያለው በመሆኑ ነበር! ሰዱቃውያን የኢየሱስን መደምደሚያ ንቀው ለመተው ይፈልጉ ነበር። ሆኖም ቀዳምያኑን የሕግ መምህራን አፍ ባስያዘበት መልሱ ምክንያት አበጀህ ብለውታል (ሉቃ **20÷39-40**)! ከዚህ በተጨማሪም F.G. Downing, "The Resurrection of the Dead: Jesus and Philo," *JSNT* 15 (1982): 42-50 በሚለው ጽሑፉ በኢየሱስ የዘፀአት 3÷15 ትንታኔና ይህንኑ በተመለከተው የፊሎ (Philo's) ትንታኔ መካከል ተመሳሳይነት መኖሩን ያስተውሏል። ስለዚህ የኢየሱስ መልስ ለሰዱቃውያን ባይሆንም፣ ለፈሪሳውያን ሥነ ፍታቴያዊ ተጠየቅ፣ ተቀባይነት ይኖረው ነበር ብለን ለመደምደም እንችላለን።

[35] ጄ. ጄ. ኪልጋላን የተባለው ጸሐፊ እንዲህ ያስቀምጠዋል፤ «ያህዌ ሕይወት ይገባቸዋል ያላቸው መነሣት ይኖርባቸዋል፤ ለእነርሱ ያለው ፍቅር ሌላ መደምደሚያ አያውቅምና» ("The Sadducees and Resurrection from the Dead: Luke 20:27-40," *Biblica* 67 [1986]: 478-495). J.G. Jansen "Resurrection and Hermeneutics: On Exodus 3:6 in Mark 12:26," *JSNT* 23 (1985): 43-58 በሚለው ጽሑፍ አንድ እርምጃ እልፍ ይላል፤ ዘፀ 3÷6 እና ማር 12÷26 የሚያተኩሩት በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ነው በማለትም ግምታቸውን ይሰነዝራሉ። ይህም ዘይቤአዊ በሆነ መልክ «ቋሚ ሞት» ተብሎ የተገለጸው ሲሆን፣ «በትውልድ ትንሣኤ» በኩል እግዚአብሔር ከዚህ ጉዳይ ታድጓቸዋል። ስለዚህ ሦስትዮሹ ቀመር፣ «አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ» የእግዚአብሔር ታማኝነትና የማዳን ሥራው መግለጫ ነው። ይህ በተለይ በዘፀ 3÷6 ዐውድ ውስጥ ነው። እግዚአብሔር የሞተ ዘራቸውን በማስነሣት (ሮሜ 4÷19፤ ዕብ 11÷11-12) ሕዝቡን የሚያድን ከሆነ፣ ከሞትስ አያድናቸውምን?

የኢየሱስ ቃሎች ብርቱ ዐልፎ ተርፎም ከባድ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ ለዚህ ወሳኝ ርእስ ጉዳይና ጊዜ ተገቢዎች ናቸው::

እንደገናም ሕዝቡ ተማረከዋል:: የሕጉ መምህራን (ፈሪሳውያን) ደስ በሚል መልኩ ተደንቀዋል:: ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ከሰዱቃውያን ጋር ተከራክረዋል፤ ሆኖም ለዘመናት በዳበረው ጥበባቸው እንደ ተገነዘቡት ኢየሱስ እንዳቀረበው ያለ ምክንያታዊና የመጨረሻ ከሆነ ማሰሪያ የሚያደርስ ነገር ለማግኘት አልቻሉም ነበር:: ሰዱቃውያን ግራ ተጋብተዋል:: ለተሰጣቸው መልስ የሚሉት ነገር ወይም የሚያቀርቡት ጥያቄ አልነበራቸውም ሁለተኛ ድል - ሰዱቃውያን ከጨዋታ ውጭ ሆኑ::

**§ 135**
**ጥያቄ ቍጥር 3 በፈሪሳውያን:- ታላቂቱ ትእዛዝ የትኛዪቱ ናት (ማቴ 22÷34-40፤ ማር 12÷28-34፤ ከሉቃ 10÷25-27 ጋር ያነ)**

(ማቴ 22)34ኢየሱስ ሰዱቃውያንን ዝም እንዳሰኛቸው ሰምተው፣ ፈሪሳውያን በአንድነት ተሰበሰቡ::

(ማር 12)28ከጸሐፍትም አንዱ (የኦሪት ሕግ አዋቂ[ማቴ]) መጥቶ ሲከራከሩ ሰማቸው፤ ኢየሱስ ለቀረበለት ጥያቄ ተገቢውን መልስ መስጠቱን አስተውሎ፣ «ለመሆኑ ከትእዛዛት ሁሉ የሚበልጠው የትኛው ነው?» ሲል ጠየቀው::

በመጀመሪያው ዙር ፈሪሳውያን ኢየሱስን ለማጥመድ ከሄሮድሳውያን ጋር ደቀ መዛሙሮቻቸውን ላኩና ክፉኛ ተሸነፉ:: ከዚያም አላዋቂዎችን ከመላክ ይልቅ ከፍተኛ የሕግ ሊቃውንትን ለመላክ በመወሰን እንደገና ተደራጁ:: ሰዱቃውያን ክርስቶስን ለማሸነፍ ጥረት ሲያደርጉ ለመታዘብ በወቅቱ እስፍራው ደረሰ:: ከሄሮድሳውያን የተሻለ ዕድል አልነበራቸውም:: ይህ ደግሞ ፈሪሳውያንን ያለጥርጥር ደስ አሰኝቷል::



አሁን ይህ የሕግ ዐዋቂ ከሌሎቹ ይልቅ ለኢየሱስ ወዳጅ ይመስላል፤ (1) ኢየሱስ ለሰዱቃውያን አጥጋቢ መልስ የሰጠ መሆኑን ልብ ብሏል፤ (2) የላቀ ምክንያታዊና አስፈላጊ ጥያቄ ይጠይቃል፤ (3) የኢየሱስ መልስ አርኪ መሆኑን አምኖአል፤ ስለዚህ (4) ኢየሱስ ይህ ሰው ከእግዚአብሔር መንግሥት የራቀ እንዳልሆነ በመግለጽ እውነተኛ መሆኑን አረጋገጠለት::

የሕግ አዋቂው ጥያቄ በፈሪሳውያን ዘንድ የታወቀ ክርክር ነበር:: ከስድስት መቶ ዐሥራ ሦስት የብሉይ ኪዳን ትእዛዛትና ጉልቍ መሳፍርት ከሌላቸው ትውፊቶች አንጻር ሲታይ መልሱ እንዲህ ቀላል አለነበረም:: ኢየሱስ ይህን ጥያቄ ሲጠየቅ የመጀመሪያ ጊዜው እንዳልሆነም ልብ ማለት አለብን:: አንድ ቀን አንድ ሕግ ዐዋቂ ወደ ኢየሱስ መጥቶ፣ «የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ላድርግ?» አለው:: ኢየሱስም፣ «በሕግ የተጻፈው ምንድን ነው እንዴትስ ታነበዋለህ?» በማለት ጥያቄውን ወደ ራሱ መለሰበት:: ሕግ ዐዋቂውም እነዚህኑ ሁለት ትእዛዞች በመድገም መለሰ:: ይህም የደጉ ሳምራዊ ምሳሌ መነሻ ሐሳብ ሆነ (ሉቃ 10÷25-37፤ ክፍል 103):: ስለዚህ ጥያቄውም ሆነ የኢየሱስ መልስ አዲስ አይደለም::[36]

**ማር 12÷29-30**

29ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ «ከሁሉ የሚበልጠው ይህ ነው፤ 'እስራኤል ሆይ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፤ 30አንተም ጌታ አምላክህን

[36] እንዲያውም፣ E.E. Lemcio, "Pirke 'Abot 1:2(3) and the Synoptic Redactions of the Commands to Love God and Neighbor," *ATJ* 43 (1988): 43-53 በሚለው ላይ የዘዳ 6÷5 እና የዘሌ 19÷18 ጥምረት የተመሠረተው በ Simon the Just (በግምት 350-200 B.C.E.) «ዓለም የቆመችው በሦስት ዐምዶች ላይ ነው» በሚለው ነው ይላል፤ ይኸውም፣ «በቶራህ፣ በ[ቤተ መቅደስ] አገልግሎትና ከፍቅር ቸርነት የተነሣ በሚከናወኑ ሥራዎች» ነው:: [*Prike 'Abot* 1:2 [3]).

በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህና በፍጹም ኃይልህ ውደድ፡፡ '

[38]«ይህ የመጀመሪያውና ከሁሉ የሚበልጠው ትእዛዝ ነው፤

ማቴ 22፥38

[31]ሁለተኛውም ይህ ነው (ያንኑ ይመስላል[ማቴ])፤ 'ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ፡፡' ከእነዚህም የሚበልጥ ትእዛዝ የለም፡፡»

ማር 12፥31
ከማቴ 22፥39 ጋር

[40]«ሕግና ነቢያት በእነዚህ ሁለት ትእዛዛት ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው፡፡»

ማቴ 22፥40

[*ማቴ* 22፥37-39 *እና ማር* 12፥29-31 = *ሉቃ* 10፥27 የክፍል § 103 *ማብራሪያን ይመ*]

ዘዳግም 6፥4-6 ውስጥ ያለው የመጀመሪያ ትዕዛዝ «ሽማ» ሲሆን፣ በዕብራይስጡ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ከመጀመሪያው ቃል «ሰማ» በሚለው የተሰየመ ነው:: ሃይማኖተኛ አይሁድ በቀኑ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ የሚደግሙት ሲሆን፣ በየዕለቱ ዓርብ የምሽት የምኩራብ አገልግሎት ይከፈትበታል:: ይህ «ዮሐንስ 3፥16» የአይሁድ ሃይማኖት ሲሆን በብራናና በብራና ትልታይ ላይ ይጻፍ ነበር::[37] የእግዚአብሔርን አንድነትና እርሱን በሁለንተናችን የመውደድ ግዴታ ያለብን መሆኑን ያረጋግጣል:: ለአንድ አይሁድ ከዚህ የላቀ ግዴታ ከዚህም የላቀ እምነት ወይም መርሕ አልነበረም:: ኢየሱስ በጥበቡ ከሁሉ የሚበልጠውን ትእዛዝ መረጠ::

ብልጉ ተማሪ ዘዳግም ሦስት ገላጭ ቃሎች ብቻ (ልብ፣ ነፍስ፣ ኀይል) ሲኖሩ ማርቆስ ግን *ሐሳብን* በመጨመር በአራት ገላጭ ቃላት

[37] O.S. Brooks, "The Function of the Double Love Command in Matthew 22:34-40," *AUSS* 36/1 (1988): 7-22.



መጠቀሙን ልብ ብሏል:: የዚህ ምክንያቱ ሦስተኛው የዕብራይስጥ ቃል ጥንድ ልዩ ነገሮችን የሚያመለክት መሆኑ ነው:: ማርቆስ (12፥30) እና ሉቃስ (10፥37) ሁለቱም ለአያሌ አሕዛብ ተደራስያን በመጻፍ ያን አንድ የዕብራይስጥ ቃል በትክክል በመተርጐም፣ ሁለት ግሪክኛ ቃሎችን (*ሐሳብ* እና *ኀይል*) የሚሉትን ተጠቀሙ:: ሆኖም አራቱም ለየቅላቸው አይደሉም፤ ሁሉም የተሳሰሩ ናቸው::

ሁለተኛው ታላቅ ትእዛዝ የመጣው ከዘሌዋውያን 19፥18 ነው:: ታላቁ ግዴታችን እግዚአብሔርን መውደድ መሆኑን ከተገነዘብን፣ የታወቀው ጥያቄ «አንድ ሰው ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር እንዴት ይገልጻል?» የሚል ነው:: እርግጥ ነው ይህን በሥርዐትና በአምልኮ ልንፈጽመው እንችላለን፤ ይህም ሃይማኖታዊ ሥርዐት ነው:: ይህ ግን በማኅበረሰቡ ውስጥ በእጅጉ የሚጠቅም አይደለም::[38] የወዳጆቻችንን ፍላጎት በማሟላት ለእርሱ ያለንን ፍቅር እንገልጽ ዘንድ እግዚአብሔር ይፈልጋል (ማቴ 25፥40-45)፤ ወዳጅ ሲባል ደግሞ ኢየሱስ በሰጠው ትምህርት መሠረት ያገኘነው ሰው ሁሉ ማለት ነው (ሉቃ 10፥25-37):: እነዚህን ትእዛዞች ብንፈጽም ሙሉውን የብሉይ ኪዳን ዐይነተኛ ሕግጋት ፈጸምን ማለት ነው (ሮሜ 13፥8:10፤ ገላ 5፥14፤ ያዕ 2፥8)::

ማር 12፥32-34

[32]ጸሐፊውም እንዲህ አለው፤ «መምህር ሆይ፤ መልካም ብለሃል፤ እርሱ አንድ መሆኑን ከእርሱም ሌላ አለመኖሩን መናገርህ ትክክል ነው፤ [33]እርሱን በፍጹም

[38] ኤ ማላማ የተባለ ጸሐፊ፣ «ፍቅር በኢተሻጋሪ ግስ ሲገባ (በዘሌ 18፥34፤ በ1ነገ 5፥1፤ በ2ዜና 19፥2 ላይ 4 ጊዜ ብቻ ነው) ስለ ስሜት ሳይሆን ስለ ድርጊት ያሳያል» ይላል:: እንዲህ በማለትም በተጨማሪ ይገልጻል፤ «መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ነገር ማለትም ፍቅር እንዲሰማን ሳይሆን፤ አንድ ነገር እንድንፈጽም ነው የሚያዝዘን:: ለወዳጅህ ጠቃሚና ረዳት እንድትሆን ነው የሚያዝህ:: ይህ ግንዛቤ አንዳንዶች ያላቸውን የራስ ፍቅርና አድናቆት ከምንባቡ ያስወግዳል ("Love Your Neighbor as Yourself," *BAR* 16 [1990] 50-51)::

ልብህ፣ በፍጹም ሐሳብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ኃይልህ መውደድ፣ እንዲሁም ባልንጀራህን እንደ ራስህ መውደድ ከሚቃጠል መሥዋዕት ሁሉና ከሌሎችም መሥዋዕቶች ይበልጣል::»

34ኢየሱስም በማስተዋል እንደ መለሰለት አይቶ፣ «አንተ ከእግዚአብሔር መንግሥት የራቅህ አይደለህም» አለው:: ከዚህ በኋላ ሊጠይቀው የደፈረ ማንም አልነበረም::

ይህ ሕግ ዐዋቂ ተማርኮአል:: ኢየሱስ የዚህን አይሁዳዊ ልብ ነክቶታል:: ለእውነተኛ ይሁዲ እውነተኛ የሆነውን አንድ እግዚአብሔር ከመውደድና ለወዳጅ ቸርነት ከማድረግ የላቀ ዐይነተኛ (ዋና) ጉዳይ የለም:: እነዚህ እንደ መባዎችና መሥዋዕቶች ካሉት የአምልኮ ሥርዐታዊ ምልክቶች በጣም የላቁ ናቸው (1ሳሙ 15÷22፤ ሆሴ 6÷6)::

የተደነቀው ሕግ ዐዋቂው ብቻ አልነበረም፤ ኢየሱስም በሕግ ዐዋቂው ተደንቋል:: ሰውዬው ወደ ኢየሱስ የቀረበው በአክብሮት ነው፤ ብርቱና አስፈላጊ የሆነ ጥያቄም አቅርቧል:: የኢየሱስ መልስ አርኪ እንደ ሆነ በይፋ (በአደባባይ) ገልጾአል:: ስለዚህ ኢየሱስ፣ «አንተ ከእግዚአብሔር መንግሥት የራቅህ አይደለህም» በማለት አረጋገጠለት:: ይህ ሰው ወደ ተባለው ስፍራ ይግባ ወይም አይግባ የተነገረን ነገር የለም:: ይህ መለስተኛ መረጃ የኢየሱስ ተቃዋሚዎች ሁሉ መጥፎዎች እንዳልነበሩ ያመለክተናል:: ፈሪሳውያን ሥጋ የለበሱ የክፋት ኃይሎች አይደሉም:: የሚንከባከቡት ክብርና ሹመት ያላቸው የሃይማኖት መሪዎች ናቸው:: ለዚህ ወገን ወደ ክርስቶስ በአካል መምጣት ብርቱ መሥዋዕትነት ነበር::

እንግዲህ ይህ ሦስተኛው ድል ነው፤ ፈሪሳውያን ከጨዋታ ውጭ ሆነዋል:: ሁሉም ዐበይት ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ቡድኖች



ኢየሱስን ለማጥመድ ሙከራ አድርገዋል፤ ያተረፉት ነገር ቢኖር ክፉኛ መልሶ መጠቃትን ነው:: ከዚህ በኋላ ማንም ተጨማሪ ጥያቄ ለመጠየቅ ድፍረት አለማግኘቱ አያስገርምም::

ኢየሱስ እነዚህን ጥያቄዎች በዘመኑ ከነበሩት ሦስት ወገኖች (ጐራዎች) አንጻር ነበር:: ሌላ ተጨማሪ ጥያቄ አልነበራቸውም:: ኢየሱስ ግን ለእነርሱ የሚያቀርበው ጥያቄ ነበረው፤ መመለስ ያለበት ብቸኛ ጥያቄ ነበር፤ በእጅጉ ወሳኝ የሆነ ጥያቄም ነው፤ ኢየሱስ ማን ነው?

**§ 136**
**ጥያቄ ቍጥር 4፣**
**በኢየሱስ የቀረበ:-**
**ክርስቶስ እንዴት**
**የዳዊት ልጅ ሊሆን**
**ይችላል**
**ማቴ 22÷41-46፤**
**ማር 12÷35-37፤**
**ሉቃ 20÷41-44**

(ማቴ 22:41)ፈሪሳውያን ተሰብስበው ሳሉ ኢየሱስ፣ (በቤተ መቅደሱ አደባባይ በሚያስተምርበት ጊዜ[ማር])
እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፤ 42«ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው?»

እነርሱም፣ «የዳዊት ልጅ ነው» አሉት::

43እርሱም እንዲህ አላቸው፤ «(ጸሐፍት እንዴት ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ነው ይላሉ?[ማር]) «ታዲያ ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል (ሲናገር[ማር]) ለምን 'ጌታዬ' ይለዋል (በመዝሙራት መጽሐፍ[ሉቃ]) ለምንስ፣ እንዲህ ይለዋል?

44«'እግዚአብሔር ጌታዬን፣

ጠላቶችህን ከእግርህ በታች (ጠላቶችህን ለእግርህ መርገጫ እስከማደርግልህ ድረስ[ሉቃ])»'

45ስለዚህ ዳዊት፣ 'ጌታዬ' ብሎ ከጠራው እንዴት ልጁ ሊሆን ይችላል?»
46አንድ ቃል ሊመልስለት የቻለ ወይም ከዚያን ቀን ጀምሮ ሊጠይቀው የደፈረ ማንም አልነበረም:: (ብዙ ሕዝብም በደስታ ይሰማው ነበር[ማር])::

በዚህ በሦስተኛው ዙር መጨረሻ የአይሁድ አለቆች ፈጽሞ ተሰፋ ቈርጠዋል፤ ሕዝቡ ደግሞ እጅግ ደስ ብሏቸዋል:: ይህ ዐቢይ

የአንድነት ድምቀት ነው! እንግዲህ ኢየሱስ ጥያቄያቸውን ሁሉ ከንቱ አድርጓል፤ አሁን ደግሞ ተራው የእርሱ ነው፤ ጥያቄውን መመለስ ይኖርባቸዋል::

ቀላል ጥያቄ ነበር፤ «ክርስቶስ ማን ነው?» እርሱማ የዳዊት ልጅ ነው (የዳዊት ዘር)፤ ማንም ይህን ያውቃል (ከ2ሳሙ 7÷13-14፤ ከኢሳ 9÷2-7፤ 11÷1:10፤ ከኤር 23÷5፤ ወዘተ ጋር ያነ):: «መልካም ነው» አለ ኢየሱስ፤ «ይህ እንዳለ ሆኖ ከቍጥር 1 በመጀመር መዝሙር 110ን እናፍታታው:: ክርስቶስ የዳዊት ልጅና የዳዊት አምላክ (አዶናይ) እንዴት ሊሆን ይችላል?» በጥንድ ምክንያቶች የተነሣ ይህ ይበልጥ አስቸጋሪ ጥያቄ ነው:: በመጀመሪያ በባህላቸው አባት ከልጅ ምንጊዜም የላቀ ነው:: ዳዊት ከልጆቹ አንዱን «አምላኬ» ብሎ የሚጠራበት «ተፈጥሮዊ» መንገድ የለም:: ሁለተኛ ይህ መዝሙር የክርስቶስን መምጣት አስቀድሞ በመናገሩ (በመተንበዩ) መሲሓዊ መዝሙር ተብሎ ይታወቃል:: አዲስ ኪዳን ውስጥ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ የተጠቀሰ የብሉይ ኪዳን ክፍልም ነው (ሐሥ 2÷34-35፤ ዕብ 1÷13፤ 5÷6፤ 7÷17:21፤ 10÷13):: ሊያመልጡት ወይም ሊክዱት አልቻሉም:: እንዲያውም እኮ ኢየሱስ ስለ መጽሐፉ ሲናገር እስትንፋስ መንፈስ ቅዱስ ያለበት ነው ብሏል (ከዮሐ 10÷35፤ እንዲሁም ከሐሥ 4÷25፤ ከዕብ 3÷7፤ 9÷8፤ 10÷15፤ ከ2ጴጥ 1÷21 ጋር ያነ):: ይህንንም ሊገልጹት አልቻሉ!

እንድምታው ይህ የዳዊት ልጅ የሆነው (ይህም በእርግጥ ኢየሱስን በማመልከት ነው [ማቴ 1÷1፤ ሉቃ 3÷23:31]) የእግዚአብሔርም መለኮታዊ ልጅ መሆኑ ነው (ጳውሎስ በሮሜ 1÷3-4 ላይ ይህን በደንብ ያብራራል):: በነቢያትም ይህን የሚያሳዩ ብዙ ምልክቶች ነበሩ (ኢሳ 9÷6፤ ኤር 23÷5-6፤ 33÷15-16፤ ዘካ 12÷10፤ 13÷7):: ይህ ከሆነ ዘንድ እግዚአብሔርን ተሳድቧል የሚለው ክሳቸው



ሐሰት ነው:: የኢየሱስን መሲሕነት መቃወማቸውም ራሱን እግዚአብሔርን መቃወማቸው ነበር::

የመዝሙር 110ን የመጀመሪያ ጥቅስ የመጀመሪያ ክፍል ለመግለጽ አልቻሉም:: ኢየሱስ ወደ ጥቅሱ ሁለተኛ ክፍል እንኳ አልደረሰም:- «ጠላቶችህን ለእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ!» ወደሚለው ይህ ቃል በጠላትነት ለቆሙት ጠያቂዎች አስፈሪ ሐሳብ ነበር:: ኢየሱስ በቍጥር 2 ውስጥ ተጨማሪ ማብራሪያ ሊሰጥ ይችል ነበር:- «እግዚአብሔር ብርቱ በትርህን ከጽዮን ወደ ውጭ ይሰዳል» ወይም ደግሞ በቍጥር 4 ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ሊሰጥ ይችል ነበር:- «እንደ መልከ ጸዴቅ ሥርዐት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ::» ብሎ:: ንጉሥ እንዴት ካህን ሊሆን ይችላል? መልሱ በቀራንዮ ይመጣል::

«የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን» ለሆኑት ሰዎች ከባድ ድንጋጤን የፈጠረ ነገር መሆን አለበት:: መሠረታዊ ስለ ሆነው እምነታቸው ጥልቅ ግንዛቤ እንደሌላቸው ተገነዘቡ:: ትምህርት በሌለው በዚህ የገሊላ ሰው ድንዛዜ ገብቷቸዋል:: ያመለጠው ከነገረ መለኮታቸው ሽምቀቆ ብቻ ሳይሆን፣ በጣም ከሚወዷቸው ጥቅሶች ውስጥ በአንዱ አማካይነት ባቀረበው ቀላል ጥያቄም ነበር:: ይህን የፈጸመው አመች ሊሆንላቸው በሚችለው ግቢና በቤተ መቅደሱ አደባባያቸው እምብርት ላይ ነው:: አለቆቹ እንቅፋት ገጠማቸው:: ሕዝቡ ግን በጣም ደስ አላቸው::

**§ 137ሀ**
**«እናንተ ... የኦሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ... ወዮላችሁ (ማቴ 23÷1-36፤ ማር 12÷38-40፤ ሉቃ 20÷45-47፤ ከሉቃ 11÷37-54 ጋር ያነ)**

ይህ ማክሰኞ ዕለት በቤተ መቅደሱ ለተሰጠው ትምህርት መደምደሚያ ነበር:: የአይሁድ አለቆች በሽንፈት ወደ ኋላ ሳያፈገፍጉ አልቀረም (ማቴ 22÷22:34:36):: ከዚህ በኋላ የኢየሱስን ግድያ ለማቀድ ሄዱ:: ሕዝቡ ግን በመጠንና ሐሤት በማድረግ

*እየጨመሩ መጡ:: ኢየሱስ በዚህ በሚያስደንቅ*
*መሪር ተግሣጽ ወደ ፈሪሳውያን ተመለከተ::*
*በጣም ብርቱ ተግሣጽ*

በመሆኑ አንዳንዶች በማቴዎስ ምዕራፍ 23 እና በተራራው ስብከት (5-7) መካከል ግጭት አለ እስከ ማለት ደረሱ:: የተራራው ስብከትም አንዳንድ አስፈሪና ብርቱ ማስጠንቀቂያዎች አሉት (ለምሳሌ ማቴ 7÷13-29):: ይህ ትምህርት የተደመደመው ለአይሁድ ሕዝብ ቅን በሆነ መልኩ ግድ በመስኘት (በመጨነቅ) (ቍ 37-39)[39] ነበር:: ኢየሱስ ይህን ዐይነቱን ነገር በልዩ ልዩ ቦታዎችና ሁኔታዎች ከዚህ ቀደም የተናገረው ሲሆን (ለምሳሌ ሉቃ 11÷35-54) እዚህ ላይ የተዘረዘረው ይበልጥ ሙሉ በሙሉ ነው:: በመጨረሻም እነዚህ ፈሪሳውያን እርሱን ለማጥመድ ሙከራ ያደረጉ መሆናቸውንና አሁን ደግሞ ሞቱን ማቀዳቸውን ማስታወስ አለብን:: ስለዚህ የኢየሱስ ምላሽ በቂ ምክንያት ያለውና ተመጣጣኝ ነው::

ኢየሱስ የመግቢያ ማስጠንቀቂያ ለደቀ መዛሙርቱ ከሰጠ በኋላ (ቍ 1-12)፣ ተከታታይ የሆኑ ሰባት «ወዮዎችን» አቀረበ:: «ወዮ» [*ouai*] የሚለው ቃል አሳዛኝ ቃሎችን፣ ቍጣንና ሓቅን ሊያካትት ይችላል:: በአንድ ጊዜም ከሁሉም መጠነኛ የሆነውን ሊያካትት ይችላል:: የመጀመሪያዎቹ ስድስቱ ጥንድ ሆነው መጥተዋል:: አንድና ሁለት የፈሪሳውያንን የወንጌል ሥርጭት፤ ሦስትና አራት ደግሞ

[39] ኢየሱስ ጸረ ሰማያዊ አቋም ነበረው የሚለው ክስ የሚከተለውን ያልተገነዘበ ነው:- (1) ኢየሱስና «የሕይወት ታሪክ ጸሐፊው» ማቴዎስ ራሳቸው ከአይሁድ ወገን ሲሆኑ፣ በአይሁድ ዘንድ ወንጌል እንዲሠራጭ ናፍቆት ነበራቸው:: (2) ኢየሱስ አንዱን ያመራር ክፍል እንጂ አይሁድን ሁሉ አልነቀፈም:: ይህ ተግሣጽም ለፈሪሳውያን «ወገን» እንጂ ለእያንዳንዱ ፈሪሳዊ አልነበረም:: (3) እነዚህ ቡድኖች እርሱን ለማጥመድ ሞከሩ፤ አሁን ደግሞ ሊገድሉት ያሤራሉ:: (4) ኢየሱስ እውነቱን ተናገረ፤ የዚህን ቡድን ባሕርይም በትክክል ገለጸ:: ደግሞም (5) የኢየሱስ ቃሎች ከብዙዎቹ መዝሙሮችና ነቢያት የከፉ አልነበሩም (ለምሳሌ መዝ 58፤ ኢሳ 5÷8-23፤ ኤር 23፤ ዕን 2÷6-20)::



ሥርዐቶቻቸውን፣ አምስትና ስድስት ደግሞ ውስጣዊው ንጽሕና ከውጫዊው ንጽሕና ጋር አለመገጣጠሙን ይመለከታሉ:: ትልቁና የመጨረሻው ቍጥር ሰባት፣ የጕዳዩን ዋና ሐሳብ ይኸውም ኢየሱስን ለመግደል ያላቸውን ፍላጎት ይመለከታል::

[1]ከዚያም ኢየሱስ ለሕዝቡና ለደቀ መዛሙርቱ
እንዲህ ሲል ተናገረ፤ [2]«የኦሪት ሕግ መምህራንና ማቴ 23÷1-4
ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ላይ ተቀምጠዋል:: [3]ስለዚህ
የሚነግሯችሁን ሁሉ አድርጉ፤ ጠብቁትም፤ ነገር ግን እንደሚናገሩት አያደርጉምና
ተግባራቸውን አትከተሉ:: [4]እንዲሁም ለመሸከም የማይቻል ከባድ ሸክም አስረው
በሰዎች ትከሻ ላይ ይጭናሉ፤ ራሳቸው ግን በጣታቸው እንኳ አይነኩትም::»

የኢየሱስ አድማጮች ሁለት ወገኖችን ያካተቱ ናቸው:: እነሱም ሁኔታውን ለማየት የመጡ ደቀ መዛሙርትና ራሳቸውን በመለስተኛ መልኩ አሳልፈው የሰጡ ሕዝብ ነበሩ:: በሁለቱ ወገኖች መካከል የነበረውን ልዩነት ለመወሰን ግን በመጠኑም ቢሆን አስቸጋሪ ነው:: በሌላ አንጻር የኢየሱስ ዓላማ ያነጣጠረው በሁለት ወገኖች ላይ ነው:- በፈሪሳውያንንና በሕግ መምህራን:: በእነዚህ ወገኖች መካከል ያለው ልዩነት እምብዛም ጕልሕ አይደለም:: «ፈሪሳዊ» የሚለው ቃል ሃይማኖትንና ፖለቲካን አጣምረው የያዙትን መንፈሳዊ ወገኖች የሚመለከት ሲሆን፣ «የሕጉ መምህራን» የሚለው ግን እንደ ፈሪሳውያን አንድ ዓይነት ዝንባሌ ያላቸውንና ከዚሁ ከፈሪሳዊ ወገን ሆነው መጽሐፍ ቅዱሳዊና ትምህርታዊ የሆነውን ተግባራቸውን በተለይ ያመለክታሉ:: ልዩነቶቹ ጥቂትና ረቂቅ ናቸው::

እነዚህ ሰዎች በሙሴ ወንበር ላይ ተቀምጠዋል:: ምኵራቡ ውስጥ የሙሴን ወንበር የሚወክል ወንበር አለ:: እዚያ ላይ የሚቀመጥ የምኵራቡ ቀዳሚ መምህር ነው:: ማኅበረ ሰቡ ውስጥ ያለን ሹመትና ሥልጣን የሚያመለክት ዋና ወንበር ነው:: እስከ ሙሴ ድረስ ወደ ኋላ

በመጓዝ የተተኪነትን መሥመር ይወክላል:: ይህ የታወቀ መምህር የሙሴን የመሪነት ካባ ደርቧል:: የቀደሙትን ትውልዶች የእምነት ችቦም ይዞአል:: በእኛ ዘመን ተተካካይ ሥልጣን ያለው ትምህርተ ምልክት ምስባክ ነው:: ምስባኩ ላይ የሚገኝ ሰው (የምስባኩ «ባለቤት») የጉባኤውን ጆሮ ይቈጣጠራል:: ይህ ሥልጣን የፈሪሳውያኑ ነበር::

«ስለዚህ» አለ ኢየሱስ፣ «የሚነግሯችሁን ሁሉ አድርጉ::» የኢየሱስ አባባል ሙሉ በሙሉ ይህ ሊሆን አይችልም:: ፈሪሳውያን ትውፊታቸው ውስጥ የተወሳሰቡና በሺህ ቤት የሚቈጠሩ ጥቃቅን ደንቦች አሏቸው:: ኢየሱስ ሆን ብሎ ከንቱ የሆኑትን የፈሪሳውያን ትውፊታዊ ትምህርቶች ሽሯል (ማቴ 9፥10-13፤ ማር 2፥18-19:23-24፤ ሉቃ 6፥6-8፤ 11፥38-39፤ ዮሐ 5፥8-10):: እርግጥ «ጥቅም የለሽ የሆኑትን ደንቦቻቸውን ሁሉ አክብሩ» ማለቱ አይደለም:: ያለው፣ «ሙሴ ያስተማረውን እስካስተማሩ ድረስ ተከተሏቸው» ነው (ከዘዳ 17፥10 ጋር ያነ):: ይህ በእርግጥ ኢየሱስ በተናገረው ላይ መጨመርን ይጠይቃል:: በመሆኑም በኢየሱስ ንግግር ውስጥ ጥቂት አሽሙር ለማንበብ እንፈልጋለን:: እንደሚታወቀው አሽሙር (ፌዝ) ለኢየሱስ ፈጽሞ ባዕድ ነገር አልነበረም:: የርሱን ቃል በራሳችን አባባል ልንገልጸው እንችላለን፤ «ዋና ዋና የሆኑትን የሥልጣን ቦታዎች ይዘዋል፤ ስለዚህ እነርሱ የሚሏችሁን ብትከተሉ መልካም ይሆንላችኋል፤ ምሳሌነታቸውን መከተሉ ግን ይገድላችኋል!»

የብሉይ ኪዳንን ሕግ መጠበቁ ከባድ ነገር ነው:: እነዚህ ሰዎች ደግሞ ሕግ ዐዋቂ ብቻ ሊገነዘባቸው የሚቻለውን ጥቃቅን ደንቦች ጨምረዋል:: የላቀ መሰጠት ስላላቸው እነርሱ ሊያከብሩት ይችላሉ (ማምለጫ ቀዳዳውን ሁሉ የሚያውቁ መሆናቸውን መግለጽ አስፈላጊ አይደለም):: ተራው ሰው ግን ሌላ ዕድል የለውም:: እነርሱ ደግሞ ሸክሙን የሚያቃልሉት አይደሉም:: ከዚያ ይልቅ በተጨማሪ ደንቦችና በበደለኛነት ስሜት መከራውን ያበሉታል:: ይህ ደግሞ ኢየሱስ በእኛ



ሕይወት ከሚሠራው በጎ ነገር የተለየ ነው (ከማቴ 11፥28-30 ጋር ያነ)::

5«ስመታየት ሲሉ የሚያደርጉትን ሁሉ በሰው
ፊት ያደርጋሉ፤ አሸንክባታቸውን[*] ያሰፋሉ፤
የቀሚሳቸውን ዘርፍ ያስረዝማሉ:: 6በግብዣ ቦታ
የከበሬታ ስፍራ፣ በምኵራብም የመጀመሪያውን
መቀመጫ መያዝ ይወዳሉ:: 7እንዲሁም በገበያ መካከል
ሰላምታ መቀበልንና በሰዎች እንደበት መምህር ተብለው
መጠራትን ይሻሉ::

ማቴ 23፥5-12

8«እናንተ ግን 'መምህር' ተብላችሁ አትጠሩ፤ አስተማሪያችሁ አንድ ብቻ
ሲሆን፣ እናንተ ሁላችሁም ወንድማማቾች ናችሁና:: 9በሰማይ ያለ አንድ አባት
ስላላችሁ፣ በምድር ማንንም 'አባት' ብላችሁ አትጥሩ:: 10መምህራችሁ አንዱ
ክርስቶስ ስለ ሆነ፣ 'መምህር' ተብላችሁ አትጠሩ:: 11ከመካከላችሁ ከሁላችሁ
የሚበልጠው አገልጋያችሁ ይሆናል፤ 12ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ይዋረዳል፤ ራሱን
የሚያዋርድ ግን ይከብራል::

*[*]5 ከቅዱሳት መጻሕፍት የተወሰዱ ጥቅሶች የተጻፉበት በግንባርና በክንድ ላይ የሚታሰር ትንሽ ጥቅልል ነው::*

የአንድ ፈሪሳዊ ቀዳሚ ዐላማ መታወቅ ነው:: ይህን በማዕረግ ስሞች፣ በሹመትና ሃይማኖታዊ ግዴታዎችን በማከናወን ይፈጽመዋል:: ኢየሱስ እንዲህ ያሉትን ሁለት ሃይማኖታዊ ግዴታዎች ከዚህ ላይ ይጠቅሳል:: የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት (አሸንክታብ) እና ጸሎት (ከልብሳቸው ጫፍ ላይ ተጠቅልሎ የሚያዝ ጽሑፍ ነው):: እነዚህ አሸንክታቦች በግንባር ወይም በግራ እጅ ላይ የሚታሠሩ

ነበሩ::[40] ዘፀአት 13÷2-16ን፤ ዘዳግም 6÷4-9 እና 11÷13-21 የያዙት ትንንሽና ጥቅልል ጽሑፎችን ነው:: ይህ ልምድ የተፈጠረው ዘዳግም 6÷8ንና 11÷18ን ከልክ ባለፈ ቃል በቃል ከመተርጐም የተነሣ ነው:: «እነዚህን ቃሎቼን በልባችሁና በአእምሮአችሁ አኑሯቸው፤ በእጆቻችሁ ላይ ምልክት አድርጋችሁ እሰራቸው፤ በግምባራችሁም ላይ ይሁኑ::» እንደ ጣኦት አምላኪዎች የድግምት ጽሑፍ ሆነዋል:: ፈሪሳውያን በቀላሉ እንዲታዩ ትናንሽ ጥቅል ጽሑፎቻቸውንና ልብስ ጫፍ ላይ የሚታሰሩትን ጽሑፎቻቸውን በትልቁ ያጽፉ ነበር::

እንደዚሁም በልብሳቸው ጫፍ ላይ የሚገኘውን የጸሎት ጽሑፍ በትልቁ ያደርጋሉ:: ይህ በማንኛውም የአይሁድ ልብስ ላይ የሚደረግና የተለመደ ነው (ዘኁ 15÷37-41፤ ዘዳ 22÷12):: ኢየሱስ እንኳ እንዲህ ዐይነቱን ልብስ ይለብስ ነበር (ማቴ 9÷21):: በቀላሉ በጣት የሚያዙ ሲሆኑ፣ አንድ ሰው ግዴታዊ የእምነት ጸሎት ሲደግም እንደ መቍጠሪያ ያገለግሉት ነበር:: በቀላሉ እንዲታይ ሆኖ ነው የሚዘጋጀው፤ ፈሪሳውያን ይህን የሚያደርጉት ከማንኛውም ሰው ይልቅ ጸሎት አድራጊ መሆናቸውን ለማሳየትም ፈልገው ሳይሆን አልቀረም::

ፈሪሳውያን በማዕረግ ስሞቻቸውም ለመታወቅ ፈለጉ:: ምኵራብ ውስጥ «የሙሴን» ወንበር ምንኛ እንደ ተመኙ አይተናል:: የምኵራቡ ቀዳሚ መምህር መሆኑ ባይሳካላቸው እንኳ በግብዝ ችሎታቸው እያንዳንዱ ሰው ሊያያቸው ከሚችለው መድረክ ላይ መቀመጥን ፈለጉ:: ለእራት ግብዣ ሲሄዱ ከጋባዡ አጠገብ ያለውን የክብር ወንበር ለመያዝ ይጓጉ ነበር (ከሉቃ 14÷7-11 ጋር ያነ፤ የክፍል 114 ማብራሪያን ይመ)::

---

[40] Cf. J.H. Tigay, "On the Term Phylacteries (Matt 23:5), *HTR* 72 (1979) 45-53 በሚለው ላይ የግሪኩ ቃል *ፋይላክቴሪያ* - *phylakteria* አሽንክታብን ወይም ክታብን ያመለክታል ይላል:: ከዚህ በመነሣትም የዕብራይስጡን *ታፊሊንን* - *tefillin* ለመተርጐም የግሪኩን ፋይላክቴሪያን መጠቀሙ እነዚህ ማኅደሮች ለፈሪሳውያን ወደ ክታብ ደረጃ መውረዳቸውን ያመለክታል ይላል::



«ረቢ» (ቃል በቃል፣ «የእኔ ኀያል»)፣ «መምህር» ዐልፎ ተርፎም «አባት» በሚሉ ማዕረጎች (ላለፉት ታላላቅ ረቢያውያን ብቻ ተጠብቆ የኖረውን ማዕረግ) ለመታወቅ ፈለጉ:: ከዚህ ቀደም እንዳየነው የኢየሱስ ትምህርት ምንጊዜም ቃል በቃል መታየት የለበትም (ምሳሌ ማቴ 5÷22:29፤ 6÷3:6:17):: እዚህ ያለውም እንደዚሁ ነው:: ለምሳሌ የሥጋ አባትህን «አባት» ወይም መካሪ ብሎ መጥራት ስሕተት የለበትም (1ቆሮ 4÷15፤ ሐሥ 22÷1፤ 1ዮሐ 2÷13):: ወይም ደግሞ አንድን ሰው «መምህር» ብሎ መጥራቱ ምንጊዜም ስሕተት ነው ማለት አይደለም (ሐሥ 13÷1፤ 1ጢሞ 2÷7፤ ኤፌ 4÷11፤ ያዕ 3÷1):: ነገር ግን የአንድን ግለሰብ የሥራ ውጤት፣ ትዕቢት በሚያሳድር መልኩ ከፍ ከፍ የሚያደርጉትን ወይም ወንድሞችን በደረጃ የሚከፋፍሉትን ማዕረጎች በጥብቅ መከላከል አለብን:: ምስጋናና ክብር የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ ነው:: እግዚአብሔርን የሚያርቁ የታይታ ማዕረጎች ለኢየሱስ ደቀ መዛሙርት እርም ነበሩ (ከኤር 31÷33-34 ጋር ያነ):: የመንግሥቱ ሁኔታ በአይአወ የተሞላ ነው:: ፊተኛው ያነሰ፤ ኋለኛው ደግሞ ፊተኛ ነው:: ራሱን ከፍ ከፍ የሚደርግ ይዋረዳል፤ ራሱን የሚያዋርድ ደግሞ ከፍ ከፍ ይላል (ከማቴ 18÷1-5፤ 20÷26፤ ከሉቃ 14÷11፤ 18÷14 ጋር ያነ)::

## ወዮ ቍጥር አንድ:- ሰዎች ወደ መንግሥተ ሰማይ እንዳይገቡ መመለስ

**ማቴ 23÷13**

[13]«እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ ምሁራንና ፈሪሳውያን፤ ሰዎች ወደ መንግሥተ ሰማይ እንዳይገቡ በሰዎች ላይ በሩን ስለምትዘጉባቸው ወዮላችሁ! እናንተ ራሳችሁ አትገቡም፤ መግባት የሚፈልጉትንም አታስገቡም::

*[13]ወዮ [14]እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን፤ ወዮላችሁ! የመበለቶችን ቤት እያራቆታችሁ፣ ለሰው ይምሰል ረዥም ጸሎት ስለምታደርጉ የከፋ ፍርድ ትቀበላላችሁ::**

**አንዳንድ ትርጒሞች ይህን ክፍል አይጨምሩም*

ኢየሱስ ፈሪሳውያንን «ግብዞች» በማለት ጠራቸው:: ይህ ከግሪክ ትያትር ቤት በቀጥታ የወጣ ብርቱ ቃል ነው:: አስመሳይ ወይም ግብዝ ቃል በቃል ሲተረጐም አንድ ተዋናይ ለትያትር ተመልካች ተውኔቱን ሊተውን ሳለ ሌላውን ሰው ለመምሰል ሲል ጭምብል ይለብሳል:: ይህ ዐይነቱ ንግግር በተለይ የግሪክን ቲያትር ጨምሮ ማንኛውንም ዐይነት የግሪክ ሥልጣኔ ለሚጠሉ ፈሪሳውያን አስጸያፊ ነው::[41] እንግዲህ ኢየሱስ ይጠራቸው የነበረው በዚያ በሚጠሉት ቃል ነው::

የኢየሱስ ተቃዋሚዎች ተነሣሡ:: በዚያ ጊዜ ፈሪሳውያን ይፈጽሙት የነበረው ኢየሱስ የተቃወማቸውን ነገር ነው:: በመካከላቸው የመንግሥተ ሰማይ ንጉሥ ቆሟል:: ፈሪሳውያን ኢየሱስን አለመቀበላቸው ብቻ ሳይሆን፣ ማንም እርሱን እንዳይቀበለው ለመከልከልም በቅናት ስሜት ጥረት አደረጉ (ማቴ 11÷19፤ 12÷23-24፤ 21÷15):: ተቃወሙት::[42] ወዳጆቹ መስለው የታዩትንና (ዮሐ

[41] ሄሮድስ አንቲጳስ በዋና ግቢው በሴፍሪስ የገነባው የግሪክ ቲያትር ቤት፣ ከኢየሱስ የትውልድ ቦታ ከአንድ ሰዓት ላነሰ ጊዜ ስለሚያስጉዝ፣ ኢየሱስ ይህን ትያትር ቤት ሳያውቀው አልቀረም:: በተጨማሪም ግብዞች ለሚለው የግሪክ ቃል በዕብራይስጥ ወይም በአራማይክ ቋንቋ ተተካካይ ቃል አለመኖሩ ኢየሱስ መጠነኛ የሆነ የግሪክ ቋንቋ ያውቅ እንደ ነበርና ተግሣጹን በመጠኑም ቢሆን አሳምሮ ለማቅረብ ይህን የባዕድ ቃል ማስገባቱን ያሳያል (ከ R.A. Batey, "Jesus and the Theater," *NTS* 30 [1984]: 463-574 ጋር ያነ)::

[42] የፈሪሳውያንን ተቃውሞ የሚያሳየውን ሙሉ ዝርዝር ሉቃ 11÷37 ውስጥ የቀረቡትንና የክፍል 107 ማስታወሻ ይመልከቱ::



7÷45-52) ከእነርሱ ጋር እኩል ደረጃ ያላቸውን አጋሮቻቸውንም አስፈራሩ:: የተከተሉትን ተራ ሰዎችንም አወገዙ (ዮሐ 9÷22:34-35):: ስለዚህ ብዙ ሰዎችን ከመንግሥተ ሰማይ አራቁ::

[40]«በረጅም ጸሎታቸው እያሳበቡ የመበለቶችን ቤት ያራቍታሉ፤ እነዚህ የባሰ ፍርድ ይቀበላሉ::» **ማር 12÷40**

አንዳንድ ፈሪሳውያን ሃይማኖታዊ ሥልጣናቸውን አዳዲስ አማኞችን ለመበከል ብቻ ሳይሆን፣ የመበለቶችን ሀብት ለማሟጠጥም ተጠቅመውበታል:: ይህ ለመበለቶች ለሰጡት የጸሎት «አገልግሎት» ክፍያ ሊሆን ይችላል:: ይበልጥ የሚመስለው ግን ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው ፈሪሳውያን የመበለቶችን ርስት[43] ጠባቂዎች በመሆን ለፈጸሙት አገልግሎት ክፍያ መሆኑ ነው:: እንደዚህ ያሉት ጠባቂዎች ለሕጋዊ ሽምግልና ጠቀም ያለ ገንዘብ ሊጠይቁ ይችላሉ፤ ከዚህም በላይ ለንብረቱ በሕጉ መሠረት ይከፈላቸው ዘንድ ለመጠየቅ ይችላሉ:: እርግጥ ለብልሹነት የተመቻቸ ነገር ነበር:: ታማኝነታቸውን ለመበለቶች ለማረጋገጥና «ለሥራቸው» ዋስትናን ለማትረፍ ሲባልም ረጅም መሐላና ጸሎት አገልግሎት ላይ ውለው ነበር::

**ወዮ ቍጥር ሁለት:- ወደ አይሁድ እምነት የገቡትን አሕዛብ ወደ ገሃነም መመለስ**

[15]«እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን፣ አንድን ሰው ወደ አይሁድ ሃይማኖት ለማስገባት በባሕርና በየብስ ስለምትንዙ፣ ባመነም ጊዜ **ማቴ 23÷15**

[43] J.D.M. Derrett የሚቀጥለውን ብርቱ ጉዳይ አድርጎ አቅርቦታል፤ "Eating up the Houses of Widows: Jesus's Comment on Lawyers?" *NovT* 14 (1972): 1-9.

ከእናንተ በእጥፍ የባሰ የገሃነም ልጅ ስለምታደርጉት
ወዮላችሁ::»

በመጀመሪያው ምእት ዓመት ከአሕዛብ ወገን የነበሩትን ወደ አይሁድ ሃይማኖት የሚመልሱ ፈሪሳውያን ሰባኪዎች እንደ ነበሩ በቂ ማስረጃ አለ (Carson, p. 478):: «ከቤት ቤት» የሚዘዋወሩ ወንጌላውያን ግን አልነበሩም:: ይልቁንም አንድ ጣዖት አምላኪ ይሁዲ የመሆን ዝንባሌ ሲያሳይ፣ ፈሪሳውያኑ ወደ እርሱ ይጣደፋሉ፤ የእነርሱ የሆነውን ሕግ አክራሪነት እንዲያከብርም ይከታተላሉ:: ብዙ ጊዜ እንደሚሆነውም ተማሪዎቻቸው ከመምህሮቻቸው ይልቅ ጽንፈኞችና ቀናተኞች ሆኑ:: ጴጥሮስና ጳውሎስም በመጀመሪያይቱ ምእተ ዓመት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይህን ዐይነቱን ክሥተት ተቃወሙ (ሐሥ 11÷1-3፤ 15÷1-2፤ 1ቆሮ 4÷6:9-10፤ ገላ 1÷7-8)::

## ወዮ ቍጥር ሦስት:- አታላይ መሐላዎች

**ማቴ 23÷16-22**

16«እናንተ ዕውር መሪዎች፣ ወዮላችሁ!
'ማንም በቤተ መቅደስ ቢምል ምንም አይደለም፤ ነገር
ግን በቤተ መቅደሱ ውስጥ ባለው ወርቅ ቢምል መሐላ
ይደርስበታል' ትላላችሁ:: 17እናንተ የታወራችሁ
ተላላዎች! ከወርቁና
ወርቁ ከቀደሰው ቤተ መቅደስ የቱ ይበልጣል? 18እንዲሁም፣ 'ማንም በመሠዊያው
ቢምል ምንም አይደለም፤ ነገር ግን በላዩ ላይ ባለው መባ ቢምል መሐላው
ይደርስበታል' ትላላችሁ፤ 19እናንተ ዕውሮች፣ ከመባውና መባውን ከቀደሰው መሠዊያ
የቱ ይበልጣል? 20ስለዚህ፣ በመሠዊያው የማለ፣ በመሠዊያውና በላዩ ላይ ባለው ሁሉ
ይምላል:: 21እንዲሁም በቤተ መቅደሱ የማለ፣ በቤተ መቅደሱና በውስጥ በሚያድረው
ይምላል:: 22በሰማይ የማለም በእግዚአብሔር ዙፋንና በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው
ይምላል::



እንደ እውነቱ ከሆነ መሐላ መሳ ለመሳ ይሆናል ብለህ በምታስበው ሊገባ ይችላል በማለት ፈሪሳውያን ደነገጉ (Gundry, p. 463):: በዚህ ዐይነት መንገድ አንድ ሰው ቢዋሽ የገንዘብ ኪሳራ ሊኖርበት ይችላል:: ስለዚህ በቤተ መቅደስ ወይም በመሠዊያው የተደረገ መሐላ ፋይዳ የለውም፤ ሆኖም በቤተ መቅደሱ ወርቅ ወይም በመሠዊያወ ላይ በቀረበው መባ የቀረበ መሐላ ፋይዳ አለው:: እንዲህ ያለው ጠጉር ስንጠቃ አነሣሽ መክንያት አታላይነት ነበር:: ስሕተት የሞላበት ምክንያታቸው «ሃይማኖትን» ተንተርሰው ሰዎችን ለመዝረፍ አበቃቸው::

ኢየሱስ የመሐላ ዐላማ የገንዘብ ዋስትና ሳይሆን ሐቅ ነው አለ:: ቃልህን የምትጠብቀው ገንዘብህን ልታጣ ስለምትችል ሳይሆን ከፍ ላለ ኀይል ብሎም በእግዚአብሔር ተጠያቂ ስለሆንክ ነው:: በመሆኑም የመሐላው አካል ከፍ ባለ ቍጥር መሐላውን ለመጠበቅ የላቀ ኀላፊነት ይኖራል:: ስለዚህ ለቤተ መቅደሱና ለመሠዊያው የተደረገ መሐላ ለቤተ መቅደሱ ወርቅ ወይም ለመሠዊያው መባ ከተደረገው መሐላ የላቀ ነው::

ኢየሱስ ጉዳዩን ከፍ አድርጎ ተመለከተው:: በቤተ መቅደሱ ወይም በመሠዊያው ስትምል ሁለቱንም የራሱ ባደረገ በእርሱ መማልህ ነው:: በመንግሥተ ሳማይ ወይም በዙፋኑ ብትምል በዚያ በሚኖረው መማልህ ነው:: ይህ ተጠየቅ ለምድር ሁሉና በላይዋ ላለው ሁሉ ሊታሰብ ይችላል:: ስለዚህ ማንኛውም መሐላ እኩል ይከበራል:: በዚህ የተነሣ ኢየሱስ በተራራው ስብከት ላይ ፈጽሞ መሐላ አትማሉ አለ (ማቴ 5÷33-37):: «ስለዚህ ስትነጋገሩ ቃላችሁ፣ አዎን ከሆነ፣ «አዎን» አይደለም ከሆነ «አይደለም» ይሁን፤ ከዚህ ውጭ የሆነ ሁሉ ከክፉው የሚመጣ ነውና:: ዋናው ጉዳይ የሐቅ ሰዎች መሆን አለብን:: የመሐላና የሐሳብ ስኬት ናፍቆት ወይም የረቀቀ ሕጋዊ ጽሑፍን

መሻት የውሸት አባት፣ ሰይጣን (ዮሐ 8÷44) በሕይወታችን ላይ ያለውን ተጽዕኖ ያጋልጣል።

## ወዮ ቍጥር አራት፡- አታላይ ዐሥራት

ማቴ 23÷23-24

[23]«እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን፣ ወዮላችሁ! ከአዝሙድ፣ ከእንስላልና ከከሙን ዐሥራት እየሰጣችሁ በሕጉ ውስጥ ዋና የሆኑትን ማለትም ፍትሕን፣ ምሕረትንና ታማኝነትን ግን ንቃችኋልና፤ እነዚያን ሳትተዉ እነዚህን ማድረግ በተገባችሁ ነበር፤ [24]እናንተ የታወራችሁ መሪዎች፤ ትንኝን አጥርታችሁ ትጥላላችሁ፤ ግመል ግን ትውጣላችሁ።»

ይህ ሉቃስ 11÷42 ውስጥ ኢየሱስ የተናረው ተጨማሪ ማብራሪያ ነው። ፈሪሳውያን ሃይማኖታዊ ግዳጃቸውን በመፈጸም ረገድ በእርግጥ ማራኪዎች ነበሩ። በጓሯቸው ከሚገኘው አትክልት፣ ከአዝሙድና ከእንስላል ሳይቀር ዐሥራት ይከፍሉ ነበር (ይህም ወደ መሣቂያነት የተቃረበ ነው)። ይሁን እንጂ ለጥቃቅኑ ነገር ሲጨነቁ ዋናውን ጉዳይ አጡት። እርግጥ ነው እግዚአብሔር ዐሥራት በመከፈሉ ይደሰታል፤ መከፈልም አለበት። ነገር ግን የፍትሐችንን፣ የምሕረታችንንና የታማኝነታችንን ያህል ዐቢይ ጉዳይ አይደለም። እነዚህ ሰዎች ይህን በእጅጉ ስተውታል።

ኢየሱስ በዚህ የታይታን ሥራ በሚገልጽ ምሳሌ ተቻቸው፡- ትንኝን አጥርታችሁ ትጥላላችሁ፤ ግመል ግን ትውጣላችሁ።» ሁለቱም ንጹሕ ያልሆኑ እንስሳት ናቸው። ማንም አንዳቸው ሾርባው ውስጥ እንዲኖሩ አይፈልግም። ከሁለቱ አንዱን ለመምረጥ ካሰብህ ግን ግመልን መምረጥ ይኖርብሃል። ሥጋው በቀላሉ ይታኘካል። ይህ በአማርኛ ቋንቋ አስቂኝ ነው፤ በአራማይክ ቋንቋ ግን የቃላት ጨዋታ



ይሆናል- (ግመል [ጋምላ - gamla] እና ትንኝ [ጋልማ - galma]) የሚለው ቃል ይበልጥ አስደሳች ያደርገዋል።

የዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ምሳሌ ልዩ ትኩረት መስጠት ይኖርባታል። በእግዚአብሔር ዐይን ትናንሽ የሆኑ ነገሮች በዓለም ውስጥ በእጅጉ ፈጠው የሚታዩ ናቸው (ልብስ፣ ዐሥራት መክፈል፣ በቤተ ክርስቲያን መገኘት ወዘተ)፤ ትላልቅ የሆኑት ነገሮች ግን ብዙ ጊዜ የሚከናወኑት በግል ነው (ፍትሕ፣ ምሕረትና ታማኝነት)። ጠንቃቆች ካልሆን የእግዚአበሔን ቀዳሚ ነገሮች ችላ ብለን ተገቢ ላልሆነ ተደራሲ የምንተውን እንሆናለን።

## ወዮ ቍጥር አምስት፡- ያልታጠቡ ውስጦች

ማቴ 23÷25-26

[25]«እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን፣ ወዮላችሁ! የጽዋውንና የወጭቱን ውጭ ትወለውላላችሁ፤ በውስጣቸው ግን ቅሚያና ስስት ሞልቶባቸዋል። [26]አንተ ዕውር ፈሪሳዊ! አስቀድመህ የጽዋውንና የወጭቱን ውስጥ አጽዳ፤ ከዚያም ውጩ የጸዳ ይሆናል።»

የዛሬ ክርስቲያኖች ከትላንቶቹ ፈሪሳውያን ብዙ የተለዩ አይደሉም። እግዚአብሔር በውስጥ ከሚያየው ይልቅ ሰዎች በውጭ ለሚያዩት ነገር እንጨነቃን። አነሣሽ ምክንያቶቻችንንና ምኞታችንን የሚወስነው የውስጥ ሕይወት ትኩረታችንን ይጠይቃል። በማኅበረ ሰብ ዘንድ ለሚጠበቅብን ልዩ ልዩ ጉዳይ ጭንቀት በተሞላበት ሁኔታ መልስ ስንሰጥ፣ የውስጥ ንጽሕና ይኖረን ዘንድ የሚሰማውን ጩኸት ችላ ማለት ቀላል ነገር ነው። አሁንም ዋናው ጉዳይ፣ «ቀዳሚ ተደራሲህ ማን ነው?» የሚለው ነው። ውስጥህን ለሚያየው

ለእግዚአብሔር በመሥራት ላይ ነህ? ወይስ የውጭውን ብቻ ለማየት ለሚችሉት ሰዎች (ለሃይማኖት ሰዎች እንኳ ሳይቀር) ትሠራለህ?

ኢየሱስ ውስጣዊ አነሣሽ ምክንያታቸውን ሲገልጽ ሥሥት የሞላበትና የግል ስሜትን የሚያረካ ነው ብሏል:: ይህ አንድን ስድ ሰው እንደ መግለጽ ሊሆን ይችላል:: «የሙያ ቀሳውስት/ካህናት» የሆን ሁሉ እነዚህ ፍላጎቶች ከሃይማት መሪዎች (አለቆች) ጋር በደንብ እንደሚገጣጠሙ እናውቃን:: ደኅና መስሎ የመታየትና በብጤዎች እንዲሁም በተከታዮች ዘንድ የመከበር ፍላጎት ነው:: እነዚህ ሃይማኖታዊ መሻቶች ቢሆኑም ጽድቅ የሚታይባቸው አይደሉም:: በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ለመሆን ወደ ውስጥ መግባት አለብን:: ልብ የሚነጻው በጸጉር አቈራረጥ፣ በክራባት ማማር፣ በአምልኮ ቦታ በመገኘ ት መጠን ወይም በማዕረጎች አይደለም:: መንጻት ከውስጥ ወደ ውጭ መሆን አለበት::

## ወዮ ቍጥር ስድስት:- የውጭውን በኖራ መለሰን

ማቴ 23፥27-28

[27]«እናንት ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን፤ ውጫቸውን በኖራ ተለስነው የሚያምሩ፣ ውስጣቸው ግን በሙታን ዐፅምና በብዙ ርኵሰት የተሞላ መቃብሮችን ስለምትመስሉ ወዮላችሁ! [28]እናንተም በውጭ ለሰዎች ጻድቃን ትመስላላችሁ፤ ውስጣችሁ ግን በግብዝነትና በክፋት የተሞላ ነው::»

በዚህ ጊዜ ኢየሱስ የመንጻትን ጉዳይ አንድ ደረጃ ከፍ አደረገው፤ መንጻት መጀመር ያለበት ከውስጥ ወደ ውጭ ብቻ አይደለም፤ መንጻት በቦታው ከሌለ አሳሳቢ ውጤቶች ይከተላሉና:: በውጭ ንፁህ በውስጥ ግን ብልሹ የሆኑ መሪዎች በተከታዮቻቸው ላይ ተላላፊ መዘዝ ያስከትላሉ::



ሬሳን የነካ ሰው ሁሉ ርኩስ መሆኑን ብሉይ ኪዳን ገልጾአል (ዘኍ 19፥16):: አይሁድ ይህን ወደ ሬሳ ሣጥንና ወደ መቃብር ሳይቀር አሻገሩት:: ስለዚህ ከፋሲካ አንድ ወር ቀደም ብሎ የተወሰኑ ቡድኖች በኢየሩሳሌም ዙሪያ ባሉት ቦታዎች ሁሉ በመሠማራት መቃብሮችን ሁሉ ኖራ ይቀቡ ጀመር፤ ምክንያቱ ንጹሓን መንፈሳዊ ተጓዦች ሳያውቁ መቃብር ረግጠው በፋሲካ በዓል ላይ ከመሳተፍ እንዳይገለሉ ነው:: ከሁለት ቀን ቀደም ብሎ ኢየሱስ ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ሲጓዝ አዲስ የተቀቡ መቃብሮችን አይቶ ይህንኑ ያስታውሳል:: በውበታቸው ትሳባላችሁ፤ እነርሱን በመንካት ግን ትረክሳላችሁ:: በፈሪሳውያን ላይ የሚሆነውም እንደዚሁ ነው::

ለአንድ ፈሪሳዊ የሬሳ ሣጥን ተብሎ ከመሰደብ የከፋ ነገር የለም:: የኢየሱስ ቃሎች ከባድ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ቢሆኑም ትክክል ናቸው:: ጠቅላላው የአይሁድ ሕዝብ በፈሪሳውያን ተማርኮ ነበር:: ቅዱሳት መጻሕፍትን በደንብ ያውቃሉ:: በሃይማኖት ሥርዐታቸውም ጥንቅቆች ነበሩ:: በልባቸው ግን ትዕቢተኛና ራስ ወዳድ ነበሩ:: ሰዎች ፈሪሳውያንን በተከተሉ መጠን የእነርሱም ቅደም ተከተል ተንጋደደ:: ወዳጆቻቸውን ለመውደድ ኀላፊነት ሳይሰማቸው ወይም ለተናቁትና ለጠፉት ምሕረት ሳያደርጉ ሥርዐት በመጠበቃቸው ብቻ ራሳቸውን አጸደቁ:: በዚህ ሁኔታ ፈሪሳውያንን «በመንካት» ረክሰው ነበር::

## ወዮ ቍጥር ሰባት:- ገዳይ ምኞቶች

ማቴ 23፥29-32

[29]«እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን፤ ወዮላችሁ! የነቢያትን መቃብር እየገነባችሁ፣ የጻድቃንንም ሐውልት እያስጌጣችሁ፣ [30]'በአባቶቻችን ዘመን ብንኖር ኖሮ፣ የነቢያትን ደም በማፍሰስ እንተባበራቸውም ነበር' ትላላችሁና:: [31]በዚህም የነቢያት ገዳዮች ለነበሩት አባቶቻችሁ ልጆች መሆናችሁን በራሳችሁ ላይ ትመሰክራላችሁ:: [32]እንግዲህ የአባቶቻችሁን ጅምር ተግባር ከፍጻሜ አድርሱ!»

ፈሪሳውያን ጥፋቶቻቸው ሁሉ ቢደመሩ በሚብስ ሁኔታ የነቢያት ሁሉ መደምደሚያ የሆነውን ኢየሱስን ለመግደል ፈለጉ:: አባቶቻቸው ነቢያትን በመግደላቸው ከነርሱ ጋር እንደማይስማሙ ይገልጻሉ:: የነቢያትን መቃብሮች በማስጌጥ ይህን ገልጸዋል:: ኢየሱስ ግን ይህ ሁሉ ማስጌጥ የአባቶቻቸው ሥራ ቀጣይነት እንጂ ተቃራኒ አይደለም ይላል::

[ቍ. 29-32 = ሉቃ 11÷47-48፤ የክፍል 107 ማስታወሻን ይመ]

ማቴ 23÷33-36

[33]«እናንተ እባቦች፤ የእፉኝት ልጆች! (ከ3÷7፤ 12÷34 ጋር ያነ) ከገሃነም ፍርድ እንዴት ልታመልጡ ትችላላችሁ? [34]ስለዚህ ነቢያትን፣ ጠቢባንንና መምህራንን እልክላችኋለሁ፤ ከነዚህም አንዳንዶቹን ትገድላላችሁ፤ ሌሎቹንም በምኵራቦቻችሁ ትገርፏቸዋላችሁ፤ ከከተማ ወደ ከተማ ታሳድዷቸዋላችሁ:: [35]ስለዚህ፣ ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በመቅደሱና በመሠዊያው መካከል እስከ ገደላችሁት እስከ በራኪዮ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ በምድር ላይ በፈሰሰው ንጹሕ ደም ሁሉ እናንተ ተጠያቂዎች ናችሁ:: [36]እውነት እላችኋለሁ፤ ይህ ሁሉ ነገር ሁሉ ይህ ትውልድ ይጠየቅበታል::»

እግዚአብሔር ኢየሱስን ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎች ነቢያትን፣ ጠቢባን ሰዎችን፣ መምህራንና ሐዋርያትንም ላከ (ሉቃ 11÷49):: እነዚህ ከኢየሱስ በፊት የነበሩ ሰማዕታት ብቻ ሳይሆኑ እርሱን የተከተሉትም ናቸው:: በሌላ አነጋገር ስለ እምነት የሞቱ ሁሉ ከኢየሱስ ሞት ጋር በመተባበር ሞቱ::

የነቢያት ቁንጮ የሆነው ኢየሱስ በሦስት ቀን ውስጥ ይገደላል:: ስለዚህ ይህ ትውልድ ከአቤል ጀምሮ እስከ ዘካርያስ ያሉትን ነቢያት ሁሉ በመግደል በደለኛ ይሆናል:: ዘካርያስ ማን እንደ ሆነ



በእርግጥ አናውቅም፤ ይሁን እንጂ ቢያንስ ሦስት ዕድሎች (አማራጮች) አሉ፤ (1) የባርክ ልጅ ዘካርያስ ሊሆን ይችላል:: በ67-68 ዓ.ም. በቤተ መቅደስ ግቢ ተገደለ (Josephus, *War* 4,334-344):: የቅዱሳት መጻሕፍትን አፈዎት (እስትንፋስ መንፈስ ቅዱስ) የሚቀበሉ ወይም የማቴዎስን ሐቀኝነት የሚቀበሉ ሁሉ ይህን አማራጭ መቀበል የለባቸውም፤ ለዚየሱስ ዘመን በጣም የዘገየ ነውና:: (2) የበራክዮ ልጅ ነቢዩ ዘካርያስ ሊሆን ይችላል (ዘካ 1÷1):: እዚህ ላይ ያለው ብቸኛ ችግር ድኅረ ክርስትና የሆኑ አንዳንድ አይሁዳዊ ማጣቀሻዎች ቢኖሩም እንኳ፣ ሞቱን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ማጣቀሻ የሌለ መሆኑ ነው:: ወይም (3) ካህኑ ዘካርያስ ሊሆን ይችላል (2ዜና 24÷20-25):: ማንነቱን አስመልክቶ ሁለት ችግሮች ይነሣሉ:: በመጀመሪያ ማቴዎስ እንደሚለው የዮዳሄ ልጅ እንጂ የበራክዮ ልጅ አይደለም:: ይሁን እንጂ «ልጅ» የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ «ትውልድ» ማለት ነው:: ስለዚህ ዘካርያስ የታወቀ ትውልድ ሐረግ ልጅ እንጂ፣ የገዛ አባቱ ልጅ ተብሎ ላይታወቅ ይችላል (ከካርሳን ገጽ 485-486 ጋር ያነ):: ሁለተኛው ችግር የዮዳሄ ልጅ ዘካርያስ የተገደለው መቅደሱ ውስጥ እንጂ በመሠዊያውና በመቅደሱ (ቍ. 35) መካከል ባለው አደባባይ አይደለም:: ሆኖም ይህ ከማቴዎስ ሐሳብ ጋር ቅርብ ሊሆን ይችላል:: ይህ ትክክለኛ ማጣቀሻ ከሆነ፣ ኢየሱስ የሚናገረው በዘመን ቅደም ተከተል ሳይሆን፣ በመጻሕፍት ቅደም ተከተል መሠረት ነው (በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቅደም ተከተል መሠረት ማለት ነው):: አቤል የመጀመሪያው የተገደለ ሰው ነበር (ዘፍ 4÷8-10):: በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቅደም ተከተል መሠረት ደግሞ ዘካርያስ የመጨረሻው የተገደለ ሰው ነበር::

ቍጥር 36 ውስጥ ኢየሱስ ተግሣጹን ከፈሪሳውያን ወደ ተከታዮቻቸው ማዞሩን ልብ ይበሉ:: ካስጠነቀቃቸው በኋላ አለቆቻቸውን ለመተው እምቢተኞች በመሆናቸው፣ እነርሱም ለኢየሱስ

ሞት ተጠያቂዎች ይሆናሉ:: የኢየሱስ መገደል በቅድስቲቱ ከተማ ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ያመጣል:: እርሱን ደስ ከማሰኘት በመራቁ፣ የኢየሩሳሌም ዕጣ ፈንታ ኢየሱስን አስለቀሰው::

**§ 137ለ**
**ኢየሱስ ስለ ኢየሩሳሌም አለቀሰ**
**(ማቴ 23÷37-39)**

ኢየሱስ ፈሪሳውያንን ክፉኛ በማጥቃት አይደሰትም (ማቴ 23):: ወይም በቅርብ ሊመጣ ባለው የኢየሩሌም ጥፋት ሐሤት አያደርግም:: የከተማዋ የወደፊት ዕድል ምን እንደ ሆነ በማየቱ ልቡ በሐዘን ተነክቷል፤ ዐይኖቹም በዕንባ ተሞልተዋል::

*ማቴ 23÷37-39*

37«አንቺ ነቢያትን የምትገድዪ፣ ወደ አንቺ የተላኩትንም በድንጋይ የምትወግሪ ኢየሩሳሌም ሆይ፤ አንቺ ኢየሩሳሌም! ዶሮ ጫጩቶችዋን በክንፎቿ ሥር እንደምትሰበስብ፣ ልጆችሽን ለመሰብሰብ ስንት ጊዜ ፈለግሁ! እናንተ ግን ፈቃደኛ አልሆናችሁም፤ 38እነሆ፤ ቤታችሁ ወና ሆኖ ይቀርላችኋል! 39እላችኋለሁና፤ 'በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው' እስከምትሉ ድረስ ዳግመኛ አታዩኝም::»

ይህ እይታ ኢየሱስ በፈሪሳውያን ላይና (ማቴ 23) በኢየሩሳሌም ከተማ ላይ በሰጠው ማስጠንቀቂያ (ማቴ 24) መካከል ድልድይ ነው:: በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ ያለውን፣ «የደብረ ዘይት ንግግር» እንድናነብ ያዘጋጀናል:: እዚህ ላይ እግዚአብሔር እንደ ተናገረው ሁሉ ኢየሱስም ተናገረ:: እስራኤልን በክንፉ ለመሰብሰብ ያለውን ፍላጎት፣ ብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር የተጠቀመበትን ምስያ ተጠቀመ (ዘዳ 32÷11፤ መዝ 17÷8፤ 36÷7፤ 91÷4፤ ኢሳ 31÷15)::

እነዚህ ቃሎች ከሦስት ወር ቀደም ብሎ ዮርዳኖስ ማዶ ከተናገራቸው ሉቃስ 13÷34-35 ውስጥ ካሉት ጋር አንድ ዐይነት ናቸው (በክፍል 113ለ ያለውን ማብራሪያ ይመ):: እዚህ ላይ ካለው እይታው ይልቅ ሉቃስ ወንጌል ውስጥ ካለው ትራኬ በተለየ መልኩ



የሚሠራ ቢሆንም እንኳ፣ የቃላቱ ትርጉም (ምንነት) በመሠረቱ አንድ ዐይነት ነው::

**§ 138**
**የመበለቲቱ ስጦታ**
**(ማር 12÷41-44፤ ሉቃ 21÷1-4)**

ኢየሱስ ይህችን ድኻ ሴት ስለ ታላቅ መሥዋዕቷ አመሰገናት:: ይህ ግልጽ ነው:: ነገር ግን እዚህ ላይ ዐይን ከሚያየው በላይ የላቀ ነገር ሊኖር ይችላል:: የማርቆስና የሉቃስ ዐውድ ፋይዳ አለው:: «የመበለቶችን ቤት» በማራቆታቸው ኢየሱስ ፈሪሳውያንን ነቅፎአል (ማር 12÷40፤ ሉቃ 20÷47):: በሚቀጥሉት ቁጥሮች ደግሞ ቤተ መቅደሱ እንደሚወድም ትንቢት ተናገረ:: ስለዚህ ይህ ምንባብ ከንቱ ሃይማኖት መበለቶችን የቱን ያህል ከንቱ እንደሚያስቀራቸው በደንብ ገልጦ ያሳያል::[44]

*ማር 12÷41-44 ከሉቃ 12÷1 ጋር*

41ኢየሱስ በገንዘብ ማስቀመጫው አንጻር ተቀምጦ ብዙ ሰዎች ስጦታቸውን ወደ ቤተ መቅደሱ ገንዘብ ማስቀመጫ ሣጥን ሲያስገቡ ይመለከት ነበር:: (ቀና ብሎ ሲመለከት[ሉቃ]) ብዙ ሀብታሞች ብዙ ገንዘብ አስገቡ:: 42አንዲት ምስኪን መበለት ግን ከአንድ ሳንቲም የማይበልጡ ሁለት የናስ ቤሳዎች አስገባች::

43ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ፣ እንዲህ አላቸው፤ «እውነት እላችኋለሁ፤ ይህቺ ድኻ መበለት ሣጥኑ ውስጥ ከጣሉት ከሌሎቹ የበለጠ አስገባች:: 44እነዚህ ሁሉ ከተረፈው ሀብታቸው ሰጡ፤ እርሷ ግን በድኽነት ዐቅሟ ያላትን ሁሉ አውጥታ ለመኖሪያ የሚሆናትን እንዳለ ሰጠች::»

[44] A.G. Wright, "The Widow's Mites: Praise or Lament? - A Matter of Context," *CBQ* 44 (1982): 256-265 & R.S. Sugirtharajah, "The Widow's Mites Revalued," *ExpT* 103 (1991): 42-43.

ኢየሱስ ለመጨረሻ ጊዜ የቤተ መቅደሱን አደባባይ ትቶ ሄደ:: የመለከት ቅርጽ ካላቸው፣ ከነሐስም ከተሠሩ 13 የዕቃ ማስቀመጫዎች ባሻገር በሴቶቹ አደባባይ ተቀመጠ:: እነዚህ ሣጥኖችም እያንዳንዳቸው ለልዩ ልዩ መባ ማስቀመጫነት የተዘጋጁ ሲሆኑ፣ ገንዘቡ ለምን ጉዳይ እንደሚውል የሚያሳይ ምልክት በላያቸው ላይ ተለጥፎ ነበር:: ሀብታሞቹ ጭብጥ ሙሉ ሳንቲም በኩራት ሲያስቀምጡ፣ ኢየሱስ ሆን ብሎ በጥንቃቄ ያስተውላቸው ነበር:: ከነሐስ የተሠራው ገንዘብ ሲቀመጥና ከማስቀመጫ ሣጥን ጋር ሲያቃጭል ሁለቱ ያስተጋባሉ፤ ከዚያም የታለመውን ትኩረት ይስባሉ::

በዚህ ትዕይንት መካከል አንዲት መስኪን መበለት መጣች:: እንዲያውም አነስተኛ በሆነው ስጦታዋ አፍራ ስለ ነበር ማንም ሳያያት ለመሄድ ሳትፈልግ አልቀረችም:: ሁለት የናስ ቤሳዎችን ስታስቀመጥ የሚሰማ ድምፅ አይኖርም:: ብዙ ጊዜ «ቤሳቢስቲ» የሚባለው «ቤሳ» (ሊፕታ - lepta[45])የሚለው ቃል «መላጥ» ከሚለው ቃል የተገኘ ነው:: የብረት ፍቅፋቂዎች ናቸው:: ከአንድ ላይ ተደምረው 1/64 የቀን ክፍያ ነበሩ:: እነርሱን መቍጠሩ ካላቸው ዋጋ በላይ ጭንቀት ይፈጥራል::

ኢየሱስ በመደነቅ ደቀ ዘማሙርቱን ጠራቸው:: ወደ እርሱ ሲጣደፉ ሳለ፣ ልዩ ነገር እናያለን ብለው ሳያስቡ አልቀሩም:: በዚያን ዕለት በተከናወኑት ታላላቅ ሁኔታዎች ውስጥ እነርሱ የሚደነቁበት በእጅጉ አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ ኢየሱስ ሳይዝላቸው አልቀረም:: ያ ሁሉ ግርግር ስለ ሁለት ቤሳዎች መሆኑን ሲገነዘቡ የቱን ያህል ይደነግጡ:: ለኢየሱስ ግን ትልቅ ነገር ነበር:: እርሱ ስጦታን የሚመዝነው በሚዛን ሳይሆን በልብ ሁኔታ ነው:: የሚያየው የገንዘቡን ልክ ሳይሆን

[45] ማርቆስ የቤሳን ዋጋ መገለጽ አስፈላጊ ሆኖ አገኘው፤ ይህን ያደረገውም በምዕራቡ ዓለም ብቻ የሚታወቀውን የላቲንን የሳንቲም መጠሪያ (ኳድራንስ - *quadrans*) በመጠቀም ነው፤ ይህም ማርቆስ ለሮማውያን አልጻፈም ለሚለው ተቃራኒ ሐሳብ መሆኑን ያመለክታል (Wessel, p. 741)::



የመሥዋዕቱን መጠን ነው:: ሰዎች ማየት የሚችሉት የተሰጠውን ስጦታ ብቻ ነው፤ እግዚአብሔር ግን ሳይሰጥ የቀረውን ያያል (2ቆሮ 8፥1-7:12):: ይህች ሴት ከሀብታሞቹ ይበልጥ ሰጥታለች፤ ያስቀረችው ነገር የለም::

በዚያ ዘመን ሰዎች ደሞዝ ይከፈላቸው የነበረው በየቀኑ ነው:: ስለዚህ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ለማቅረብ በዚያ ዕለት መጾም ነበረባት:: ነገር ግን መበለት መሆኗን በማጤን ያ ገንዘብ የዕለት ክፍያዋ ሳይሆን ያጠራቀመችው የመጨረሻ ገንዘብ ሊሆን ይችላል:: እንደ ሰራፕታዪቱ መበለት የቀራትን ትንሽ ነገር ለእግዚአብሔር አገልግሎት ሰጠች (1ነገ 17፥12-16)::

በቀሯት ሁለት ቤሳዎች የዕለት ምግቧን መግዛት አትችልም ነበር:: ስለዚህም ምናልባት፣ «ትልቅ ነገር ነው፤ መራቤ እንደ ሆነ አልቀረም:: የእግዚአብሔር ምሕረት ለእኔ ክብካቤ ያደርግ ዘንድ ሙሉ በሙሉ በእርሱ ከመታመኔ በፊት አንድ የመጨረሻ ምግብ ማግኘቴ ምን ለውጥ ያመጣል?» ይህም 1000.00 (አንድ ሺህ ብር) ከመስጠት ይልቅ ጥቂት ሳንቲሞች መስጠቱ ቀላል ነገር ሊሆን ይችላል:: ሆኖም በገንዘብ ጉዳያችን ረገድ ባለን እምነት፣ መምጣት ያለብን ወደዚሁ ቦታ ነው:: በሳንቲሞቻችን በእግዚአብሔር የማንታመንበት ከሆነ፣ በከፍተኛ ገቢያችን ላይ ሥልጣን ይኖረዋል ማለቱ የማይመስል ነገር ነው::

# ምድብ ዐሥራ አንድ
# ለክርስቶስ ሞት የሚደረግ ዝግጅት
# የደብረ ዘይት ንግግር

**§ 139ሀ**
**ዳራውን መዘርጋት**
**(ማቴ 24፥1-3፤ ማር 13፥1-4፤ ሉቃ 21፥5-7**

በዚህ ክፍል ኢየሱስ ሁለት ሁኔታዎችን ይገልጻል:- የኢየሩሳሌም መፈራረስ (በ70 ዓ.ም.) እና ዳግም ምጽአቱ:: በምዕራፉ ግማሽ አካባቢ በእነዚህ ሁለት ሁኔታዎች መካከል መሥመር ማድረግ አለብን:: ይሁን እንጂ ይህ የሚነገረውን ያህል በቀላሉ የሚተገበር አይደለም:: የየራሳቸውን መሥመር በዘረጉት አያሌ ሊቃውንት መካከል ላይ እንኳን ግዙፍ ልዩነት ነበር:: ይህ ቀላል ተግባር የከበደበት አንዳንድ ምክንያቶች አሉ::

በመጀመሪያ ደረጃ አሁን ልናነባቸው የተዘጋጀንባቸው አንዳንድ ጽሑፎች የኢየሩሳሌምን መጥፋትና ዳግም ምጽአት በቀላሉ ሊገልጹ ይችላሉ:: ይህ ደግሞ በትንቢት የተለመደ ነው (ለምሳሌ ኢሳ 7፥14፤ ኤር 31፥15፤ ሚክ 5፥2):: የመጀመሪያው «ፍጻሜ» ወደፊት እውን የሚሆነውን ታላቅ ፍጻሜ ሊያሳይ ወይም ሊያለክት ይችላል:: ስለዚህ «የአሁን ግን የገና» የሚለው እሳቤ እውስጡ አለ:: በተመሳሳይ መንገድም ማቴዎስ ምዕራፍ 24 ውስጥ የኢየሩሳሌምን መጥፋት ለመግለጽ አገልግሎት ላይ የዋሉት ቃላቶች በመጨረሻ (ዞሮ ዞሮ) ዳግም ምጽአትን ሊገልጹ ይችላሉ (ቍ. 23-81):: ለምሳሌ በ70 ዓ.ም. ኢየሩሳሌም ያለፈችባቸው ችግሮች «በዘመኑ መጨረሻ» ወደ ዓለም ዐቀፋዊ ደረጃ ከፍ ሊል ይችላል:: እንዲያውም ማቴዎስ ከኢየሩሳሌም መጥፋት ጋር ያዛመደውን (ማቴ 24፥17-20) ሉቃስ ምስል አድርጎ



በማየት በተለየ ዐውድ ላይ ከዳግም ምጽአቱ ጋር ያዛምደዋል (ሉቃ 17፥31)::[1]

ሁለተኛ ትንቢት ብዙ ጊዜ ከምጽአቱ ጋር የሚፈጸመው ተምሳታዊ በሆነ መልኩ ነው:: እነዚህን ነገሮች ተምሳሌታዊ በሆነ መንገድ ለመተርጐም ኀፍረት ይሰማናል:: «ታማኝነታችንን» ያጓደልን ይመስለናል:: ተምሳሌት እንዲሆን የታቀደውን ቃል በቃል ብንተረጕመው ግን የምንባቡን ትክክለኛ መልእክት ሳናገኘው እንቀራለን (ከዮሐ 2፥19-21፥19-21፤ 3፥3-4፤ 6፥51-52፤ 11፥11-12 ወዘተ ጋር ያነ):: በተጨማሪም ይህ ምንባብ የጊዜንና የሁኔታን ቅደም ተከተል ጠብቆ ይጓዛል ብለን እናስባለን፤ ነገር ግን እንዲያ ላይሆን ይችላል:: አንዳንዶች ኢየሱስ የኢየሩሳሌምን መጥፋትና (መውደምና) ዳግም ምጽእትን አቀናጅቶ በመናገር ወደፊትም ወደኋላም ተመልሷል በማለት ሐሳብ አቅርበዋል::

ሦስተኛ ይህ አቡቀለምሲሳዊ ጽሑፍ ነው:: ንረታዊ (የናረ) ትንቢት ተብሎ ሊጠራ ይችላል (እንደ ዳንኤልና እንደ ዮሐንስ ራእይ):: ብዙው ጕዳይ ቃል በቃል የሚታይ ሳይሆን፣ በትንቢታዊ ምስያና ቃል የተሞላ ነው:: በ4ኛው ክፍለ ዘመን ላለነው እንግዳ ነገር ቢሆንብንም እንኳ፣ አቡቀለምሲሳዊ ጽሑፍ በመጀመሪያው ምእት ዓመት እንግዳ ነገር አልነበረም::[2] ያም ሆኖ ሊተረጕሙት የሚያስቸግር የጽሑፍ ዘር (ወገን) ነበር:: የችግሩ አንድ ክፍል የብርቱ ምክርን ያህል ይህኛው

---

[1] ማቴዎስ 24፥4-22 በቀዳሚነት የሚያመለክተው 70 ዓ.ምን. መሆኑን የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ እምነት ነው:: ማቴዎስ 24፥23-31፣ 70 ዓመተ ምሕረትንና ዳግም ምጽአትን በማመልከት መንትያ አመላካችነት አለው:: ከማቴ 24፥36 በኋላ ያለው ክፍል ግን ሙሉ በሙሉ የሚመለከተው የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ነው::

[2] B.S. Easton, "The Little Apocalypse," *BW* 40 (1912): 130-138 ቢ.ኤስ. ኢስቶን የተባለ ጸሐፊ፣ ምንባቡ ውስጥ «አዲስ ነገር የለም፤ እያንዳንዱ ምስያም ከአቡቀለምሲሳዊ ጽሑፍ ጋር ሙሉ በሙሉ ጕድኝት ሆኖ ሊታይ ይችላል» ብሏል::

ማብራሪያ ይሰጥበት ዘንድ አለመታቀዱ ነው:: አቡቀለምሲሳዊ ጽሑፍ ሥነ ፍጻሜያዊ ቅደም ተከተልን[3] ለመግለጽ አልታለመም ነበር:: የታለመው በሥቃይ ላይ የሚገኙትን ቅዱሳን እስከ መጨረሻው ታማኞች ሆነው እንዲጸኑ ለማበረታታት ነው::

አራተኛው ይህን ምንባብ የምናቀርብበት ሺህ ዓመታዊ ሥርዐት «መሥመሩን የት ላይ እንደምናሠምረው» ይወስነዋል:: አንዳንዶች ሺህ ዓመታዊ አመለካከትን የኛ አላደረግነውም ማለት ይችላሉ (ይኸውም ቅድመ፣ ወይም ድኅረ) ነው:: ይሁን እንጂ ሁሉም ሰው ለማለት ይቻላል፣ ልብ ይበለውም አይበለው ስለ ሥነ ፍጻሜና ስለ ትንቢታዊ ጽሑፍ ቅድመ እሳቤ (Presuppositions) አለው:: እነዚህ ሁሉ በ70 ዓ.ም. እና በጌታ ዳግም ምጽአት መካከል የት ላይ መሥመሩን ማስመር እንደሚኖርብን በሐሳባችን ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ:: መሥመሩን የት ላይ ማሥመር እንዳለብን በምናደርገው ውሳኔ ላይም ከፊል ተጽዕኖ አላቸው::

ማቴ 24÷1-3
ከማር 13÷1-3፤
ከሉቃ 21÷5-6
ጋር

1ኢየሱስ ከቤተ መቅደስ ወጥቶ ሲሄድ፣ ደቀ መዛሙርቱ የቤተ መቅደሱን ሕንጻ ሊያሳዩት ወደ እርሱ ቀረቡ:: («መምህር ሆይ፤ ድንጋዮች እንዴት እንደ ሆኑ፣ ሕንጻውም እንዴት ውብ እንደ ሆነ እይ»[ማር]) (በውብ ድንጋዮችና በስእለት ስጦታዎች እንዳማረ፣[ሉቃ]) 2እርሱ ግን፣ «ይህን ሁሉ ታያላችሁ? እውነት እላችኋለሁ (የማይቀርበት ጊዜ ይመጣል[ሉቃ])፤ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ተከቦ የምታዩት፣ ሳይፈርስ እንዲሁ እንዳለ የሚቀር አንድ ድንጋይ እንኳ አይኖርም» አላቸው::

3በደብረ ዘይት ተራራ ተቀምጦ ሳለ፣ (ከቤተ መቅደሱ ትትዩ፣ ... ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ ዮሐንስና እንድርያስ[ማር]) ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው፣ «እስቲ ንገረን፤ የምትለው ሁሉ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክትስ ምንድን ነው?» አሉት::

ለደቀ መዛሙርቱ ቤተ መቅደሱ ውስጥ መሆን ጥሩ ቀን ነበር:: ጌታቸው የቀረበለትን ጥያቄ ሁሉ መልሷል:: የአይሁድ አለቆችንም ባቀረበው ጥያቄ ጸጥ አሰኝቷቸዋል:: ከዚያም ኢየሱስ ፈሪሳውያንን ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ይብስ አወገዛቸው (ማቴ 23):: ጊዜው ለአዳር ወደ ቢታንያ የሚመለሱበት ወቅት ነበር::

ደቀ መዛሙርቱ በእጅጉ ደስ ብሏቸዋል:: ዕለቱ ወሳኝ የሆነ የኢየሱስ የድል ቀን ነበር፤ ለእነርሱም እንዲሁ:: ከቤተ መቅደሱ ሲወጡ አንድ ሰው በመልካም መዐዛ ደስ እንደሚሰኝ ሁሉ፣ እነርሱም በወቅቱ ሐሤት አድረገው ነበር:: በእርግጥ ታላቅ ቀን ነበር:: በተለይ የቤተ መቅደሱን ታላቅነት ልብ አሉ:: ማን እንደሚኖርበት እንጂ ፈራሽ ስለ መሆኑ አላሰቡም:: ምናልባትም፣ ኢየሱስ መንግሥቱን ለመመሥረቻነት የቤተ መቅደሱን ሕንጻ ለመውሰድ ተቃርቧል በማለት አስበው ይሆናል:: ስለ ግል ቢሮአቸው መጠንም ሳያሰላስሉ አልቀሩም:: የአዲሱ መንግሥት ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች እነርሱ ናቸውና::

ቤተ መቅደሱ ማራኪ ነበር (Josephus *Ant* 15. 391-402; *Wars* 5, 184-227; Tacitus *Histories,* 5.8.12):: ታላቁ ሄሮድስ ቤተ መቅደሱን ማደስ የጀመረው በ19 ዓ.ቅ.ክ. ነው:: እስከ 60 ዓ.ም. ድረስ ሥራው ገና አይጠናቀቅም ነበር:: ቢሆንም ባለበት ደረጃ ደህና ሁኔታ ላይ ነው ያለው፤ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታም ጌጥ በጌጥ ሆኗል::

[3] ማቴዎስ ምዕራፍ 24 ውስጥ በተከታታይነት «በዚያን ጊዜ» የሚለውን ሐረግ እናገኛለን:: ይህም በአቡቀለምሲሳዊ ጽሑፍ ውስጥ በላላ መልኩ የጊዜንና የሁኔታን ቅደም ተከተል አመልካች ነው፤ «ከዚህ በኋላ» ወይም «በተከታታይ ሁኔታዎች ውስጥ ቀጥሎ ያለው» ወይም ደግሞ እንዲሁ «ስለዚህ» (ከጊዜና ከሁኔታ ቅደም ተከተል ይልቅ ተጠያቂ ቅደም ተከተል ነው) ማለት ሊሆን ይችላል::

ኢየሱስ አስደንጋጭ ነገር ሰነዘረባቸው፤ «ይህን ሕንጻ ታዩታላችሁን? ይፈርሳል!» አለ። ከዚያም ተጨማሪ ማብራሪያ ሳይሰጥ፣ ከቄድሮን ሸለቆ ባሻገር፣ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ በሚገኘውና የቤተ መቅደሱን ኮረብታ አሻግሮ በሚያየው በደብረ ዘይት ተራራ[4] ፊት ለፊት ባለው ምሥራቅ በር ወጣና ተቀመጠ። ግራ የተጋቡት ደቀ መዛሙርት ተከትለውታል። ማርቆስ እንደሚለው ጥያቄዎቹን የጠየቁት ጴጥሮስ፣ እንድርያስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ ቢሆኑም፤ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርትም በጥያቄዎቹ ላይ ሳይተባበሩ አልቀሩምና የኢየሱስን መልስ ለመስማት ጓግተው ነበር።

ሦስት ጥያቄዎችን ነው ደቀ መዛሙርቱ የጠየቁት:- (1) ቤተ መቅደሱ የሚፈርሰው መቼ ነው? (2) የመምጫህ (የምጻትህ) ምልክት ምንድን ነው? (3) የዘመኑስ ፍጻሜ ምልክት ምንድን ነው? እነዚህ ሦስቱ ነገሮች በአእምሯቸው በአንድ ጊዜ ይከሠታሉ። «ከዘመኑ ፍጻሜ በፊት» የቤተ መቅደሱን መፍረስ ማሰብ አይችሉም። ከእኛ እይታ አኳያ ቢያንስ ሁለት ጉልሕ ሁኔታዎችን ለማየት እንችላለን:- (1) የኢየሩሳሌም መፈራረስ እና (2) ዳግም ምጽአት። ኢየሱስ ሁለቱን ሁኔታዎች በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ ይገልጻል። አለመታደል ሆነና ደቀ መዛሙርቱ በጥያቄዎቻቸው እንዳደረጉት ሁሉ፣ ኢየሱስም በሚሰጠው መልስ ላይ በሁለቱ መካከል የሚያደርገው ልዩነት መጠነኛ ይሆናል። ድርጊቱ ይህን ምንባብ ለማብራራት ጥረት በሚደረግበት ጊዜ ከፍተኛ ችግርን አስከትሏል።

**§ 139ለ**
**የምጥ ጣር**
**(ማቴ 24፥4-14፤ ማር 13፥5-13፤ ሉቃ 21፥8-19)**

እነዚህ ቍጥሮች ብዙ ጊዜ የኢየሱስን ዳግም ምጽአት ያመለክታሉ ተብለው ይታሰባሉ። ለ70 ዓ.ም. የሚታሰብ ከሆነ፣ እንደ ተባለው ከዳግም ምጽአቱ ጋር መያያዝ አለባቸው።

[4] ስለዚህ ንግግሩ፣ «የደብረ ዘይት ንግግር» ተባለ። ይህ ተራራ ለደቀ መዛሙርቱ ሥነ ፍጻሜያዊ ቃና አለው (ከዘካ 14፥4 ጋር ያነ)።



እንደሚታወቀው ኢየሱስ የመጀመሪያውን ጥያቄ በአመጣጡ ቅደም ተከተል መሠረት በመጀመሪያ ይመልሳል ተብሎ ይታሰባል፤ ይኸውም ስለ ቤተ መቅደሱ ነው። ይበልጥ ዋና ጉዳይ የሆነው ደግሞ ቍጥር 16 ውስጥ የተጻፈው ቃል ደቀ መዛሙርቱ ወደ ይሁዳ ኮረብታዎች (ተራሮች) እንዲሸሹ ማደፋፈሩ ነው። ይህ የኢየሱስን ዳግም ምጽአት አያመለክትም። ኢየሱስ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ መሸሹ ጥቅም የለውም፤ ደቀ መዛሙርቱ በእርግጥ ይህን አይፈልጉም።

**ማቴ 24፥4-8**
**ከሉቃ 21፥8-11**
**ጋር**

4ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ «ማንም
እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤ 5ብዙዎች፣ 'እኔ ክርስቶስ[መ]
ነኝ' በማለት በስሜ ይመጣሉና ('ጊዜው ቀርቦአል'[ሉቃ])
ብዙዎችንም ያስታሉ። (እነርሱን አትከተሏቸው[ሉቃ]) 6ስለ ጦርነትና ጦርነትን የሚያናፍስ
ወሬ ትሰማላችሁ፤ እነዚህ ነገሮች (አስቀድሞ[ሉቃ]) የግድ መፈጸም አለባቸው፤ ሆኖም
መጨረሻው ገና ስለ ሆነ በዚህ እንዳትደናገጡ ተጠንቀቁ። 7ሕዝብ በሕዝብ ላይ፣
መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣል፤ በተለያየ ስፍራም ራብና የመሬት
መንቀጥቀጥ (ራብና ቸነፈር፣ እንዲሁም ከሰማይ ምልክት[ሉቃ]) ይሆናል። 8ይህም ሁሉ
ግን የምጥ መጀመሪያ ነው።

*[መ]5 ወይም መሲሕ፤ ቍ 23 ይመ*

የኢየሩሳሌምን መውደም የሚያመለክቱ የተወሰኑ ምልክቶች ነበሩ። ኢየሱስ «የምጥ መጀመሪያ» በማለት ይጠራቸዋል። የሚያስከትሉት መከራ የማይቻል ሥቃይ ስለ አለው አገላለጹ ትክክል ነው። አንድ ከባድ ነገር በመምጣት ላይ መሆኑን ያመላክታሉ፤ ገና በሩቅ ሳሉ አጠገባችን ላይ እንደ ደረሱ አድርገን እንድናስብ ያደርጉናል። ኢየሱስ በተለይ ሦስት የምጥ መጀመሪያዎችን ያመለክታል። ሐሰተኛ ክርስቶሶች ጦርነትና የጦርነት ሽብር።

የተፈጥሮ ጥፋትና በሽታዎች ሦስቱም ከ30-70 ዓ.ም. ባለው ዘመን ውስጥ ሊታዩ (ሊታሰቡ) ይችላሉ::

***ሐሰተኛ ክርስቶሶች:-*** ይህ ዘመን ከሐሰተኛ መሲሖች ጋር ሁከት የተካሄደበት ወቅት እንደ ነበር ኢዮሳፍስ ይመሰክራል (*Wars* 2:259-264):: የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንኳ ጥቂቱን ይዘረዝራል:: ቴዎዳስና ይሁዳ (5÷36-37)፣ አንድ ግብፃዊ (21÷38) ምናልባትም በርያሱስ (13÷6-8) እና ሲሞን (ከ8÷9 ጋር ያነ):: ብዙዎቹ መሲሕ ነን ባዮች በወቅቱ የተከሠተውን የማኅበራዊና የፖለቲካዊ አለመረጋጋት እንደ አመች ሁኔታ በመጠቀም አያሌዎችን ማታለላቸው አያጠያይቅም::

***ጦርነትና ጦርነትን የሚያናፍስ ወሬ:-*** በዚህ ዘመን አይሁድ በሦስት ልዩ ልዩ ነገሥታት ምክንያት ሥጋት ውስጥ ገብተው ነበር:- ካሊጉላ፣ ቅላውዲያና እና ኔሮን (ኔሮ) (Meserve, p. 23):: ለአይሁድ ሕዝብ ይበልጥኑ አሥጊ ሁኔታ የነበረው ግን ውስጣዊው መከፋፈል ሲሆን፣ በሕዝቡ መካከል የእርስ በርስ ጦርነት አስከትሏል::

***ራብና የመሬት መንቀጥቀጥ:-*** በቀላውዴዎስ ዘመን (በ44 ዓ.ም.) በሐዋርያት ሥራ 11÷28 ላይ በአጋቦስ የተተነበየውን ጨምሮ በሰነድ ላይ የሰፈሩ አያሌ የመሬት መንቀጥቀጦችና ርሀብ ነበሩ:: ሌሎች 46ን ወይም 47፣ 51፤፣ 60፣ 62 ወይም 63ን ይጨምራሉ (Meserve, p. 25)::

«አስፈሪ ነገር እንዲሁም ከሰማይ ታላቅ ምልክት» የሚለው የሉቃስ አገላለጽ ቀደም ያሉትን ሦስት የምጥ መጀመሪያዎች እጥር ባለ መልክ በማቅረብ ነቢያዊ ቃልን የሚወክል ሊሆን ችሏል:: ይህም ሆኖ ከእነዚህ አንዳቸውም መጨረሻው አይቀሬ መሆኑን አያመለክቱም:: የሚያመለክቱት የከፋ (የላቀ ሥቃይ) የሚመጣ መሆኑን ብቻ ነው::



*ሉቃ 21÷12-18*
*ከማር 13÷9-11*
*ከማቴ 24÷9*
*ጋር*

(ስራሳችሁ ተጠንቀቁ[ማር]) «ይህ ሁሉ ከመሆኑ
በፊት ግን ሰዎች ይይዟችኋል፤ ያሳድዷችኋል
(ይገድሏችኋል[ማቴ]) (በምኩራብ ይገርፏችኋል ምስክር
ትሆኑን ዘንድ[ማር])፤ በነገሥታትና በገዥዎች ፊት
ያቀርቧችኋል:: ይህም ሁሉ በስሜ ምክንያት
ይደርስባችኋል:: [13]ይህም ስመመስከር ጥሩ ዕድል ይሆንላችኋል:: [14]ስለዚህ ምን
መልስ እንሰጣለን በማለት አስቀድማችሁ እንዳትጨነቁ ይህን ልብ በሉ፤
[15]ተቃዋሚዎቻችሁ ሁሉ ሊቋቋሙትና ሊያስተባብሉት የማይችሉትን ቃልና ጥበብ
እሰጣችኋለሁና:: (የሚናገረው መንፈስ ቅዱስ እንጂ እናንተ አይደላችሁምና::[ማር])
[16]ወላጆቻችሁ፣ ወንድሞቻችሁ፣ ዘመዶቻችሁና ጓደኞቻችሁ እንኳ ሳይቀሩ አሳልፈው
ይሰጡአችኋል፤ ከእናንተም አንዳንዶቹን ይገድላሉ፤ [17]ስለ ስሜም በሰዎች (በሕዝብ
ሁሉ[ማቴ]) ዘንድ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ:: [18]ነገር ግን ከራሳችሁ ጠጉር አንዷ
አትጠፋም፤»

[*ቍ 12-18 = ማቴ 10÷17-22*፤ በክፍል 70 ላይ *ያለውን ማብራሪያ ይመ*]

ማርቆስና ሉቃስ ይህን ምንባብ ከደብረ ዘይት ንግግር ጋር ማጣመራቸው ተገቢ ነው:: ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ እነዚህን ቃሎች ሲናገር ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት «ብቻቸውን» ለመጀመሪያ ጊዜ በመላክ ላይ ነበር:: ሆኖም በሐዋርያቱ የመጀመሪያ ጉዞ ከእነዚህ ነገሮች አንዳቸውም አልተከሠቱም:: ስለዚህ ኢየሱስ ስለ ወደፊት ሁኔታዎች ትንቢት በመናገር ላይ መሆኑን እናውቃለን:: ብዙዎቹም በሐዋርያት ሥራ ተዘርዝረዋል:: እንግዲህ እነዚህ ቃሎች ማቴዎስ ምዕራፍ 10 ውስጥ ካለው ይበልጥ ተተግባሪ ሆነው ባይገኙም እዚህ ላይ ግን ተገባሪዎች ናቸው::

ማቴ 24÷10-14
ከሉቃ 21÷19
ጋር

10«በዚያን ጊዜ ብዙዎች ይሰናከላሉ፤ እርስ
በርስ አሳልፈው ይሰጣጣሉ፤ ይጣላሉም:: 11ብዙዎች
ሐሰተኛ ነቢያት ይነሣሉ፤ ብዙዎችን ያስታሉ:: 12ክፋት
ስለሚገን የብዙ ሰዎች ፍቅር ይቀዘቅዛል:: 13እስከ
መጨረሻው የሚጸና ግን እርሱ ይድናል (ነፍሳችሁን
ታተርፋላችሁ::[ሉቃ])
14ለሕዝብ ሁሉ ምስክር እንዲሆን፣ ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓም ሁሉ ይሰበካል፤
ከዚያም መጨረሻው ይመጣል::»

ከዚህ ላይ ከኢየሩሳሌም መውደም በፊት የሚመጡ ሦስት ተጨማሪ ምልክቶች ይገኛሉ:- ስደት፣ የሐሰት ትምህርቶች፣ «በዐለም ሁሉ» ወንጌል መሰበኩ:: እነዚህም የሚመጣውን ፍርድ ከመተንበይ በቀር ሌላ ፋይዳ አልነበራቸውም::

*ስደት:-* የሐዋርያት ሥራ ሲቪላዊና የተቀናጁ ስደቶችን (7÷54-60፤ 8÷1-9÷2፤ 23) አካባቢያዊና ዐልፎ ዐልፎ የሚከሠት ስደትን (13÷50-51፤ 14÷18-19፤ 16÷19-23፤ 17÷5-10፤ 19÷23-41) በሚገባ ዘግቧል:: ታሲተስ የተባለ ጸሐፊ ክርስቲያኖችን «በርኩሰታቸው የተጠሉ ወገኖች» ብሎ ሲገልጽ፣ ለሮማዊው ዓለም ባብዛኛው በመናገር ላይ ነበር (Annals, 15.44):: በ64-68 ዓ.ም. ኔሮ በቤተ ክርስቲያን ላይ[5] የመጀመሪያውን ሮማዊ ስደት ተገበረ::

*የሐሰት ትምህርቶች (ኑፋቄዎች):-* ከሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 ጀምሮ እስከ 1ዮሐንስ ድረስ ቤተ ክርስቲያን የሐሰት ትምህርቶችን አዘውትራ መዋጋት ነበረባት:: ገላትያ፣ ቈላስይስ፣ 2ቆሮንቶስ፣ 2ጢሞቴዎስ፣ 2ጴጥሮስ፣ 1ዮሐንስና ይሁዳ የተጻፉት በመጀመሪያዋ ... ክርስቲያን ተስፋፍቶ የነበረውን የሐሰት አስተምህሮ ለመዋጋት

[5] በመጀመሪያው ምእት ዓመት በክርስቲያኖች ላይ ስለ ደረሰው ስደትና ከፍተኛ ጥላቻ ሰፋ ያለውን ዝርዝር ለማስተዋል W. Barclay, "Great Themes of the NT: VI Matthew 24", *ExpT* 70 (1959): 327-328 ይመልከቱ::



ነበር:: ከኢየሩሳሌም መፈራረስ ወዲህ ዮሐንስ፣ የሐሰት ሐዋርያትን (2÷2)፣ የሰይጣንን ምኩራብ (2÷9:13፤ 3÷9)፣ ኒቆላውያንን (2÷6:15)፣ የበለዓምን ትምህርትና (2÷14) የኤልዛቤልን ትምህርት (2÷20) በመቃወም የዮሐንስ ራእይን ከጻፈ በኋላ እንኳ የተሻለ ነገር አልነበረም::

***«በዓለም ሁሉ» ወንጌልን መስበክ:-*** የኢየሩሳሌምን መውደም ሳይሆን የኢየሱስን ዳግም ምጽአት ማመልከት አለበት የሚለውን ሐሳብ ለማረጋገጥ ይህ ክፍል ብዙ ጊዜ ይጠቀሳል (ለምሳሌ ባርክሌይ፣ ገጽ 336፤ ዋልቨርድ፣ ገጽ 183):: አርሜርዲግም የተባለ ሰው «የኢየሱስ ዳግም ምጽአት አይቀሬ ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም ወንጌል ሙሉ በሙሉ አልተሰበከም» ይላል::[6] ተመሳሳዩን ተጠየቅ በመጠቀም ሄንድሪክሰን የተባለው ተከራካሪ ተቃራኒ ሐተታ ሲያቀርብ እንዲህም ይላል፤ «ከመጀመሪያው ዘመን አንሥቶ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ያለው የተልእኮዎች እድገት አጭር ደሳሳ (ቅኝት) ወደ መጨረሻው እየተቃረብን ስለ መሆናችን ማንንም ያሳምናል::[7]

ይሁን እንጂ «በዓለም ሁሉ» የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ሰው የሚኖርበትን ዓለም ነው (ከማቴ 4÷23፤ 9÷35፤ ከሉቃ 2÷1 ያነ፤ Josephus, *Ant* 15:387; 19.193) ይህ እኛ ከምናስበው በጣም የተለየ ነው:: በዚህ ላይ ደቡብ አሜሪካና ሀዋይን፣ ሩስያን፣ ጃፓንን ወዘተ እናካትታለን:: *ኦይኳዎሜኔ* የሚለው ቃል እነዚህን ሁሉ አያሳይም:: የቃሉ ትርጉም በመሠረቱ ከሮም ግዛት ጋር አቻ ለአቻ ነበር:: በሌላ አነጋገር ኢየሱስ ማነኛውም የመጨረሻ ሰው ወንጌልን ይሰማል አላለም፤ ያለው ወንጌል ለሚታወቀው ሀገር (ሕዝብ) ሁሉ ይዳረሳል

[6] C.E. Armerding, *Dreams, Visions & Oracles* (Grand Rapids: Baker, 1977), p. 169.

[7] W. Hendriksen, *Lectures on the Last Things* (Grand Rapids: Baker, 1951) p. 19.

ነው:: ዋናው ጉዳይ የሚከተለው ነው:- ጳውሎስ ወንጌል ለአይኳዋሜኔ ሁሉ ደርሷል ይላል (ሮሜ 1÷8፤ 10÷18፤ 16÷26፤ ቈላ 1÷6:23፤ 1ተሰ 1÷8):: ስለዚህ ይህ ትንቢት ከ70 ዓ.ም. በፊት ተፈጽሟል ቢባል ትክክል ነው::

ይህ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ከሚመጣው የምድር ሁሉ መጥፋት ጋር ሲነጻጸር የ70 ዓመተ ምሕረቱ ጥፋት ግምት ውስጥ የሚገባ አይደለም:: ስለዚህ በዚህ ንግግር ላይ ኢየሱስ የሚዘረጋቸው (የሚጥላቸው) አካሄዶችና መርሖች ለሁለቱም ሁኔታዎች እኩል አግባብነት አላቸው:: ወንጌል በሮም ግዛት ውስጥ ሙሉ በሙሉ መሰበኩ የ70 ዓ.ም. ድርጊት ቀዳሚ መሆኑ፣ ታላቁ ተልእኮ የዳግም ምጽአት ቀዳሚ ሆኖ መፈጸሙን ሊያመለክት ይችላል:: ንስሐ መግባት ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጋር እስከ ተገናኘ ድረስም የሐዋርያት ሥራ 3÷19-20ም ወደዚህ አቅጣጫ ሊያመለክት ይችላል:: እንድንሠራ የተጠየቅነውን ነገር ካጠናቀቅን በኋላ ኢየሱስ የሚመለስ መሆኑ እንግዳ ሐሳብ ነውን?

ወደሚቀጥለው ክፍል ከመንዛችን በፊት አንድ የመጨረሻ ማሳሰቢያ እነሆ:: ኢየሱስ፣ «እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል» ብሏል:: ወይም ሉቃስ «ነፍሶቻችሁን ታተርፋላችሁ» ብሏል:: ይህ ሐሳብ ማቴዎስ ወንጌል ውስጥ በሌላ ቦታ የተገለጸ ቢሆንም እንኳ (ማቴ 10÷22፤ ዕብ 10÷36-39፤ ራእ 2÷10-11 ወዘተ)፣ የድነት ቅድመ ሁኔታ ተደርጎ ስለ ጽናት መነገሩ አይደለም:: የኢየሩሳሌምን መጥፋት ያመለክታል:: በኢየሱስ በማመናቸው ምክንያት የተጠሉት ከተማይቱን ለቀው ሄዱ፤ ዘግናኝ ጥፋቷንም አስቀሩ:: ሉቃስ እንዳለው ነፍሳቸው ተረፈች:: በሌላ በኩል ግን ኢየሱስን የተዉት እንደ ሌላው የኢየሩሳሌም ክፍል በተመሳሳይ ፍርድ ውስጥ ነበሩ::



**§ 139ሐ**
**የጥፋት ርኵሰት**
**(ማቴ 24÷15-28፤ ማር 13÷14-23፤ ሉቃ 21÷20-24**

(ማቴ24)15እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተነገረው፣
የጥፋት ርኵሰት በተቀደሰው ስፍራ (ስፍራው ባልሆነ
ቦታ[ማር]) ቆሞ ስታዩ አንባቢው ያስተውል:: («ኢየሩሳሌም
በጦር ሰራዊት ተከባ በምታዩበት ጊዜ[ሉቃ]) 16በዚያን ጊዜ
በይሁዳ የሚገኙ ወደ ተራራዎች ይሽሹ፤ 17በቤቱ ጣራ
ላይ የሚገኝ ማንም ሰው ዕቃውን ከቤቱ ለማውጣት አይውረድ:: 18በዕርሻ ቦታው
የሚገኝ ማንም ሰው ልብሱን ለመውሰድ አይመለስ:: (በከተማ ያሉትም ከዚያ
ይውጡ፤ በገጠር ያሉትም ወደ ከተማዪቱ አይግቡ፤ 22የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ
ይህ የበቀል ጊዜ ነውና::[ሉቃ]))»

«መለየትን የሚያመጣው ጥላቻ» መርከስንና ጥፋትን የሚያመጣ ድርጊት ወይም አንድ ነገር ነው:: ይህ ዘግናኝ ነገር በቅዱሱ ቦታ (ይኸውም በቤተ መቅደስ) የሚፈጸም መሆኑን ዳንኤል አስቀድሞ ተነበየ:: በኪዳናቱ መካከል የነበሩት አይሁድ ይህን ሁኔታ በ167 ዓ.ቅ.ክ. ከሰራዊቱ ጋር ወደ ቤተ መቅደሱ ከገባው ሶርያዊው አንጢዮስ ኤጲፋኔስ ጋር በትክክል አገናኙት:: ይህ ሰው ብዙ የሃይማኖት ሰዎችን ገደለ፤ ሰራዊቱ ቤተ መቅደሱ ውስጥ ዝሙት እንዲፈጽም ፈቀደ፤ በእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ ዐሣማ ዐረደ፤ ከዚያም ህንጻውን አፈራረሰው (1መቃ 1÷54-61፤ 6÷7):: ይህ «የጥፋት ርኵሰት» ጥሩ ምሳሌ ነው:: «የጥፋት ርኵሰት» 63 ዓ.ቅ.ክ. ንም ይመለከታል:: በዚህ ጊዜ የሮም ጀኔራል ፖምፔ ከተማዋን አፈራረሳት፤ ወደ ቅድስተ ቅዱሳንም ገባ:: ይህ ጉዳይ ወደፊት እንደሚፈጸም ኢየሱስ አይቶ ነበር:: በ70 ዓ.ም. የተፈጸመው ጥፋት ከዚያ ገለጻ ጋር ይስማማል:: በተለይ ሉቃስ ሁኔታውን «ኢየሩሳሌም በጦር ሰራዊት ተከባ» (21÷20) ያለው ስጤን ይህ እውነት ነው:: ኢዮሳፍስ (*Wars*) የዚያን ዘግናኝ የጥፋት ርኵሰት እንደሚከተለው ይገልጸዋል::

| | |
|---|---|
| 5.31 | የሕዝቡ ጩኸት ከጦርነቱ ድምፅ ይልቅ ከፍ ያለ ነበር:: |
| 5.429-438 | አይሁድ ወታደሮች ምግብ ለማግኘት ሲሉ ሕዝቡን አሠቃዩት:: ልጆች ዕድሜያቸው ከገፋ ወላጆች ምግብ ሰረቁ፤ እናቶች ደግሞ ከሕፃናቶቻቸው ምግብ ሰረቁ:: |
| 5.446-451 | በሺህ ቤት የሚቈጠሩ የስቅላት ግድያዎች:: |
| 6.1-2 | የረሀቡና የሬሳ ቊልል አስፈሪ ገለጻ:: |
| 6.201-213 | ከተማዋ ውስጥ ሰውን ሰው መብላቱ - እናት የራሷን ልጅ በላች:: |
| 6.271-280 | የኢየሩሳሌም መቃጠል:: |
| 6.285-288 | የሐሰት ነቢያት እግዚአብሔር ያድነናል አሉ:: |
| 6.420 | 1,100,000 ሰዎች ሞቱ፤ በምርኮም ተወስደው ለባርነት ተሸጡ:: |
| 7.1-3 | ከጥቂት የታወቁ ማማዎች በቀር ደንጋይ ሁሉ ፍርስርሱ ወጣ:: |

እነዚህ ትንቢያዎች ሁሉ 70 ዓ.ም.ን ማመልከት አለባቸው፤ ዳግም ምጽአትን የሚመለከቱ ቢሆን ኖሮ፣ ሰዎች ወደ ይሁዳ ተራሮች እንዲሸሹ ለምን ታዘዙ? ኢየሱስ ሲመጣ ከእርሱ ሊያመልጡ ነውን≅ ክርስቲያኖች ከኢየሱስ ለመሸሽ ለምን ይፈልጋሉ≅ በዚህ ዐውድ መሠረት ቊ 16-18 ለዳግም ምጽአት ፋይዳ የላቸውም:: በኢየሩሳሌም መጥፋት ግን ከፍተኛ ፋይዳ አላቸው:: በ70 ዓ.ም. ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ በነበረው ከበባ ሲስተስ ጋሉስ በ68 ዓ.ም. ከከተማዋ ምስጢራዊ የሆነ ማፈግፈግ አደረገ (Josephus, *Wars* 2.538-539)::

> ነገር ግን የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በጦርነቱ ወቅት ከተማዋን ለቀው ዮርዳኖስ ማዶ ወዳለችውና ፔላ ተብላ በምትጠራ ከተማ ውስጥ እንዲኖሩ ታዘው ነበር::



> በክርስቶስ ያመኑ ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም በመጡ ጊዜ የአይሁድ ቤተ መንግሥት፣ ከተማና መላው የይሁዳ ምድር ቅዱሳን ተሚጠው የሄዱባቸው መስለው ነበር ... (Eusebius, Ecclesiastical History, 3.5.3)::

የሮም ሰራዊት ከተማዋን እንደ ከበባት ከተረጋገጠ፣ ኢየሱስ ይናገር የነበረው ከከተማይቱ ስለሚደረገው አማናዊው ሽሽት ነበር:: ሴቶቹ ዕርጉዝ ባልሆኑበት ወይም ሽሽቱ በክረምት ባይሆን ወይም ደግሞ ከሰንበት ዕገዳዎች የተነሣ ቅዳሜ ዕለት መጓዙ አስቸጋሪ ስለሚሆን ሽሽቱ በእነዚህ ወቅቶች ባይሆን ጥሩ ነው (ከማቴ 24÷19-20 ጋር ያነ):: ከአንድ ትውልድ በኋላ የነበሩት ክርስቲያኖች የኢየሱስን ቃል አምነው በመቀበልና ከኢየሩሳሌም የግፍ ጭፍጨፋ በማምለጥ የራሳቸውንና የቤተ ሰዎቻቸውን ሕይወት አተረፉ::

ሉቃስ እነዚህ ሥቃዮች ሁሉ የደረሱት የተጻፈው እንዲፈጸም ነው ይላል:: እርግጥ ነው:: የሚናገረው ስለ ብሉይ ኪዳን ትንቢቶች በተለይ ስለ ዳንኤል 9÷27፤ 11÷31፤ 12÷11 ነው:: ኢየሱስ ራሱም እነዚህ ነገሮች እንደሚደርሱ ከአንድ ጊዜ በላይ በትንቢት ተናግሮአል:- ሉቃ 13÷35፤ 19÷43-44፤ 23÷28-31፤ ማቴ 23÷35-38:: እነዚህ ቊጥሮች ኢየሩሳሌም ስትከበብ ስለሚደርሱት የተለዩ ሥቃዮች አስፈላጊ ዝርዝሮችን አክለው ይዘዋል:: ይህ የደካማ ፖለቲካ ወይም የሰዎች ተፈጥሮአዊ ጭካኔ ውጤት ያለመሆኑን ሐቅም ገልጸዋል:: ይህ የራሱን የእግዚአብሔርን ልጅ ማለትም መሲሑን በመግደላቸው በከተማዋ ላይ የመጣ መለኮታዊ ፍርድ ነው::

ነገር ግን ይህ ጽሑፍ የሚመለክተው 70 ዓመተ ምሕረትን ብቻ ነውን? «የአመፅ ሰው» በቅዱሱ ቦታ ላይ ቁሞ (2ተሰ 2÷1-9፤

ራእ 13፥3-10)[8] ከሚለው ጋር በተያያዘና ይህንኑም ልብ በማለት ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተመራማሪዎች (ተማሪዎች) ሌላ ተጨማሪ የትንቢት ፍጻሜ እንደሚኖር አሻግረው ያያሉ:: ይህ እውነት ሊሆን የሚችል ቢሆንም (ወደፊት ጊዜ የሚገለጠው ይሆናል) የሉቃስ 21፥20 እና 24 ግልጽ ጉድኝት፣ በ70 ዓ.ም. ላይ ኢየሩሳሌምን ወደ ከበቧት ሰራዊት ያመለክታል:: እነዚህ ቃሎች በቀጥታና ሙሉ በሙሉ ኢየሩሳሌም በወደቀች ጊዜ ተፈጸሙ:: ትንቢቱ ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ እንዲሆን የወደፊት ክሥተት (ሁኔታ) አስፈላጊ አይደለም::

«በምድሪቱ ላይ ታላቅ መከራ ይሆናል፤ በዚህም ሕዝብ ላይ ቍጣ ይመጣል፤ [24]በሰይፍ ይወድቃሉ፤ ወደ አሕዛብም ሁሉ በምርኮ ይወሰዳሉ፤ ኢየሩሳሌም የአሕዛብ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ፣ በአሕዛብ የተረገጠች ትሆናለች::

ሉቃ 21፥23ለ-24

[19]በእነዚያ ቀናት ለነፍሰ ጡሮችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው! [20]እንግዲህ ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት ቀን እንዳይሆን ጸልዩ፤ [21]በዚያን ጊዜ፣ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ (እግዚአብሔር ፍጥረትን ከፈጠረበት ጊዜ እንሥቶ[ማር]) እስከ ዛሬ ድረስ ሆኖ የማያውቅ፣ ከዚያም በኋላ የሚስተካከለው የሌለ፣ ታላቅ መከራ ይሆናል:: [22]ቀኖቹ ባያጥሩ ኖሮ ሥጋ ለባሽ ሁሉ ባልተረፈ ነበረ፤ ስለ ተመረጡት (ስለ መረጣቸው ምርጦቹ[ማር]) ሲባል ግን እነዚያ ቀኖች ያጥራሉ::

ማቴ 24፥19-22
ከማር 13፥19-20
ጋር

[8] E.g., Lewis Chafer, *The Kingdom in History and Prophecy* (Philadelphia: Sunday School Times, 1992) and John Walvoord, *Matthew - Thy Kingdom Come* (Chicago: Moody Press 1974).



እነዚህ ቍጥሮች ወደፊት እንደሚፈጸሙ የሚያመለክቱ ሁለት ነገሮች አሉ:: በመጀመሪያ ሉቃስ 21፥24 «የአሕዛብ ሙላት እስኪገባ ድረስ» የሚለው ሮሜ 11፥25ን ይመስላል:: ሮሜ 11፥25 አሁንም የወደፊት ሁኔታን አመልካች እንደሆነ ለማድረግ ይፈልጋሉ:: ነገር ግን ሁለት ቍጥሮች ተመሳሳይ ቃላትን ስለ ተጠቀሙ ስለ አንድ ዐይነት ነገር ይናገራሉ ማለት አይደለም:: እርግጥ ሉቃስና ጳውሎስ ስለ ሁለቱ የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ይናገራሉ:: ሉቃስ የሚናገረው ስለ ኢየሩሌም መጥፋት ሲሆን፣ ጳውሎስ የሚናገረው ወንጌልን ለአሕዛብ ስለ ማድረስ ነው:: አንድ ዐይነት መስለው ቢታዩም ትክክለኛ ተጓዳኞች አይደሉም:: ስለዚህ ሮሜ 11፥25፤ ሉቃስ 21፥24ን የወደፊት ተፈጻሚ ሊያደርገው አይችልም::

ሁለተኛ ማቴዎስ፣ ይህ ሥቃይ ዘመን ከተቈጠረ ጀምሮ አቻ የሌለው በመሆኑ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ወደር አይገኝለትም ይላል:: ከ70 ዓ.ም. ይልቅ በናዚ ጀርመን አያሌ አይሁድ ማለቃቸው በጕልሕ ተመልክቶአል:: ስለዚህ 70 ዓ.ም. የዓለም የመጨረሻው ዘመን መጥፎ ስደት አይደለም ተብሏል:: ከዚያም የተነሣ እነዚህ ትንቢቶች በመጨረሻው ቀን ስለሚደርሰው ብርቱ መከራ ማመልከት አለባቸው:: ይሁን እንጂ ይህ መከራ የሚለካው እንዲሁ በአሐዝ ሳይሆን መከራው በሚያደርሰው መጠን ነው:: ኢዮሳፍስ እንደ ገለጸው 70 ዓ.ም. ከእግዚአብሔር የመጣ ቍጣ ሆኖ በመንፈሳዊና በአካላዊ ሽብሩ ወደር ያልተገኘለት ነበር:: በተጨማሪም ኢየሩሳሌም በወደቀች ጊዜ መዋጋት የነበረባቸው ሮማውያንን ብቻ ሳይሆን በከተማው ውስጥ ተጧጥፎ የነበረውን የእርስ በርስ ጦርነትም መቋቋም ነበረባቸው:: ጉዳዩን የባሰ ሲያደርገውም የ70 ዓ.ም. ሥቃይ የሰው ሕይወት መጥፋቱ ብቻ ሳይሆን፣ ቅድስቲቱ ከተማና የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መርከሳቸውም ነበር:: ቤተ መቅደሱን በማስወገድ፣ ብሎም መሥዋዕቱ እንዲቀር በማድረግ ይህ ክሥተት የአይሁድ እምነትን እስከወዲያኛው

ለወጠው። በዚህ አሳብ መሠረት 70 ዓ.ም. አይሁድ ከዚህ ቀደም ከቶ ያላለፉበት የመጨረሻው ክፉ ተመክሮ ነው።

በመሆኑም ይህን መከራ በዓለም መጨረሻ ላይ ማስቀመጡ በጽሑፉ ላይ መንትያ ችግሮችን ማስከተል ነው። በመጀመሪያ በማቴዎስ 24፥20 እና በቍ. 21 መካከል 2000 ዓመት ያህል አስቸጋሪ ክፍተት አለ። ሁለተኛ ኢየሱስ ይህ ሥቃይ፣ «ከዚያ በኋላ የሚስተካከለው የሌለ» ለምን አለው? የመጨረሻ ከሆነ የሚስተካከለው የሌለ መሆኑ የታወቀ ነው።[9]

ማቴዎስ 24፥22 ከዓለም መጨረሻ ይልቅ ወደ 70 ዓ.ም. የሚያመለክት ይመስላል። ኢየሱስ የተመረጡት በሕይወት ይኖሩ ዘንድ ይህ መከራ በአጭሩ ይቀጫል ብሏል። የተመረጡት በዓለም መጨረሻ በአካል የመኖራቸው ፋይዳ ምንድን ነው? መከራው የአይሁድን 70 ዓ.ም. ይመለከታል መባሉ ትክክል ነው። የመከራውን ጊዜ በማሳጠር እግዚአብሔር የአይሁድን ትሩፋን ለራሱ አስቀረ። ይህ እግዚአብሔር ለሕዝቡ በዘላቂነት የሰጠው ተስፋ ነው (ኢሳ 6፥13፤ ሮሜ 9፥27-29፤ 11፥5:29)።

23«በዚያን ጊዜ ማንም፣ *ይኸውላችሁ
ክርስቶስ እዚህ አለ* ወይም *እዚያ አለ* ቢላችሁ
አትመኑ፤ 24ሐሰተኛ ክርስቶሶችና ሐሰተኛ ነቢያት
ይነሣሉና፤ ቢቻል የተመረጡትን ለማሳት ሲሉ ታላላቅ
ምልክቶችንና ታምራትን ያደርጋሉ። (ስለዚህ
ተጠንቀቁ፤[ማር]) 25እነሆ፤ አስቀድሜ ነግሬአችኋለሁ።

ማቴ 24፥23-28
ከማር 13፥23 ጋር

26«ስለዚህ፣ *ያውላችሁ አበረሐው ውስጥ አለላችሁ* ቢሏችሁ ወደዚያ
አትውጡ፤ *ይኸውላችሁ እልፍኝ ውስጥ አለላችሁ* ቢሏችሁ አትመኑ፤ 27መብረቅ
ከምሥራቅ ወጥቶ ምዕራብ ድረስ እንደሚያበራ፣ የሰው ልጅ አመጣጥም እንደዚሁ
ይሆናል። 28በድን ባለበት ስፍራ ሁሉ አሞሮች ይሰበሰባሉ።»

[ቍ. 25-28 = ሉቃ 17፥23-24:37፣ የክፍል 120ለ ማብራሪያን ይመልከቱ]

«በዚያን ጊዜ» ቃል በቃል «ከዚያም» በግሪክኛ ቶቴ፣ የሚለው ቃል አንዳንድ ጊዜ የሂደትንና የጊዜን ቅደም ተከተል የሚመለከት ሲሆን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ተጠየቃዊ ምልክት ነው። ከዚህ ላይ የኋለኛ ውን የሚያመለክት ይመስላል። ቀጥሎ ምን እንደሚሆን ብዙ ባይናገርም ሐሰተኛ መሲሖች ብቅ ባሉ ቍጥር የእነርሱን ተጠየቃዊ አንድምታ ያመለክታል። ኢየሱስን ለማየት ጓግተናል። በዚህ ዓለም ችግር ተቸግረናል። ይህ ሁኔታ ኢየሱስ ነን በሚሉ ሐሰተኛ መሲሖች እንድንታለል ያዘጋጀናል ይህ አዲስ ነገር አይደለም (ከ2ተሰ 2፥1-2 ጋር ያነ)። ውስብስብም አይደለም። ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ እንደ መብረቅ በግልጥ የሚታይ ይሆናል። ስለዚህ አንድ ሰው ክርስቶስ ነኝ ብሎ ትከተለው ዘንድ ቢጠይቅህ አትከተለው። ክርስቶስ መጥቶ ይወስድሃል፤ በመሆኑም በምድረ በዳ ወይም በድብቅ የባዕድ አምልኮ ግቢ ውስጥ ኢየሱስን መፈለግ የለብህም። «ሐሰተኛ ክርስቶሶች» ታምሮቻቸው ማስመሰያ ናቸው ማለት አይለደም፤ ወደ እግዚአብሔር ከመምራት ይልቅ ያታልላሉ ማለት ነው እንጂ።[10]

---

[9] Blomberg (p. 359) ይህ የመከራ ዘመን በ70 ዓመተ ምሕረት እውን ከሆነው ከኢየሩሳሌም መውደም ጀምሮ እስከ ክርስቶስ መመለሻ ድረስ ያለውን ሙሉ ዘመን ያካትታል ይላል። ይህ 70 ዓመተ ምሕረትን የመከራ መጨረሻ አድርጎ የመግለጽን ችግር ቢያቀልልም እንኳ፣ ሌላ ችግር ያስከትላል። እነዚህ ገለጻዎች (ቍ. 15-25) በተወሰነ ጉዳይ ላይ በእጅጉ ያነጣጠሩ ናቸው። ቍ. 21 ይህን ሁሉ ዘመን ያካትታል ማለት ከዐውዱ ባሕርይ መውጣት ይመስላል።



[10] ከ G. Harris, "Satan's Deceptive Miracles in the Tribulation" *BS* 156/623 (1999):308-324 ጋር ያጻጽሩ።

እነዚህ ሰዎች ክርስቶስ ዳግም እስከሚመጣ ባለው የታሪክ ዘመን ሁሉ ይመጣሉ:: ለምሳሌ ሉቃስ የኢየሱስን ዳግም ምጽአት ለመግለጽ እነዚህኑ ቃላት ተጠቅሞአል (17፥22-24:37):: ይሁን እንጂ ከ70 ዓ.ም. ጋር እኩል ፋይዳ አላቸው (ከማቴ 24፥5 ጋር ያነ):: ያለው ብቸኛ ልዩነት፣ እነዚህ ሐሰተኛ መሲሖች ታላላቅ ምልክቶችን እንደሚፈጽሙ ማቴዎስ ያከለ መሆኑ ነው:: ይህ «የመጨረሻ ጊዜ ንግግር» ቢመስልም እንኳ (ከማቴ 7፥21-23፤ ከ2ተሰ 2፥9-12፤ ከራእ 13፥11-17 ጋር ያነ)፣ ሁለቱንም ሁኔታዎች በእኩል ደረጃ የሚመለከት እንዲሆን ማድረግ ይቻላል::

አሁን ቊጥር 27-28ን ይዘን ወደ መጨረሻው እንንዛለን::[11] ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ የከፋ ፍርድ ይሆናል:: ቊጥር 28 በሥዕላዊ መንገድ የሚገልጸው ከፍርድ ቤት በሆነው ሥዕል ሳይሆን ከጦርነት ሜዳ በሆነ ሥዕል ነው:: የሰማይ አሞራዎች በበሰበሰው ሥጋ ሐሤት ያደርጋሉ፤ ይህ ሁሉ ሬሳ በመላ ምድሪቱ ይረፈረፋል (ከራእ 19፥11-21 ጋር ያነ):: ፍርዱ ኢየሱስ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ እንደሚሆነው ዐይነት ይሆናል:: በሌላ አነጋገር ኀጢአት ባለበት ፍርድ መኖሩ አይቀርም:: ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ ሰው ሁሉ እንደሚያየው ሁሉ እያንዳንዱም ኀጢአት የፍርዱ ሰለባ ይሆናል::

**§ 139መ**
**የሰው ልጅ መምጣት**
**(ማቴ 24፥29-31፤ ማር 13፥24-27፤ ሉቃ 21፥25-27)**

እንደ ቊጥር 27-28 ይህ ምንባብ ቀድሞውንም የተመለከተው ወደ ዳግም ምጽአቱ ነበር:: ነገር ግን የብሉይ ኪዳን ዳራቸውን ይዘን ስናነባቸው በ70 ዓ.ም. የነበረውን ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ነውጥም

---

[11] J.A. O' Flynn ቊ 27፣ ኢየሱስ በ70 ዓ.ም. ካደረገው ፍርድ አንጻር በአቡቀለምሲሳዊ መልኩ ሊታይ ይችላል በማለት ቢከራከርም እንኳ ["The Eschatological Discourse," *ITQ* 18 [1951]:277-281]::



ሊገልጹ ይችላሉ:: እንዲያውም በሉቃስ ወንጌል ውስጥ እነዚህ *ጋላክሲካዊ* ነውጦች ከማቴዎስና ከሉቃስ ወንጌል ይልቅ ከኢየሩሳሌም ውድቀት ጋር ተያይዘዋል::

**ማቴ 24፥29**

[29]ወዲያውኑ ከእነዚያ ከመከራ ቀናት በኋላ፣ ፀሐይ ትጨልማለች፤ ጨረቃ ብርሃኗን ትከለክላለች፤ ከዋክብት ከሰማይ ይረግፋሉ፤ የሰማይ ኀይላትም ይናጋሉ::

*[29]ኢሳይያስ 13፥10፤ 34፥4*

**ሉቃ 21፥25-26**

[25]...ከባሕሩና ከሞገዱ ድምፅ የተነሣ በምድር ላይ ያሉ ሕዝቦች ይጨነቃሉ፤ ይታወካሉም፤ [26]የሰማያት ኀይላት ስለሚናወጡ፣ ሰዎች በፍርሃት በዓለም ላይ ምን ይመጣ ይሆን እያሉ በመጠባበቅ ይዝላሉ::

**ማቴ 24፥30-31**

[30]«በዚህ ጊዜ የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ላይ ይታያል፤ የምድር ወገኖች ሁሉ ያለቅሳሉ፤ የሰው ልጅም በሰማይ ደመና ላይ ሆኖ በኀይልና በታላቅ ክብር ሲመጣ ያዩታል፤ [31]መላእክቱንም ከታላቅ የመለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፤ እነርሱም ምርጦቹን ከአራቱም ነፋሳት፣ ከሰማያት ከአንዱ ዳርቻ ወደ ሌላው ዳርቻ ይሰበስባሉ::»

ከመከራው ዘመን በኋላ «ወዲያወኑ»፣ «ጋላክቲካዊ» ብጥብጥ ይሆናል:: ይህ መቼ ይሆናል? እንግዲህ «ወዲያውኑ» የሚለው ቃል ነቢያዊ ቃል መጠቀምን ሳያመለክት አይቀርም:: ይህም «በተከታታይ ሁኔታዎች ውስጥ ቀጥሎ ያለው» ማለት ሲሆን፣ ገና በሩቅ ያለ ነገር

ሊሆን ይችላል:: ይህ እንደ ተጠበቀ ሆኖ «ወዲያውኑ» የሚለው ቃል አዲስ ኪዳን ውስጥ ለማኒያ ጊዜ ተጠቅሷል:: ይህም ዘወትር፣ «ሳይዘገይ፣ ከዚያው ላይ፣ ከዚያ ሳይርቅ» ማለት ነው:: ከዚህ እሳቤ ልዩ የሆኑት ሁለት ብቻ ናቸው:: በመጀመሪያ ማርቆስ 4-5 በዐፈሩ ምሳሌ ላይ ቡቃያው «ወዲያውኑ» ብቅ ይላል፤ ምክንያቱም ዐፈሩ ጥልቀት አልነበረውም:: እዚህ ላይ በተለይ ከሌሎች ቡቃያዎች ጋር ሲነጻጸር ቃሉ የሚያመለክተው በጣም አጭር ጊዜን ነው:: ሌላውና ልዩ የሆነው ዮሐንስ፣ «በቅርቡ ላይህ ተስፋ አደርጋለሁ» ያለበት 3ኛ ዮሐንስ 14 ነው:: ርግጥ ነው ጉዞ ጊዜ መውሰዱ አይቀርም:: ስለዚህ ቃል «አጭር ጊዜ»[12] ተብሎ ግንዛቤ ሊወስድበት ይችላል:: የ2000 ዓመት መዘግየት ግን የማይታመን ነገር ሳይሆን አይቀርም:: «ወዲያውኑ» የሚለው ቃል ለማቴዎስ ያልተለመደ በመሆኑ፣ ከዚህ ላይ ለእርሱ ልዩ ፋይዳ ያለው ቃል ይመስላል:: ከዚህም የተነሣ ማቴዎስ 24፥23-28 ከኢየሩሳሌም ጥፋት ጋር በተያያዘ መልኩ አንዳች ፋይዳ ካለው፣ «ወዲያውኑ»ን ተከትሎ የሚገኘው የቍጥር 29-31 ሁኔታ ለ70 ዓ.ም. ሁኔታዎች ተምሳሌታዊ በሆነ መልኩ አመላካችነት ሊኖረው ይችላል::[13]

እነዚህ ቍጥሮች የማታ ማታ (ዞሮ ዞሮ) ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ የሚፈጸሙ ቢሆኑም፣ ጉልቍ መሳፍርት የሌላቸው እነዚህ ሁኔታዎች የኢየሩሳሌምን መጥፋት ሥዕላዊ በሆነ መልክ ያሳያሉ:: ይህ ለእኛ እንግዳ ነገር ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን የብሉይ ኪዳንን ጽሑፍ በሚገባ ላስተዋሉት ደቀ መዛሙርት ትስስሩን ለማየት ችግር የለባቸውም:: ለምሳሌ *ፀሐይ ትጨልማለች፤ ጨረቃ ብርሃኗን

[12] ኢዩቴዎስን - *eutheos* ኢውሱን ጊዜ አድርጎ ወዲያውኑ ብሎ መተርጐም ትክክል አይደለም፤ ከFloyd Hamilton, *The Basis of Millennial Faith* (Grand Rapids: Baker, 1959). p. 68 ጋር ያነጻጽሩ::

[13] T. Hatina "The Focus of Mk 13:24-27 - The Parousia or the Destruction of the Temple?" *BBR* 6 (1996): 43-66 በሚለው ላይ ሐተታ ያቀርባል::



ተከለክላለች፤ ከዋክብት ከሰማይ ይረግፋሉ፤* የሚለው ሐረግ የትልቅ ሕዝብን ውድቀት ለመግለጽ ብዙ ጊዜ ብሉይ ኪዳን ውስጥ ጥቅም ላይ ወሎአል:: ኢሳይያስ 13፥10:19 ውስጥ ባቢሎንን ያመለክታል:: የነቢያትን ቃል በመጠቀም ኢየሱስ የታላቅ ሕዝብን ውድቀት ገለጸ፤ «እንዲህ ሲባል ግን ይህ ቋንቋ የመላለምን ጥፋት ያመለክታል ማለት አይደለም» (Lewis p. 128)::

እንዲያውም አንዳንዶች ማቴዎስ 24፥30ን ከኢየሩሳሌም መውደቅ ጋር ያገናኙታል:: «የሰው ልጅ በደመና ውስጥ» የሚለው ሐረግ ጌታ ቍጣንና ቅጣትን ይዞ መምጣቱን የሚያመለክት ሲሆን (በዳን 7፥13-14 ላይ በመመሥረት)፣ የአይሁድ ፈሊጣዊ (ዘይቤአዊ) አነጋገር ሆኖ «የጌታ ቀን ነው» ተብሎ ሊተረጐም ይችላል:: ይህ ጌታ በደመናና (ዘዳ 33፥26፤ መዝ 68፥4) በቍጣ (ኢሳ 30፥27፤ ሕዝ 30፥13፤ ናሆ 1፥3) ሲመጣ ከሚሉ አንዳንድ የብሉይ ኪዳን አመላካቾች ጋር ይስማማል:: እንዲያውም እኮ ይህ ጥፋት ሰዎች ኢየሱስን በመግደላቸው (ሉቃ 19፥42-44፤ 23፥28-31፤ ማቴ 23፥35-39) የእግዚአብሔር ቍጣ ውጤት ነው:: ከዚህም በላይ፣ «የምድር ወገኖች ሁሉ ያለቅሳሉ» የሚለው ቃል በቃል፣ «የምድሪቱ ነገዶች ሁሉ» ተብሎ ሊተረጐም ይችላል:: ስለዚህ ይህ የቍ 30 ለቅሶ የአይሁድን እንባ ሊያመለክት ይችላል:: አንዳንዶች በራሳቸው ሥቃይ ያለቅሳሉ፤ ሌሎች ደግሞ ኢየሱስን በመግደላቸው ያዝናሉ (ዘካ 12፥10-14፤ ዮሐ 19፥37):: ይሁን እንጂ ዞሮ ዞሮ ሕዝቦች ሁሉ በደረሰባቸው ቅጣት የሚያለቅሱበትን የኢየሱስን ዳግም ምጽአት ያሳያል (1ተሰ 4፥17፤ ራእ 1፥7):: ያ ቀን የመለኮታዊ አዝመራ መሰብሰቢያ ቀን ይሆናል (ቍ 31፤ ከማቴ 13፥24-30:47-50 ጋር ያነ)::

(ማቴ24)32«ከበለስ ዛፍ ይህን ትምህርት ተማሩ፤ ቅርንጫፏ ሲለመልም፣ ቅጠሏ ሲያቈጠቍጥ፣ ያን ጊዜ በጋ እንደ ተቃረበ ታውቃላችሁ። 33እንደዚሁም እነዚህን ሁሉ (መፈጸማቸውን ማር) ስታዩ እርሱ በደጅ እንደ ቀረበ ታውቃላችሁ። 34እውነት እላችኋለሁ፤ ይህ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም። 35ሰማይና ምድር ያልፋሉ፤ ቃሌ ግን ፈጽሞ አያልፍም።»

**§ 139ሠ**
**የበለስ ዛፍ ምሳሌ**
**(ማቴ 24÷32-41**
**ማር 13÷28-32**
**ሉቃ 21÷28-33)**

*34ወይም ትውልድ*

የበለስ ዛፍ ምሳሌ ግልጽ ነው። ከቅርንጫፉ የሚወጣው ፎጠና አረንጓዴ ሲሆንና ትናንሽ ቅጠሎች ሲወጣ ስታዩ በጋ እየመጣ መሆኑን ታውቃላችሁ። በሌላ አነጋገር የሚመጣውን ወቅት አስቀድመው የሚናገሩ ተፈጥሮአዊው አንዳንድ ምልክቶች ዓለም ውስጥ አሉ። እንደዚሁም የሚመጣውን የኢየሩሳሌም ጥፋት ለማወቅ ያግዟቸው ዘንድ (ከማቴ 16÷28፤ ከማር 9÷1፤ ከሉቃ 9÷27 ጋር ያነ) ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ አንዳንድ ምልክቶችን ሰጣቸው። በኢየሱስ ቃል ሊተማመኑ ይችላሉ። እንዲያውም የኢየሱስ ቃል ከተፈጥሮአዊው መላለም (ማቴ 24÷35) ይልቅ በላቀ ጽኑና ዘላቂ ነው። ወደፊት ለሚያጋጥማቸው መከራ የሚያስፈልጋቸው መጽናናት በእርግጥ ይህ ዐይነቱ ነው።

እንግዲህ ብዙ ተንታኞች የበለስ ዛፍ ምሳሌ የኢየሱስን ዳግም ምጽአት ይመለከታል ይላሉ።[14] የሉቃስ «የቤዛነት» ሐሳብ በአብዛኛው ሮሜ 8÷23ን ይመስላል። ከዚህ ቀደም ልብ እንዳልነውም ቀደም ያሉት ቍጥሮች (ማቴ 24÷27-31፤ ማር 13÷24-27፤ ሉቃ 21÷25-27) ዳግም ምጽአትንና የኢየሩሳሌምን መጥፋት ያመለክታሉ ተብለው ሊታሰቡ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ እነዚህ ቍጥሮች እንደ ቀደመው ምንባብ ዐይነት «ዕጥፍ አገልግሎት» አላቸው እንል ዘንድ አያስገድደንም። እንግዲህ ልብ በሉ ኢየሱስ ልዩነት ሳያደርግ ሁለቱንም ጥያቄዎች በመመለስ ላይ ነው። ዕጥፍ ዘይቤን መጠቀምና ከዚያም ስለ 70 ዓመተ ምሕረት ብቻ ወደሚናገረው ይዘት መመለሱ ለእርሱ እንግዳ ነገር አይደለም። ይህ ምሳሌ ዳግም ምጽአትን ለምን እንደማያመለክት የሚያሳዩ አንዳንድ ምክንያቶች አሉ።

*በመጀመሪያ*፣ ምሳሌው ወደፊት እንዲመለከቱና የመከራውን ወቅት እንዲለዩ ደቀ መዛሙርቱን ያደፋፍራል። ይህ ለ70 ዓ.ም. ክሥተት (ሁኔታ) ተገቢ ሲሆን ለዳግም ምጽአት ግን ተገቢ አይደለም። የማቴዎስ 24÷36-25÷30 ጠቅላላ ሐሳብ ኢየሱስ መቼ እንደሚመጣ *ማወቅ አትችሉም* የሚል ነው። አንዳንዶች ቀኑን ወይም ሰዓቱን ማወቅ ባንችልም ወሩንና ዓመቱን ማወቅ እንችላለን በማለት በዚህ እንቆቅልሽ ውስጥ መላ አላቸው። እነዚህ ትንበያዎች በአሁኑ ጊዜ ድምር ውጤታቸው አልቦ መቶኛ ከመሆኑም በላይ የኢየሱስን ግልጽ ቋንቋ (ሐሳብ) ማስተዋል አልቻሉም። ቀኑንም ሆነ ሰዓቱን፣ ወሩን ወይም ዓመቱን ይሁን ኢየሱስ መቼ እንደሚመጣ ማወቅ አንችልም። «ቀንና» «ሰዓት» የተባሉት ቃላት በጥቅሉ ጊዜን ያመለክታሉ እንጂ፣ የተለየውን ቅደም ተከተላዊ ጭማሬ አያመለክቱም (7÷22፤ 10÷19፤ 24÷42:44:50፤ 25÷13፤ 26÷45)። «ቀን» የሚለው ቃል «የጌታን ቀን ያመለክታል»። ይህም በነቢያዊ ቃል ሲገለጽ፣ «እግዚአብሔር ለፍርድና ለድኅነት የሚመጣበት ቀን» ማለት ነው (ኢል 2÷11፤ አሞ 5÷18:20፤ ሚል 4÷5)። በሌላ አነጋገር «ቀን» የሚለው ቃል ያዘለው ሐሳብ የዘመኑን ፍጻሜ ነው። ያ መቼ እንደሚሆን ማወቅ አንችልም። ስለዚህ እንዘጋጅ ዘንድ ተመክረናል።

[14] እነዚህን ሁለት ትርጓሜዎች ለማነጻጸር A. McNicol, "The Lesson of the Fig Tree in Mark 13:28-32: A Comparison Between Two Exegetical Methodologies," *RestQ* 27 (1984): 193-207 ይመልከቱ።

ሁለተኛ፣ ቍጥር 36 በጥንድ ንኡስ አገባቦች peride [«ነገር ግን» በማለት ይጀምራል:: NIV - New International Version] የተባለው የእንግሊዝኛ ቅጅ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ሳይተረጐመው ቀርቷል:: ይህ ትስስር ጠንካራ ንጽጽርን እውን የሚያደርግ መሆኑ የሚገርምና «ነገር ግን» የሚለውን ማያያዣ ሐረግ አድምቆ እንደ ማሳየት ያለ ግሩም ነው:: በሌላ አነጋገር ቍጥር 36 ጕልሕ የሆነ የአጽንዖት ለውጥን የሚመለከት ይመስላል:: ስለዚህ ቍጥር 36ን ምዕራፉን የሚከፍል መሥመር አድርጎ ማየቱ ምክንያታዊ ነው:: 70 ዓመተ ምሕረትንና የክርስቶስን መመለስ የሚመለከቱ አንዳንድ ይዘቶች በመጀመሪያው የምዕራፉ አጋማሽ ቢኖሩም እንኳ (ይኸውም ቍ 23-31)፣ አስቀድሞ ነገር የሚያተኵረው ግን በመጀመሪያው ምእት ዓመት ሁኔታዎች ላይ ነው:: ይሁን እንጂ የቀረው ክፍል ማቴዎስ ምዕራፍ 24 እና 25 ሙሉ በሙሉ የሚያተኵረው በዳግም ምጽአት ላይ ብቻ ነው::

ሦስተኛ፣ ኢየሱስ እነዚህ ነገሮች ሁሉ የሚፈጸሙት በአንድ ትውልድ ዘመን ውስጥ ነው ብሏል:: አድማጮቹ (ተደራስያኑ) አርባ ዓመትን ግምት ውስጥ ሳያስገቡ አልቀሩም፤ ራሳቸውን ጨምረው ማየታቸውም ያለ ነው:: ይህም በርግጥ የሚገጣጠመው፣ «በመጨረሻው ዘመን» ከሚታዩት ሁኔታዎች ጋር ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ከ70 ዓ.ም. ጋር ነው:: አንዳንድ የተሰነዘሩ መፍትሔዎች አሉ፤ (1) ግድፈቱ የጌታ ወይም የማቴዎስ ነው ብላችሁ ዐስቡ፤ ይህን አንቀበልም:: ምክንያቱም፣ (ሀ) የላቀ ማብራሪያ አለ፤ እና (ለ) መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛቱን በጕልሕ አሳይቷል:: (2) ትውልዱን - ኍጠር ጀምር (ይኸውም 40 ዓመት)፤ ቈጠራውን የምትጀምረውም ከኢየሱስ ዘመን ሳይሆን ከበለስ ዛፍ ማቆጥቆጥ ነው:: ይህ የበለስ ዛፍ ማቆጥቆጥም እ.ኤ.አ. በ1948 ዓ.ም. ከአይሁድ መንግሥት መልሶ መቋቋም አንስቶ 40 ዓመታቱ እስከሚያልፉ ድረስ በ1967 ዓ.ም. ከተካሄደው ከስድስቱ ቀን ጦርነት ጋር ተያይዞ ይታያል:: ይህ በሥነ



ልሳናዊነት ረገድ የሚቻል ቢሆንም እንኳ፣ በዚህ ዐውድና ኢየሱስ ይህንኑ ትውልድ የሚለውን ቃል ከተጠቀመበት ሌሎች አገባቦች አንጻር ግን የሚቻል አይመስልም (ከማቴ 16÷28፤ 23÷35-36፤ ከማር 9÷1፤ ከሉቃ 9÷27 ጋር ያነ):: (3) አንዳንዶች «ትውልድ» የሚለው ቃል በተለይ የአይሁድን ሕዝብ የሚመለከት ሆኖ «ሕዝብ» ተብሎ መተርጐም አለበት ይላሉ:: አልፎርድ የተባለ ጸሐፊ ግልጽ እንዳደረገው ሁሉ «ጀኒያ- genea» የሚለው ቃል በሄሌናዊ ግሪክ «የሰው ዘር ወይም የሰዎች ቤተ ሰባዊ አንድነት» የሚል ትርጕም አለው፣ (ከሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ኤር 8፡3 እና ከማቴ 23፡36 ጋር ያነ)[15]:: ይህም አንዳንዶቹን እስከ መጨረሻው ዘመን ድረስ ያለውን ቀጣይ ትውልድ እንዲያስቡ አድርጎአቸዋል (Ryle, p. 323):: ርግጥ ነው ማቴዎስ 12÷45፤ 17÷17፤ 23÷36፤ ሉቃስ 16÷8፤ 17÷25 እና ፊልጵስዩስ 2÷15 ሙሉውን (ጠቅላላውን) የእስራኤልን ሕዝብ ይመለከታል ተብሎ ግንዛቤ ሊገኝበት ይችላል:: ይሁን እንጂ አሁንም «በዚያን ጊዜ» ነው:: ግልጽና በጣም ቀጥተኛ የሆነው የ«ትውልድ» ግንዛቤ የኢየሱስ ዘመነኛ የሆኑት ሰዎች ናቸው:: ቍጥር 27-31 ዳግም ምጽአትን የሚመለከቱ ቢሆንም እንኳ በኢየሱስ ፊት የቆሙት በቍጥር 4 እና 35 መካከል የተጻፈው ሁሉ ሲፈጸም ያያሉ::

**§ 139ሠ (ይቀጥላል)**
**የመምጫውን ጊዜ ማንም አያውቅም**
**(ማቴ 24÷36-41፤ ማር 13÷32)**

(ማቴ24)36«ያን ቀንና ሰዓት ግን ከአብ በስተቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ፣ ወልድም ቢሆን ማንም አያውቅም:: 37ልክ በኖኅ ዘመን እንደ ሆነው የሰው ልጅ መምጣትም እንደዚሁ ይሆናል፤ 38ከጥፋት ውሃ በፊት ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ ሰዎች ሲበሉና ሲጠጡ ሲያገቡና ሲጋቡ እንደ ነበረ፣ 39እስከዚያ ጊዜ

[15] Henry Alford, *The Greek Testament, Vol .1* (Chicago: Moody, 1958), p. 244.

ድረስም ምን እንደሚመጣ ሳያውቁ ድንገት የጥፋት ውሃ እንዳጥለቀለቃቸው፣ የሰው ልጅ ሲመጣም እንደዚሁ ይሆናል:: 40በዚያን ጊዜ ሁለት ሰዎች በዕርሻ ላይ ይውላሉ:: አንዱ ይወሰዳል፤ ሌላው ይቀራል:: 41ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዷ ትወሰዳለች፣ ሌላዋ ትቀራለች::»

*ʿ36 አንዳንድ ቅጂዎች ወይድም ቢሆን የሚለው የላቸውም::*

[ቍ 37-41 = ሉቃ 17÷26-27:34-35፣ የክፍል 120ለ ማብራሪያን ይመልከቱ]

ከዚህ ጀምሮ ያለው ሁሉ ዳግም ምጽአቱን ይመለከታል:: ኢየሱስ ስለ ዳግም ምጽአት ሦስት ዋና ዋና እውነቶችን ይገልጻል:: በመጀመሪያ መቼ እንደሚሆን ማወቅ እንደማንችል በግልጽ ቋንቋ ይናገራል:: መላእክት እንኳ መቼ እንደሚሆን አያውቁም:: እንዲያውም ኢየሱስ እንኳ መቼ እንደሚመለስ አያውቅም:: ይህ ሆኖ ሳለ እኛ እናውቃለን ብለን እናስባለን?!

ሁለተኛ የእርሱ መምጣት ብዙ ሰዎችን እንደሚያስገርም ኢየሱስ ተናግሯል:: ከኖኅ ዘመን ጋር ያነጻጽረዋል:: ኖኅ የጥፋት ውሃ በመምጣት ላይ ነው በማለት ለ0ሥርት ዓመታት ሰበከ:: ነገር ግን ሰዎች የተለመደውን ሥራ እየሠሩ ችላ አሉት:: የጥፋት ውሃ በመጣ ጊዜ ያልታሰበ አደጋን ይዞ ሳያስቡት ደረሰባቸው:: ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣም የሚሆነው እንደዚሁ ነው::

ሦስተኛ ዳግም ምጽአት በጣም ቅርብ የሆነውን ግንኙነት እንካ ይለያያል:: ሁለት ሰዎች አንድን ዕርሻ በአንድ ላይ ያርሳሉ፤ አንዱ ከሌላው ይነጠላል:: በወፍጮ ላይ የሚፈጩ ሴቶች ይለያያሉ:: ሉቃስ በ17÷34 ውስጥ በአንድ አልጋ ላይ የተኙ ሁለት ሰዎች ይለያያሉ ይላል:: ይኸውም ባሎች ከሚስቶቻቸው፤ ልጆች ከወላጆቻቸው::



§ 139ረ
ለኢየሱስ መምጣት እንድንዘጋጅ የሚገፋፉ አራት ምሳሌዎች
(ማቴ 24÷42-25÷30፤ ማር 13÷22-37፤ ሉቃ 21÷34-36)

ኢየሱስ መቼ ተመልሶ እንደሚመጣ ስለማናውቅ፣ ደግሞም መምጣቱ ያልታሰበ በመሆኑ፣ በጣም ቅርብ የሆነውንም ግንኙነት በእጅጉ ስለሚለያየው ኢየሱስ በማንኛውም ሰዓት ይመጣል ብለን ብንዘጋጅ ይመረጣል:: ቀጥሎ ያሉት አራት ምሳሌዎች ዋና ጉዳይም ይኸው ነው:: ሁሉም በየበኩላቸው የሚሉት አንድ ነገር ነው:- ተዘጋጁ!

(ሉቃ21)34«እንግዲህ በገደብ የለሽ ሕይወት፣ በመጠጥ ብዛትና ስለ ኑሮ በመጨነቅ ልባችሁ እንዳይዝልና ያ ቀን እንደ ወጥመድ ድንገት እንዳይደርስባችሁ



ተጠንቀቁ፤ 35ይህ በመላው ምድር በሚኖሩት ሁሉ ላይ ይደርሳልና:: 36ስለዚህ ከሚመጣው ሁሉ እንድታመልጡና በሰው ልጅ ፊት መቆም እንድትችሉ ሁልጊዜ ተግታችሁ ጸልዩ::

ማር 13÷34

34«ይህም ቤቱን ለአገልጋዮቹ ትቶ፣ እያንዳንዱን አገልጋይ በየሥራ ድርሻው ላይ አስማርቶ፣ በረኛው ነቅቶ እንዲጠብቅ አዝዞ የሄደውን ሰው ይመስላል::»

ማርቆስና ሉቃስ ከመጀመሪያው ምሳሌ በፊት ዕጥርታ የሆነ ሐሳብ ያቀርባሉ፤ ያም ይዘጋጁ ዘንድ ደቀ መዛሙርቱን ያስጠነቅቃል:: የማቴዎስን የመጀመሪያ ምሳሌም ይመስላል፤ አራተኛውንም ይመስላል (ማቴ 25÷14-30)::

*ቍጥር 1:- በሌሊት እንደሚመጣ ሌባ:- ኢየሱስ ሳይታሰብ ይመጣል*

ማቴ 24÷42-44

42«እንግዲህ ጌታችሁ የሚመጣበትን ቀን ስላማታውቁ ነቅታችሁ ጠብቁ:: 43ይህን ልብ በሉ፤

ባለቤት ሌሊት ሌባ በየትኛው ሰዓት እንደሚመጣ
ቢያውቅ
ኖሮ፣ በነቃም ቤቱም እንዳይደፈር በተጠባበቀ ነበር:: 44የሰው ልጅም ባላሰባችሁት
ሰዓት ይመጣልና እናንተም እንደዚሁ ዝግጁ ሁኑ::»

[ቍ 42-44 = ሉቃ 12፥39-40፣ የክፍል 108ሐ ማብራሪያ ይመልከቱ]

ሌቦች ባልታሰበ ጊዜ እንደሚመጡ ገልጠው የጉዞ ዝርዝራቸውን አይልኩልህም:: የሚልኩ ከሆነ አደገኛ ውሻ ወይም ጠበንጃ ይጠብቃቸዋል:: ኢየሱስ እንደ ሌባ አስቀድሞ ሳያስጠነቅቅ ይመጣል (ሉቃ 12፥39፤ 1ተሰ 5፥2:4፤ 2ጴጥ 3፥10፤ ራእ 3፥3፤ 16፥15):: ይህ ኢየሱስ ወንጀለኛ እንዳልሆነ የሚያመለክተውን ያህል ምስጢራዊ ሐሜት እንደሚኖርም አያመለክትም:: የንጽጽሩ ብቸኛ ሐሳብ ኢየሱስ ሳያስጠነቅቅ የሚመጣ መሆኑ ነው::

ኢየሱስ ዳግም ምጽአቱን ለመግለጽ የታወቀውን ነቢያዊ ሐረግ ተጠቀመ:- «የጌታ ቀን» (ኢል 2፥11፤ አሞጽ 5፥18:20፤ሚል 4፥5):: ብሉይ ኪዳን ውስጥ እንኳ አይቀሬ መሆኑ ብዙ ጊዜ ተገልጾአል (ኢሳ 13፥6:9፤ ሕዝ 30፥3፤ ኢል 1፥15፤ 2፥1፤ 3፥14፤ አብ 1፥15፤ ሶፎ 1፥7:14):: እርግጥ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን መምጣት ነው:: ሁለት ውጤትንም ያስከትላል:: በመጀመሪያ ለእግዚአብሔር ታማኝ የነበሩት የእርሱን ጥበቃና ሽልማት ይቀበላሉ:: ታማኝ ያልነበሩት ደግሞ ክፉኛ ይቀጣሉ:: በብሉይ ኪዳን «የጌታ ቀን» ብዙ ጊዜ በአንድ ሕዝብ ላይ የሚደርሰውን ጊዜያዊ ቅጣት ያመለክታል:: በአዲስ ኪዳን ግን በመደበኛነት የሚያመለክተው የመጨረሻውን ፍርድ ነው (ከ1ቆሮ 5፥5፤ ከ2ጴጥ 3፥10 ጋር ያነ):: ስለዚህ የኢየሱስ የመመለሻና የፍርድ ቀን በአንድ ቀን የሚከናወኑ ብቸኛ ክሥተት ሆነው ተገልጸዋል::



## *ቍጥር 2:- እንደ ታማኝ አገልጋይ:- ኢየሱስ ይመጣል ከተባለበት ጊዜ ዘግይቶ ይመጣል*

45«በተገቢው ጊዜ ምግባቸውን እንዲሰጣቸው
ባለቤቱ በቤቱ ላይ የሾመው ታማኝና ብልኅ አገልጋይ
እንግዲህ ማነው? 46ባለቤቱ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ
የተጣለበትን ዐደራ እየፈጸመ የሚያገኘው ያ አገልጋይ የተባረከ ነው፤ 47እውነት
እላችኋለሁ፤ በንብረቱ ሁሉ ላይ ይሾመዋል:: 48ነገር ግን ያ አገልጋይ ክፉ ቢሆንና
ለራሱ፣ 'ጌታዬ ይዘገያል' በማለት 49ተነሥቶ ሌሎች አገልጋይ ባልንጀሮቹን መምታት
ቢጀምር፣ ከሰካራሞችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ፣ 50እርሱ ባልጠበቀው ቀንና ባላሰበው
ሰዓት ጌታው መጥቶ፣ 51ይቈራርጠዋል፤ ዕድል ፈንታውንም ከግብዞች ጋር
ያደርግበታል፤ በዚያም ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል::»

*ማቴ 24፥45-51*

[ቍ 45-51 = ሉቃ 12፥42-46፣ የክፍል 108ሐ ማብራሪያን ይመልከቱ]

ማቴዎስና ሉቃስ በተለየ ዐውድ ይሁን እንጂ ይህንኑ ምሳሌ ቃል በቃል[16] ይናገራሉ:: ሉቃስ ወንጌል ውስጥ ጴጥሮስ ምሳሌው የሚመለከተው እያንዳንዱን ሰው ወይም ልዩ የሆኑትን ጥቂቱን እንደ ሆነ ኢየሱስን በመጠየቅ ምላሹን ያሰማል:: በሌላ አነጋገር ጴጥሮስ የተለየ መብትን ስለ ማግኘት ይጠይቃል:: ኢየሱስ ጴጥሮስን በመገሠጽ ስለ ጴጥሮስ ልዩ ኀላፊነቶች ይናገራል:: ይሁን እንጂ እዚህ ላይ ስለ መዘጋጀት የተደረገውን ያህል በኀላፊነት አጽንዖት አልተደረገም::

ሳምንታት ወደ ወሮች፣ ወሮችም ወደ ዓመታት በተሻገሩ ቍጥር አገልጋይ ተታሎ ከኀላፊነቱ በቀላሉ ከኃላፊነቱ ይዘናጋል::

---

16 በግሪኩ ቅጅ ከ102 ቃላት ውስጥ ሆሄ ከሆሄ ተመሳሳይ ያልሆኑት ቃላት 14 ብቻ ናቸው:: ስድስት ተመሳሳይ ቃላት ናቸው:: አምስቱ ደግሞ የተለየ የግስ ጊዜያት አላቸው:: አንዱ የሚጠቀምባቸው ሌላው ጸሐፊ ግን የማይጠቀምባቸው ቃሎች ግን ሦስት ብቻ ናቸው::

የንብረቱ ጌታ ረጅም ጊዜ በቆየ ቊጥር በሚቀጥለው ቀን ሲመለስ ይችላል የሚለው ግምት እየራቀ ይሄዳል:: ርግጡ ግን ተቃራኒው ነው:: ተመልሶ ይመጣል:: ሰዓቱ ጊዜውን ጠብቆ በተጓዘ ቊጥርም መመለሻው እየቀረበ ይመጣል::

### *ቊጥር ፫:- እንደ ዝንጉዎች/አስተዋዮች ደናግል:- ኢየሱስ ከታሰበው ፈጥኖ ይመጣል*

ማቴ 25÷1-5

[1]«በዚያን ጊዜ መንግሥተ ሰማያ መብራታቸውን የዘው ሙሽራውን ሲቀበሉ የወጡ ዐሥር ቈጃገረዶችን ትመስላለች:: [2]ከእነርሱም አምስቱ ቈጃገረዶች ዝንጉዎች፣ አምስቱ ደግሞ አስተዋዮች ነበሩ፤ [3]ዝንጉዎቹ መብራት ይዘው መጠባበቂያ ዘይት አልያዙም ነበር:: [4]አስተዋዮቹ ግን ከመብራታቸው ጋር መጠባበቂያ ዘይት በማሰሮ ይዘው ነበር:: [5]ሙሽራው በዘገየ ጊዜ፣ ሁሉም እንቅልፍ ተጫጫናቸውና ተኙ::»

መሲሕን ከሙሽራ ጋር ማነጻጸሩ የተለመደ ነበር (ኢሳ 54÷4-6፤ 62÷4-5፤ ሕዝ 16÷7-34፤ ሆሴ 2÷19፤ ከዮሐ 3÷27-30፤ ከማቴ 9÷15፤ ከማር 2÷19-20 ጋር ያነ):: ይህ የፍልስጥኤማውያውን ጋብቻ መደበኛ ሥዕል ነው:: በሙሽራዋ ቤት የጋብቻ ሥነ ሥርዐት ከተፈጸመ በኋላ ወደ ሙሽራው በሚያመራውና ትልቅ ድግስ በተዘጋጀበት ቤት መንገድ ላይ ሰልፍ ይኖራል:: ሙሽራውንና ሰልፉን መጠባበቅ የሙሽሪት ሚዜዎች ተግባር ነበር:: ነገር ግን ያ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ማንም ከቶ አያውቅም:: ምሽት ላይ ስለሚሆን ፋኖስ ይዘው ይሄዱ ነበር:: እነዚህ ፋኑሶች ከሸክላ የተሠሩ ሲሆኑ፣ የክብ አጋማሻቸው ሦስት ኢንች ሆኖ መያዣ ይሆን ዘንድ በአንድ ጐን የተሰረጐዱ ነበሩ:: እነዚህ ፋኖሶች የሚይዙት አንድ የምግብ ዘይት



ማንኪያ ያህል ነው:: ስለዚህ ሙሽራው የሚዘገይ ከሆነ መጠባበቂያ ዘይት መያዝ አስፈላጊ ነበር::

ማስጠንቀቂያ:- ይህ ምሳሌ በግል ለራስ ለሚሰጥ መልስ ሲባል በርከት ያሉ ዝርዝሮች አሉት:: ስለዚህ እንድምታ (ውስጠ ወይራ) አለው ተብሎ መታሰብ የለበትም:: (1) አምስቱ አስተዋዮች ሲሆኑ አምስቱ ደግሞ ዝንጉዎች ነበሩ:: ይህ ማለት ግን ኢየሱስ ሲመለስ ከቤተ ክርስቲያን አባቶች ውስጥ ኀምሳ መቶኛው ከእርሱ ጋር አይሄዱም ማለት አይደለም:: (2) ሁሉም ተኝተው የነበሩ መሆናቸው እምነታቸውን ያጐደሉ ወይም «ወደ ኋላ ያፈገፈጉ» መሆናቸውን አያመለክትም:: እነዚህ ሚዜዎች ሙሽራውን ወደ ትልቁ ድግስ አጅበው እንዲሄዱ ታስበው ነበር:: በመሆኑም እርሱን ሲጠባበቁ ሳለ እንቅልፍ እንዲያሸንፋቸው አልተጠበቀባቸውም:: መረሳት የሌለበት ጉዳይ እነዚህ የሙሽሪት ሚዜዎች እንጂ የሮም ወታደሮች አልነበሩም:: (3) ሴት ሚዜዎቹ «ደናግል» ነበሩ:: ይህ የቤተ ክርስቲያንን ንጽሕና በትእምርትነት እንዲያሳይ አልታቀደም:: በዚያን ዘመን የነበሩት ያላገቡ ሴቶች በወሲብ ድርጊት አይታሙም ነበር:: ስለዚህ «ድንግል» የሚለው ቃል «ወጣት ሴት» ከሚለው ጋር አቻነት አለው:: (4) አምስቱ በማሰሮ ዘይት ይዘው ነበር:: ይህ መንፈስ ቅዱስን አይወክልም:: አንዳንዶች የአምስቱን አስተዋይ ሴቶች ግልጽ ራስ ወዳድነት ለማሳየት ሲሉ ይህን ምሳሌ ተጠቅመውበታል:: ዘይት መንፈስ ቅዱስን የሚወክል ከሆነ፣ ሌሎቹ «መንፈሳቸውን» በእርግጥ አላካፈሉም:: ምክንያቱም ይህ የሚቻል ነገር አይደለም:: የያዙትን ዘይት ግን ማካፈል ይችሉ ነበር:: ይህ ምሳሌውን ከሚገባው በላይ መተርጐም ነው:: የምሳሌው ሐሳብ የሚከተለው ነው:- ለኢየሱስ መምጣት መዘጋጀት አለብህ:: ተዘጋጅተህ ከሆነ አስተዋይ ነህና ከኢየሱስ ጋር ለመሄድ ተዘጋጅ:: ያልተዘጋጀህ ከሆነ፣ ዝንጉ ነህና ከኀብረቱ ታግደሃል (ዕድል ፈንታ እንዳይኖርህ ተደርገሃል)::

ማቴ 25፥6-13

6«እኩለ ሌሊት ላይ፣ 'ሙሽራው እየመጣ ነው፤
ወጥታችሁ ተቀበሉት!' የሚል ጥሪ ተሰማ።
7«በዚህ ጊዜ ልጃገረዶቹ ሁሉ ተነሥተው መብራቶቻቸውን እየተረኰሱ
መዘጋጀት ያዙ። 8ዝንጉዎቹ ለለተዋዮቹን፣ 'መብራታችን ሊጠፋብን ስለሆነ፣
ከዘይታችሁ ስጡን' አሏቸው።
9«ለለተዋዮቹ ልጃገረዶች ግን መልሰው፣ 'ያለን ዘይት ለእኛም ለእናንተም
ሳይበቃ ስለሚችል ሄዳችሁ ከሻጮች ለራሳችሁ ግዙ' አሏቸው።
10«ዘይት ሊገዙ እንደ ሄዱ፣ ሙሽራው መጣ፤ ተዘጋጅተው የነበሩት
ልጃገረዶችም ወደ ሰርጉ ግብዣ አብረውት ገቡ፤ በሩም ተዘጋ።
11«ዘግየት ብለው ሌሎቹ ልጃገረዶች መጥተው፣ 'ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤
በሩን ክፈትልን' አሉ።
12«እርሱ ግን መልሶ፣ 'እውነት እላችኋለሁ፤ አላውቃችሁም' አላቸው።
13«እንግዲህ ቀኑን ወይም ሰዓቱን ስለማታውቁ ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ።»

እኩለ ሌሊት ላይ ሙሽራው በመምጣት ላይ መሆኑን በሚያስታውቅ ጥሪ ዐሥሩ የሴት ሚዜዎች ተቀሰቀሱ (ከማቴ 24፥31፤ ከ1ቆሮ 15፥52፤ ከ1ተሰ 4፥16 ጋር ያነ)። ከእንቅልፋቸው ነቅተው ሰውነታቸውን ካፍታቱ በኋላ መብራታቸውን ለማብራት ክሩን ኰስተሩት። «ዝንጉዎቹ አምስቱ» ብርሃኑን ለመጨመር ክሩን ወደ ውጭ አወጡት። ሆኖም በዘይት መያዣው ውስጥ የቀረውን ዘይት አሟጠጠባቸው። ዘይታቸውን ያካፍሏቸው ዘንድ «አምስቱን ባለዘይቶች» ለመኗቸው። ነገር ግን ሙሽራው ሊደርስ የተቃረበ ስለሆነና ያልታሰበ መስተንጐልም በመንገድ ላይ ሊያጋጥመው ስለሚችል ለዝንጉዎቹ ቢሰጧቸው ይህ ያላቸውን ዘይት ሊያሟጥጥባቸው ይችላል። ስለዚህ አስተዋዮቹ ደናግል አንስጥም



አሉ። ከዚህ ይልቅ የራሳቸውን ዘይት እንዲገዙ «አምስቱን ዝንጉዎች» በአካባቢ ወደሚገኘው ነጋዴ ላኳቸው።

አምስቱ ዝንጉዎች መጠነኛ ዘይት ለመግዛት በመርበትበት ተጣደፉ። ብዙ ጊዜ ሡቆች ዝግ ናቸው። ሆኖም በማኅበረ ሰቡ ውስጥ ትልቅ የጋብቻ ድግስ ሲኖር፣ ቤተ ሰቡ ለሚፈልገው ነገር አገልግሎት ለመስጠት ሲባል ትንሽ ሡቃቸውን ክፍት ያደርጋሉ። እዚህ ላይ የምናወሳው ስለ ትልቁ የንግድ ድርጅት ሳይሆን፣ ስለ መለስተኛ የቤተ ሰብ የንግድ ድርጅት መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል።

ነገር ግን አምስቱ ዝንጉዎች በተመለሱ ጊዜ ሙሽራው ደርሷል፤ አምስቱን ሚዜዎች በመያዝም ወደ ቤቱ ገብቶ በሩን አስዘጋ። አምስቱ ዝንጉዎች በሩን በማንኳኳት ወደ ቤት ይገቡ ዘንድ ለመኑ። ሙሽራው ግን፣ «ከዚህ ሂዱ፤ ከቶ አላውቃችሁም» አለ። እነዚህ ምስኪን ልጃገረዶች ዘይት ለማግኘት ወደ ሡቅ ከመጣደፋቸው አኳያ ሲታይ፣ ይህ ጭካኔ የተመላበት ድርጊት ሊመስል ይችላል። ይህ ኢየሱስ ለሐሰተኞች ነቢያት ከሰጣቸው የተስፋ ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው (ማቴ 7፥23)። አለመዘጋጀታቸው ፍቅር የሌላቸው መሆናቸውን ያሳያል።

## *ቍጥር 4፡- የሀብት ዐደራ እንደ ተሰጣቸው አገልጋዮች*

ከአምስት ቀን ቀደም ብሎ ከኢያሪኮ ወደ ቢታንያ በመጓዝ ላይ እያለ (ሉቃ 19፥11-27፤ ክፍል 127ለን ይመ) እንደ ተናገረው ይህ ምሳሌ በጣም አስፈሪ ነው። ልዩነቱ ሉቃስ ወንጌል ውስጥ የሚገኘውን ምሳሌ ኢየሱስ የተናገረው የእግዚአብሔር መንግሥት እነርሱ እንደሚያስቡት አይቀሬ አለመሆኑን ለማስጠንቀቅ ነው (ሉቃ 19፥1)። ይሁን እንጂ ማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ያን መንግሥት ይጠባበቁ ዘንድ ይህ ምሳሌ ያስጠነቅቃል።

መለስተኛ የሆኑ ሌሎች ልዩነቶች አሉ:-

| ሉቃስ 19፥11-27 | ማቴዎስ 25፥14-30 |
|---|---|
| ወደ ኢየሩሳሌም መቃረብ | ኢየሩሳሌምን ለቆ መሄድ |
| 10 አገልጋዮች ለእያንዳንዳቸው አንዳንድ ምናን ተሰጣቸው | ሦስት አገልጋዮች ለአንዱ 5፣ ለሌው 2፣ ለሦስተኛውም 1 ታላንት ተሰጣቸው |
| ንጉሥ የሚሆነውን ሰው ሰዎቹ ጠሉት | ሌሎች ተዋንያን (ገጸ ባሕርያት) ተልተጠቀሱም |
| ንጉሥ | ሀብታሙ ሰው |
| በትርፍነት ለተገኘው ለእያንዳንዱ ምናን እያንዳንዱ አገልጋይ አንዳንድ ከተማ ተሰጠው | ልዩ ሽልማት አልተጠቀሰም (የተጠቀሰ ልዩ ሽልማ የለም) |
| የመጨረሻው አገልጋይ ገንዘቡን «በጨርቅ» ጠቅልሎ አስቀመጠ | የመጨረሻው አገልጋይ ገንዘቡን ጉድጓድ ውስጥ ቀበረ |

ነገር ግን ተመሳሳይነታቸው ከልዩነታቸው ይልቅ ሚዛን ይደፋል:-

1. የመጨረሻው አገልጋይ ገንዘቡን ለትርፍ ከማስቀመጥ ይልቅ ቀብሮ ደበቀው::
2. «... 'ደግ አድርገሃል፤ አንተ መልካም ታማኝ አገልጋይ፤ በትንሽ ነገር ላይ ታማኝ ስለ ሆንህ በብዙ ነገር ላይ እሾምሃለሁ፤ ... '»::
3. ክፉዎቹ አገልጋዮች ስለ ንብረት ለጌታቸው የሰጡት ግምት ተመሳሳይ ነው::
4. ቀሪው ገንዘብ ብዙ ላተረፈው አገልጋይ ተሰጠ::
5. «ላለው ይጨመርለታል::»



6. ሁለቱም ምሳሌዎች የተደመደሙት በፍርድ ነው::

እነዚህ ተመሳሳይነቶች ማቴዎስና ሉቃስ የኢየሱስን ቃል እንዳለ ከመጻፍ ይልቅ አርታዒዎች መሆናቸውን አያመለክቱም:: ኢየሱስ ምሳሌውን የተናገረው ሁለት ጊዜ ነው ብሎ ማሰቡ በጣም ያስኬዳል:: ለምላሽ ንግግር ሲባልና ለተደራስያኑ በማሰብም ዝርዝር ጉዳዮችን ለውጧቸዋል::

> [14]«የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋዮቹን ጠርቶ ያለውን ንብረት በአደራ በመስጠት ወደ ሌላ አገር ሊሄድ የተነሣ አንድ ሰውን ትመስላለች፤ [15]ለእያንዳንዱ እንደ ችሎታው በመደልደል ለአንዱ አምስት ታላንት፣[ሀ] ለሌላው ሁለት፣ ለሌላው ደግሞ አንድ ታላንት ሰጥቶ ጉዞውን ቀጠለ:: [16]አምስት ታላንት የተቀበለው ሰውዬ ወዲያው በገንዘቡ ንግድ ጀምሮ አምስት ታላንት አተረፈ፤ [17]እንዲሁም ሁለት ታላንት የተቀበለው ሁለት አተረፈ፤ [18]አንድ ታለንት የተቀበለው ግን መሬት ቆፍሮ የጌታውን ገንዘብ ደበቀ::»

ማቴ 25፥14-18

*[ሀ15] አንድ ታለንት በሺህ የሚቆጠር ብር የሚያህል ነው::*

የአገልጋዮቹ ጌታ ለአገልጋዮቹ ምን ያህል ገንዘብ እንደ ሰጣቸው በርግጠኝነት ማወቁ አስቸጋሪ ነው:: አንዱ ምክንያት ታላንት የክብደር መለኪያ እንጂ ጥሬ ገንዘብ አልነበረም:: ወርቅ፣ ብር ወይም ነሐስ ባለህ መጠን የታላንቱ ዋጋ በእጅጉ ይለያያል:: ማለት የምንችለው ይህ ብዙ ሊሠራበት የሚቻል አያሌ ገንዘብ መሆኑን ነው::

ኢየሱስ «ታላንት» በሚለው ቃል በተጠቀመ ጊዜ አድማጮቹ ያሰቡት ስለ ገንዘብ ብቻ ነው:: እኛ ታላንት የሚለውን ቃል ስንጠቀም አድማጮቻችን የሚያስቡት ስለ ኪሀልና ስለ ስጦታ ነው:: በዚህ መልኩ ካየነውም ምሳሌውን አልተገነዘብነውም ማለት ነው:: ይህ

እንዳለ ሆኖ በምሳሌው ውስጥ የገንዘብ ምሳሌ እግዚአብሔር የሰጠንን ሀብት ሁሉ የሚመለከት ሲሆን፣ ገንዘባችንን፣ ችሎታችንን፣ ጊዜያችንንና ያለንን ዕድል ሁሉ፣ ወዘተ የሚመለከት ነው።።

እያንዳንዱ አገልጋይ የተሰጠው እንደ ችሎታው ነበር። የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ዐደራ ከተሰጣቸው 100% በማትረፍ ከዚህ ቀደም የነበራቸውን ዝናና መልካም ሥራ አስመሰከሩ። የመጨረሻው አገልጋይ ሙከራ ለማድረግ እንኳ አልፈለገም። ሙከራ በማድረግ ፈንታ በጓሮው ጉድጓድ ቈፍሮ ገንዘቡን ቀበረው።

ማቴ 25÷19-23

[19]«የአገልጋዮቹም ጌታ ከብዙ ጊዜ በኋላ
ከሄደበት ተመልሶ የሰጣቸውን ገንዘብ ተሳሰበ።
[20]አምስት ታላንት የተቀበለውም፣ ሌላ አምስት ተጨማሪ
ታላንት ይዞ በመቅረብ፣ 'ጌታ ሆይ! አምስት ታላንት
ዐደራ ሰጥተኸኝ ነበር፤ ይኸውልህ አምስት ታላንት
አትርፌአለሁ' አለው።
[21]ጌታውም፣ 'ደግ አድርገሃል፤ አንተ መልካም ታማኝ አገልጋይ፤ በትንሽ
ነገር ላይ ታማኝ ስለ ሆንህ በብዙ ነገር እሾምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ' አለው።
[22]«እንዲሁም ሁለት ታላንት የተቀበለው አገልጋይ ቀርቦ፣ 'ጌታ ሆይ፤ ሁለት
ታለንት ሰጥተኸኝ ነበር፤ ይኸው ሁለት ተጨማሪ ታለንት አትርፌአለሁ' አለው።
[23]«ጌታውም 'ደግ አድርገሃል፤ አንተ መልካም ታማኝ አገልጋይ፤ በትንሽ
ነገር ላይ ታማኝ ስለ ሆንህ በብዙ ነገር ላይ እሾምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ'
አለው።»

[ቍ. 19-23 = ሉቃ 19÷15-18 የክፍል 127ለ ማብራሪያን ይመልከቱ]



ቀደም ሲል በተመለከተው በዚህ ምሳሌ ትረካ እንደታየው፣ የአገልጋዮቹ ጌታ ታማኝ አገልጋዮቹን ሀብት በሀብት አደረጋቸው።

ማቴ 25÷24-30

[24]«አንድ ታላንት የተቀበለው አገልጋይ ቀርቦ፣
'ጌታ ሆይ፤ አንተ ካልዘራህበት የምታጭድ፣
ካልበተንህበትም የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን
ዐውቃለሁ፤ [25]ስለዚህ ፈራሁህ፤ ሄጄም መሬት ቈፍሬ
ታላንትህን ጕድጓድ ውስጥ ደበቅሁት፤ ገንዘብህ
ይኸውልህ' አለው።
[26]«ጌታውም መልሶ፣ 'አንተ ክፉ፣ ሰነፍ አገልጋይ፤ ካልዘራሁበት የማጭድ፣
ካልበተንሁበትም የምሰበስብ መሆኔን ታውቅ ኖርሃል? [27]ታዲያ፣ በምመለስበት ጊዜ
ገንዘቤን ከነወለዱ እንዳገኘው ለለዋጮች መስጠት ይገባህ ነበር።
[28]«'በሉ እንግዲህ ታላንቱን ውሰዱበት ዐሥር ታለንት ላለው ስጡ፤ [29]ላለው
ይጨመርለታል፤ የተትረፈረፈም ይኖረዋል፤ ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳ
ይወሰድበታል። [30]ይህን የማይረባ አገልጋይ ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወደበት በውጭ
ወዳለው ጨለማ አውጥታችሁ ጣሉት' አለ።»


[ቍ. 24-30 = ሉቃ 19÷20-27፣ የክፍል 127ለ ማብራሪያን ይመልከቱ]

ይህ ክፉ አገልጋይ ጌታውን መፍራቱን በተናገረ ጊዜ ዋሽቷል። ጌታውን በእውነት ቢፈራ ኖሮ፣ ገንዘቡ ትርፍ ያስገኝ ዘንድ ለገንዘብ አበዳሪ ይሰጥ ነበር። እውነቱ ግን ጌታው አየመለስም ብሎ በሙሉ ልብ ተማምኖ ነበር። ገንዘቡን የቀበረበት ምክንያት፣ በኋላ ቈፍሮ በማውጣት ለራሱ ጥቅም ለማዋል ነው! ይህ ደግሞ ያልታሰበ ዕዳ አመጣበት፤ ጌታው በተመለሰ ጊዜ ይህ አገልጋይ የእጁን አገኘ (ቍ. 30)። Steinmetz እንዲህ ይላል:-

በሰነፉ አገልጋይ ላይ የተላለፈው ፈጣን ፍትሕ፣ ዐመፀኞችና እምነታቸውን ያጐደሉት ሁሉ የእግዚአብሔርን ቸርነት ወይም የመለኮትን ርኅራኄ እንደ ቀላል ነገር በመቍጠር፣ ወደ መንግሥተ ሰማይ እንገባለን የሚሉትን ሰዎች ሐሳብ ከንቱ የሚያደርግ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቸርነት እንዲህ ባለ የቂል አስተሳሰብ ቀድሰናን ችላ አይልም፡፡ መለኮታዊ ርኅራኄ በደልን ይቅር ይላል፤ ሆኖም ማናቸውንም በደል አያበረታታም፡፡[17]

የኢየሱስ ዳግም ምጽአት ብዙ ዘመን የቆየ ቢሆንም እንኳ፣ ተመልሶ ይመጣል፡፡ በመጣ ጊዜም በመጋቢነት በተሰጠን ሕይወት ምን እንደ ሠራን ለእርሱ አንገልጻለን፡፡ ለዳግም ምጽአቱ በደንብ የተዘጋጁት በሽልማታቸው ሐሤት ያደርጋሉ፡፡ ዘግይቷልና ከእንግዲህ ነገ ወይም ከነገ ወዲያ አያመጣም እያሉ የኖሩት ድንጋጤ ይገባቸዋል፤ ይፈረድባቸዋል፤ ክፉኛ ይቀጣሉ፡፡

**§ 139ለ**
**ፍርድ በዳግም ምጽአት**
**ቴ 25÷31-46)**

ይህ ምንባብ ስለ ኢየሱስ መመለስ የሚናገሩትን ተከታታይ ምሳሌዎች ይደመድማል፤ ሙሉውን የደብረ ዘይት ትምህርትም ይቋጫል፡፡ ቀደም ያሉትን ምሳሌዎች መሠረታዊ የሆነውን ዋና ነገርም ይጋራል፡፡ ተዘጋጅ . . . ኢየሱስ ተመልሶ ይመጣል! ይህ ራሱ ምሳሌ ባይሆንም እንኳ ትዕይንት ነው፡፡ ክርስቶስ ሲመለስ እውን የሚሆነውን የፍርድ ረቂቅ ንድፍ የያዘ ይመስላል፡፡ በጎችና ፍየሎች ጻድቃንና ክፉዎችን የሚወክሉ

[17] D.C. Steinmetz, "Mt 25:14-30," *Int* 34 (1980): 172-176.



ዘይቤዎች ናቸው፡፡ ቀሪው ክፍል ግን የሚመጣው ፍርድ ፖራቦላዊ አጕልቶ ማሳያ ሳይሆን እውናዊ ገለጻ ነው፡፡

**ማቴ 25÷31-33**

31«የሰው ልጅ ከመላእክቱ ሁሉ ጋር በክብሩ
ሲመጣ፣ በክብሩ ዙፋን ላይ ይቀመጣል፤ 32ሕዝቦች ሁሉ
በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እርሱም፣ እረኛ በጎችን ከፍየሎች እንደሚለይ ሕዝቡን አንዱን
ከሌላው ይለያል፤ 33በጎቹን በቀኙ፣ ፍየሎቹን ግን በግራው ያቆማቸዋል፡፡

ይህ የእረኝነትን ምስያ በመጠቀም የፍርዱን ምንነት የሚሳይ ቍልጭ ያለ ሥዕል ነው፡፡ የበግና የፍየል መንጋ ለአዳር በአንድ በረት መታጐሩ ወይም ቀን ሲሆን መንጋው በአንድ ላይ እንዲግጥ መደረጉ የተለመደ ነበር፡፡ ሆኖም የሚለዩበት ጊዜ ነበር (ለምሳሌ ውድ የሆነው ጠጕር ከበጉ በሚሸለትበት ጊዜ)፡፡ እነዚህ ውበት የሌላቸው እንስሳት በመጠኑ አንድ ዐይነት ቢመስሉም አንኳ፣ በጠባያቸውና በፋይዳቸው ረገድ ትልቅ ልዩነት አላቸው፤ ልዩነታቸው ጕልሕ ነው፡፡ እንደዚሁም ማን የኢየሱስ እንደ ሆነና ማንስ የኢየሱስ እንዳልሆነ ፍርድ ግልጽ ያደርገዋል፡፡[18]

**ማቴ 25÷34-40**

34«በዚያን ጊዜ ንጉሡ በቀኙ በኩል ያሉትን
እንዲህ ይላቸዋል፤ 'እናንተ አባቴ የባረካችሁ ኑ፤ ዓለም

[18] ቍጥር 31 ራእይ 19÷11-18ን፣ ቍጥር 32 ደግሞ ራእይ 20÷11-15ን ያስታውሰናል፡፡ ልዩነቱ ዳግም ምጽአትን ከፍርድ ቀን ስለሚለየው የአንድ ሺህ ዓመት ክፍተት (ራእ 20÷1-10) ማቴዎስ ምንም አለማለቱ ነው፡፡ ስለዚህ በማቴዎስ 25÷31 እና በቍጥር 32 መካከል አንድ ሺህ ዓመትን አካትተን እናስቀምጥን? አስፈላጊ አይመስልም፡፡ ማቴዎስና 2ጴጥሮስ 3÷10-13 (ሁለቱም ከዮሐንስ ራእይ ይልቅ አነስ ባለ መልኩ ተምሳሌታውያን ናቸው) ለመጨረሻው ጊዜ ያቀረቡት ግልጽ የሆነውን የጊዜና የሁኔታ ቅደም ተከተል ነው፡፡ ኢየሱስ መጣ፤ ምድር ጠፋች፤ ፍርድም ተከትሎ መጣ፡፡ የዮሐንስ ራእይን አስመልክቶ በተለይ ይህ ጥያቄያችንን ሁሉ አጥጋቢ በሆነ መልኩ ባይመልስም እንኳ፣ ኢየሱስና ጴጥሮስ ያሉትን አንብቦ ለመረዳት ቀላሉ መንገድ ይኸው ይመስላል፡፡

ከተፈጠረ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ፤ 35 ምክንያቱም ተርቤ
አብልታችሁኛል፤ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛል፤ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛል፤ 36 ታርዤ
አልብሳችሁኛል፤ ታምሜ አስታምማችሁኛል፤ ታስሬ ጠይቃችሁኛል።'

37 «ጻድቃንም መልሰው እንዲህ ይሉታል፤ 'ጌታ ሆይ፤ ተርበህ አይተን መቼ
አጠጣንህ? 38 እንግዳ ሆነህ አይተን መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ
አለበስንህ? 39 እንዲሁም ታመህ ወይም ታስረህ አይተን መቼ ጠየቅንህ?'

40 «ንጉሡም መልሶ፣ 'እውነት እላችኋለሁ፣ ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት
ወንድሞቼ ለአንዱ ያደረጋችሁት፣ ለእኔ እንዳደረጋችሁት ነው' ይላቸዋል።»

አንድ ሰው በግ ወይም ፍየል ይሁን ማን ነው የሚወስነው? እንደ ማንኛውም የአዲስ ኪዳን የፍርድ ትዕይንት ፍርድ የሚሰጠው እንደየሥራው ነው (ማቴ 16÷27፤ ዮሐ 5÷28-30፤ ሮሜ 2÷5-11፤ 2ቆሮ 5÷10፤ 1ጴጥ 1÷17፤ ራእ 20÷11-15)። ይህ ጉዳይ ድነት በጸጋ ነው ከሚለው ጋር የሚጣረስ ነውን? አንድ ሰው በጸጋ ድኖ በሥራ እንዴት ሊፈረድበት ይችላል? እንግዲህ ይህ በቀላሉ እንዲህ ነው፦ በክርስቶስ የፍርድ ዙፋን ፊት ስንቀርብ ብቸኛው ዐይነተኛ ጉዳይ ከእርሱ ጋር ያለን ግንኙነት ነው እርሱን አምነነዋልን? (ይኸውም በእርሱ ላይ እምነታችንን ጥለናልን)? ለዚህ ጥያቄ መልሱ ንግግራችን ሳይሆን አካሄዳችን ነው። አኗኗራችን የምናምነው ጉዳይ ምን መሆኑን በርግጠኝነት የሚነገርበት መንገድ ነው። መልካም ሥራችን ሁሉ .. ድነንም፤ ቀዳሚ ተልእኮአችንን በሚገባ መፈጸማችንን ወይም አለመፈጸማችንን በጉልሕ ይገልጻል እንጂ።

ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱ መደበኛ መለኪያ የሆኑትን ስድስት (ተግባራት) ጉልሕ ያደርጋል። እነዚህ የሚያከናውኗቸውን ነገሮች ሁሉ ያካተቱ አይደሉም። የሚያከናውኗቸው ነገሮች ምንነት መግለጫዎች ናቸው። የሰው ዘር መሠረታዊ ፍላጎቶች በዕጥርታ መልክ በትክክል



ያሳያሉ፤ እነርሱም ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያና ተቀባይነት ናቸው። እነዚህን ስድስት ጠባያት ስንተነትን ሳለ የግል ጊዜንና የግል ገንዘብን በእጅጉ እንደሚጠይቁ እንገነዘባለን። እነዚህ ሁለቱ ደግሞ ለብዙዎቻችን እጅግ ውድ የሆኑ ነገሮች ናቸው።

በጎቹ ደንግጠዋል፤ የደነገጡት መንግሥተ ሰማይን በመውረሳቸው ሳይሆን በጭንቅ ጊዜው (በመከራ ጊዜው) በግላቸው ንጉሡን በማገልገላቸው ነው። እርሱን አላወቁትም። ኢየሱስ ለምን እንደ ሆነ ይገልጻል። እርሱን በግሉ አላገለገሉትም። የድኾችንና የጠፉትን ሰዎች ፍላጎት ባሟሉ ጊዜ ኢየሱስ ለእርሱ እንደ ተደረገለት ቈጠረው። «ታናናሽ ከሆኑት ወንድሞቼ» የተባሉት ደቀ መዛሙርት ናቸው ወይስ አይደሉም የሚል ክርክር አለ።[19] ኢየሱስ ለሰው ሁሉ በተለይም ለክርስቲያኖች ቸርነት እንድናደርግ ይፈልግብናል (ገላ 6÷10)።

41 «ከዚያም በግራው በኩል ላሉት ደግሞ
እንዲህ ይላቸዋል፤ 'እናንተ የተረገማችሁ፤ ለዲያብሎስና
ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው የዘላለም እሳት ከእኔ
ተለይታችሁ ሂዱ፤ 42 ምክንያቱም ተርቤ አላበላችሁኝም፤ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝም፤
43 እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝም፤ ታርዤ አላለበሳችሁኝም፤ ታምሜና ታስሬ
አልጠየቃችሁኝም።'

ማቴ 25÷41-46

[19] ከአንድ ሰው «ልዩ » አተያይ አኳያ ጉዳዩን በግልጽ ለማስተዋል፣ G. Foster, "Making Sense of Matthew 25:31-46," *SBET* 16/2 (1998): 128-139 ይመልከቱ። ይሁን እንጂ J.P. Heil ከአንባቢ አኳያ ጉዳዩን በማየት ሁለቱም ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ በማለት አሳማኝ ክርክር ያቀርባል፣ "The Double Meaning of the Narrative of Universal Judgement in Matthew 25:31-46," *JSNT* 69 (1998): 3-14. ፍየሎች በሮማውያን ዘንድ አሉታዊ ፍካሬ (ትርጓሜ) ኖሯቸው ለየቅል ቢሰማሩም እንኳ፣ ሁለቱ ሁኔታው በፍልስጥኤማውያን ዘንድ በዚያ መልኩ አይታይም። ፍየሎችና በጎች «የተከበሩ» እንስሳት ነበሩ። ከK. Weber, "The Image of Sheep and Goats in Mt. 25:31-46," *CBQ* 59/4 (1997): 657-678 ጋር ያነጻጸሩ።

44«እነርሱም መልሰው፣ 'ጌታ ሆይ፤ ተርበህ ወይም ተጠምተህ እንግዳ ሆነህ ወይም ታርዘህ፣ ታመህ ወይም ታስረህ ለይተን መቼ አልደረስንልህም' ይሉታል።

45«በዚያን ጊዜ እርሱም መልሶ፣ 'እውነት እላችኋለሁ፣ ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት ወንድሞቼ ለአንዱ ለማድረጋችሁ፣ ለእኔ እንዳላደረጋችሁት ነው' ይላቸዋል።

46«እነዚህም ወደ ዘላለም ፍርድ፣ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።»

ፍየሎች ከሰይጣንና ከመላእክቱ ጋር ወደ ሲኦል ተጣሉ።[20] የተቀጡት ክፉ ሥራ በመሥራታቸው ሳይሆን መልካሙን ነገር ሳያደርጉ በመቅረታቸው ነው። ይህ የሆነው ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት «መክፈል የሚገባቸውን» ባለመክፈላቸው ሳይሆን፣ ወደ መንግሥተ ሰማይ መግቢያ ብቸኛ መንገድ የሆነውን ኢየሱስን ከልብ አለመከተላቸውን አካሄዳቸው ስለሚመሰክርባቸው ነው።

ኢየሱስም ቀደም ሲል ክፉ ከሆኑት የሰዶምና የገሞራ ሰዎች (ማቴ 10÷15)፣ የጢሮስና የሲዶና (ማቴ 11÷22:24፤ ሉቃ 10÷14) የነነዌም ሰዎች (ማቴ 12÷41፤ ሉቃ 11÷32) እንዲሁም ንግሥተ ሳባ (ማቴ 12÷42፤ ሉቃ 11÷31) እስራኤል ጌታ ኢየሱስን ባለመቀበላቸውና ምልክት በመጠየቃቸው በፍርድ ቀን እንደሚቆሙና በእነርሱ ላይ እንደሚመሰክሩባቸው ተናግሮአል። ይህ ለአይሁድ አሳፋሪ ጉዳይ ነው። ይህ ጽሑፍ ያን የአስደንጋጭነት መንፈስ አዝሎአል። እነዚህ ፍየሎች የሚሰሙትን ማመን አለቻሉም፤ ምክንያቱም (1) ኢየሱስ ፈራጅ ዳኛ የመሆኑን ሐቅ አልተቀበሉም (ዮሐ 5÷22:30፤ 9÷39)፣ እንዲሁም (2)

---

[20] እግዚአብሔር የራሱ መላእክት አሉት፤ የእርሱ ተፎካካሪ የሆነው ሰይጣንም የራሱ መላእክት አሉት ብለን በዚህ ጥቅስ የተነሣ ግራ መጋባት የለብንም። እግዚአብሔር በባሕርዩ ከመላእክቱ ልዩ ነው። ይኸውም እርሱ ፈጣሪ ነው፤ እነርሱ ደግሞ ፍጡራን ናቸው። ሰይጣን ግን በባሕርዩ ከተከታዮቹ/ከመላእክቱ ጋር እኩል ነው። ሁለቱም እግዚአብሔር የፈጠራቸው ናቸው፤ በመጨረሻም ለእግዚአብሔር ይገዛሉ።



የዚያን ፍርድ እውነተኛነትና ፍጹምነት የተመለከቱት አቃለው ነው (ማቴ 12÷36፣ ቃሎች፤ ሮሜ 2÷16፣ ሐሳብ፤ እና 1ቆሮ 4÷3-5 አነሣሽ ምክንያቶች)።

**§ 140**
**ለኢየሱስ ሕማማት ዝግጅት፡- ኢየሱስና ካህናቱ**
**(ማቴ 26÷1-5፤ ማር 14÷1-2፤ ሉቃ 22÷1-2 § 131 ላይ ከሉቃ 21÷37-38 ጋር ያነ)**

ይህ የመጨረሻው መጀመሪያ ነው። ለዚህ ለመጨረሻው ትዕይንት ልዩ ልዩ ተዋንያን ስፍራ ስፍራቸውን ሲይዙ እናያለን። በዚህ ክፍል አንድ የመጨረሻ ሕማም እውን እንደሚሆን ኢየሱስ አስቀድሞ ይናገራል። የአይሁድ ገዦች የኢየሱስን መያዝና ግድያ በማሤር የበኩላቸውን ዝግጅት አደረጉ። በሚቀጥሉት ሁለት ክፍሎች ለቀብር እንደሚሆን ዐይነት ማርያም ኢየሱስን ለመቀባት ተዘጋጀች። በመጨረሻም የአስቆሮቱ ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ስለ መስጠት ጉዳይ ከፍርድ ሸንጎ ጋር በመመሳጠር ተዘጋጀ።

(ማቴ26:)1ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች ተናሮ ከጨረሰ በኋላ፣ ደቀ መዛሙርቱን፣ 2«ከሁለት ቀን በኋላ ፋሲካ እንደሚሆን ታውቃላችሁ፤ የሰው ልጅም ሊሰቀል አልፎ ይሰጣል» አላቸው።

3ከዚህ በኃላ የካህናት አለቆችና የሕዝብ ሽማግሌዎች ቀያፋ በተባለ ሊቀ ካህን ግቢ ውስጥ ተሰብስበው፣ 4በረቀቀ መንገድ ኢየሱስን ለማስያዝና ለማስገደል ተማከሩ። 5ነገር ግን፣ «በሕዝቡ መካከል ረብሻ እንዳይነሣ በበዓል ቀን አይሁን» በማለት ተስማሙ።

«ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች ተናሮ ከጨረሰ በኋላ» በሚሉት ቃላት እን ደተመለከተው፣ አምስተኛውንና የመጨረሻውን የማቴዎስ ወንጌል ሐተታ ጨረስን (ከማቴ 8÷1፤ 11÷1፤ 13÷53፤ 19÷1 ጋር ያነ)። እነዚህ ሁኔታዎችየኢሱስ ደቀ መዛሙርት ቀኑን ሙሉ በቤተ

መቅደሱ ውስጥ ከዋሉ በኋላ፣ ምናልባት ማክሰኞ ምሽት ላይ ከተማውን ለቀው በሄዱ ጊዜ ተፈጽመው ይሆናል:: ምናልባት ረቡዕ ዕለት ሳይፈጸሙ አልቀረም:: ይህ ደግሞ በአይሁድ ዘንድ ከፋሲካ በፊት ሁለት ቀን ተደርጎ (ታካይ ሆኖ) ሳይታሰብ አልቀረም፤ የላቀው ዋና ጉዳይ ግን በዚህ በአራተኛው ትንቢት ላይ ኢየሱስ የሚከሰስበትን ትክክለኛ ጊዜ ለይቶ የማመልከቱ ሐቅ ነው::

ኢየሱስ በቢታንያ ሳለ (ከሉቃ 21÷37-38 ጋር ያነ)፣ የፍርድ ሸንጎው በቀላሉ በማይቋጨው ችግር ውስጥ ተጠምዶ ነበር:: ከሁለት ወር ገደማ በፊት ቀያፉ በሰጠው መመሪያ[21] መሠረት ኢየሱስን ለመግደል ቍርጥ ሐሳብ አደረጉ (ከ11÷49-53 ጋር ያነ):: አሁን ደግሞ በቀያፋ ቤት ሆነው ሐሳባቸውን መልሰው በማጤን ጥረታቸውን ዕጥፍ ድርብ አደረጉት:: የመጀመሪያው የግድያ ሙከራቸው ከሁለት ዓመትና ከሁለት ፋሲካ በፊት ነበር (ዮሐ 5÷18):: ይሁን እንጂ ከዚያ ጊዜ ወዲህ የሕዝቡን አዝማሚያ መገምገም እንዳለባቸው አስተውለዋል፤ ምክንያቱም ተራው ሕዝብ ኢየሱስን ይወደዋል (ማቴ 21÷46፤ ማር 12÷12):: ከሆሣዕና በዓል ወዲህ (እሑድ) ከቤተ መቅደሱ ማጽዳት በኋላ (ሰኞ)፣ ከውይይቱም ዕለት በኋላ (ማክሰኞ) ቍጥራቸው እየጨመረ የመጣው ደጋፊዎች ባሉበት ኢየሱስን ላለመያዝ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው:: እርግጥ ሕዝቡ ረብሻ የሚያነሣ ከሆነ፣ ሮማውያን ገዥዎች ረብሻውን ለማስቆም ፈጣን እርምጃ ይወስዳሉ፤ ያሁኖችን ገዥዎችም በሌላ ይተካሉ:: ለሀገራቸውና ለሹመታቸው

[21] እ.ኤ.አ. 1990 ዓ.ም. ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብ የሀብታም «ቀያፋውያን» ቤተ ሰብ የዋሻ መቃብር በቍፋሮ ተገኘ:: የዋሻው መቃብር ማሰሮዎችን ይዞ ነበር (ይህም በ30 ዓ.ቅ.ክ. እና በ70 ዓ.ም. መካከል በብዛት የተለመደ ነበር):: ይህም በጽሑፋችን ላይ ስለ እርሱ ያነበብነው ቀያፋ ሊሆን ይችላል:: ከZ. Greenhut, "Burial Cave of the Caiaphas Family," *BAR* (Sept/Oct, 1992): 29-36 ጋር ያነጻጽሩ::



ይሠጋሉ:: «ስለ ሕዝቡ አንድ ሰው ቢሞት የሚሻል» በመሆኑ ቍርጥ ሐሳብ ላይ ጸንተዋል (ዮሐ 11÷50)::

ቍጥር 2 ውስጥ ኢየሱስ በፋሲካ በዓል ጊዜ አልፎ እንደሚሰጥ ተናገረ:: በቍጥር 5 ውስጥ እንደ ተገለጠው ግን የፍርድ ሸንጎው ሕዝቡን ስለ ፈራ አንዳች ግጭት እንዳይኖር ፈለገ:: ልብ ያላሉት መልካም አጋጣሚ የአስቆሮቱ ይሁዳ ነበር:: ወደ እነርሱ መጥቶ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ሲደራደር አንዳንድ (የተጠበቀ) አደጋ ሊርስ ቢችልም፣ ያ ዕድል እንዲያመልጣቸው አልፈለጉም:: ቀጥሎ ያሉት ሁኔታዎች የተከናወኑት በሰዎች ዕቅድ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ሉዐላዊ ፈቃድ መሆኑንም እንድናስተውል ተደርገናል:: እነዚህ ሁኔታዎች ቀደም ሲል በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ስለ ሆኑ ሊከለከሉ አይችሉም::

**§ 141**
**ለኢየሱስ ሕማማት ዝግጅት:- ማርያም (ማቴ 26÷6-13፤ ማር 14÷3-9፤ ዮሐ 12÷2-8)**

ይህ ሁኔታ የተከናወነው ከአምስት ቀን ቀደም ብሎ ነው:: ከጊዜና ከሁኔታ ቅደም ተከተል አንጻር ኢየሱስ ቢታንያ ከደረሰበትና ከሆሣዕናው የድል ጉዞ ወቅት ጋር ይገጣጠማል (ክፍል 128ሀ ይመ):: ማቴዎስና ማርቆስ የሐዋርያቱን አለማስተዋል ለማሳየት ሲሉ ይህን ሐሳብ ከርእሰ ጉዳይ አንጻር ከዚህ ላይ አስገብተውታል:: ዮሐንስ፣ *ሥሥቱን* ጉልሕ አድርጎ በማሳየት በቅይጡ ውስጥ ያስቆሮቱ ይሁዳን አክሏል::[22] ስለዚህ ይሁዳ ጌታን አሳልፎ ከሰጠበት ግልጽ ከሆኑት አነሣሽ ምክንያቶች ውስጥ

[22] አንዳንዶች ኢየሱስ የመሲሕነቱን ማኗ ይወጣ ዘንድ ይሁዳ ለማስገደድ ፈልጎ ነበር የሚል ሐሳብ አቅርበዋል:: ሆኖም፣ ይህ ለይሁዳ ምን ጥቅም ያስገኝለታል? ይህ ቢሳካ እንኳ ኢየሱስ ከሐዲ የሆነውን ሰው በገንዘብ ያገርነት ኀላፊነቱ እንዲቀጥል ያደርገዋልን? (W.B. Smith, "Judas Iscariot," *HibJ* 9 [1911]: 529-544 ጋር ያነ)::

አንዱ ለገንዘብ የነበረው ጉጉት ነው:: ሁኔታው ዐሥራ አንዱ ሐዋርያት የይሁዳን እውነተኛ ጠባይ ያልተገነዘቡ መሆናቸውንም ያሳያል:: የገንዘብ ከረጢት ያዥ በመሆኑ፣ ማርያም የፍቅር መግለጫ የሆነውን ድርጊት ባከናወነች ጊዜ፣ ይሁዳ ሲያወግዛት እነርሱም ተባበሩት::

**§ 142**
**ለኢየሱስ ሕማማት ዝግጅት:- ይሁዳ**
**(ማቴ 26÷14-16፤ ማር 14÷10-11 ሉቃ 22÷3-6)**

[(ሉቃ22)3]ሰይጣንም ከዐሥራ ሁለቱ ጋር በተቈጠረው የአስቆሮቱ ይሁዳ በተባለው ገባበት፤ [4]ይሁዳም ወደ ካህናት አለቆችና ወደ ቤተ መቅደሱ ሹሞች ሄዶ ኢየሱስን እንዴት አሳልፎ እንደሚሰጣቸው ተነጋገረ::

[(ማቴ26)15]«እርሱን አሳልፌ ብሰጣችሁ እናንተስ ምን ትሰጡኛላችሁ» አላቸው:: (እነርሱም ይህን ሲሰሙ ደስ አላቸው[ማር]) እነርሱም ሠላሳ ጥሬ ብር ቈጥረው (ቃል ገቡለት[ማር]) ሰጡት::

[(ሉቃ22)6]እርሱም በነገሩ ተስማማ፤ አሳልፎ ሊሰጣቸውም ሕዝብ የማይገኝበትን ምቹ ጊዜ ይጠብቅ ጀመር::

ሰይጣን ወደ ይሁዳ መግባቱን ሉቃስ ይነግረናል (ሉቃ 22÷3)፤ ይህ ረቡዕ ዕለት ሳይሆን አይቀርም:: ከዚያም እንደ ገና ኀሙስ ምሽት ላይ ኢየሱስ የሰጠውን ቊራሽ ከበላ በኋላ፣ በይሁዳ ላይ ሰይጣን ገባበት ይላል ዮሐንስ (ዮሐ 13÷27):: ይህም ጴጥሮስ፣ ሐናንያን፣ «መንፈስ ቅዱስን ትዋሽና ... ሰይጣን ልብህን ለምን ሞላው?» ካለበት ከሐዋርያት ሥራ 5÷3 ጋር ተመሳሳይ ነው:: ሰይጣን በሰዎች ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድር አናውቅ ይሆናል:: እናስተውል ዘንድ ግን ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል:: ሦስቱ ተመሳሳይ ወንጌላት ይሁዳ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ እንደ ነበር ይገልጻሉ፤ ይህም «እርሱ እንዲህ መሥመር ከመሳት ከደረሰ፣ እናንተም ጥንቃቄ ማድረግ አለባችሁ!» የማለት ያህል ነው:: የሰይጣንን ተጽዕኖ ለመከላከል ንቁዎች መሆን አለብን::



ከሽኩቻውና ከፈተናው በማምለጥ ከእኛ ልናርቀው እንችላለን (ያዕ 4÷7)::

ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ እንዲሰጥ ያነሣሣውን ምክንያት በተመለከተ አያሌ ሐሳቦች ተሰንዝረው ነበር:: ምናልባት በኢየሱስ ቀንቶ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ማርያም ባከናወነችው ድርጊት ተበሳጭቶ ሊሆን ይችላል:: ወይም ይሁዳ ትዕግሥቱ በማለቁ ኢየሱስ ከፍርድ ሸንጎው ጋር ተጋጭቶ መንግሥቱን ያቋቁም ዘንድ ለማስገደድ ፈልጎ ሊሆን ይችላል:: ኢየሱስ የፖለቲካ መሲሕ ይሆናል ብሎ የተሣሣተ ሀሳብ ውስጥ በመግባት ግራ ተጋብቶ ሊሆን ይችላል:: ከተቀማጩ ገንዘብ ቈንጥሮ (ሰርቆ) የወሰደውን ገንዘብ በፍጥነት ለመመለስ ፈልጎም ሊሆን ይችላል:: በኢየሱስና በሃይማኖት አለቆች መካከል የነበረው ግጭት ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን ሲያይ ከዚህ ሁኔታ ራሱን ለማዳን ጥረት ማድረጉም ሊሆን ይችላል:: የኢየሱስንም ሆነ የይሁዳን አነሣሽ ምክንያቶች መቼውም ልናውቅ አንችልም፤ ማወቅ የምንችለው ውጤቱን ብቻ ነው:: ይሁዳ ይንቀሳቀስ የነበረው አስቀድሞ በተወሰነ ኀይል እጅ ምሪት መሆኑን ግን እናውቃለን (መዝ 41÷9፤ ዘካ 11÷7-14):: ይህ ማለት ግን በፈጸመው ድርጊት ላይ የራሱ ቊጥጥር አልነበረም ማለት አይደለም:: ለማለት የተፈለገው እርሱም እንደ ኢየሱስ ከዘመናት በፊት እግዚአብሔር የፈቀደውን ፈጸመ ነው::

የአንድ ተራ ባሪያ ዋጋ የሆነው ሠላሳ ብር (ዘፀ 21÷32) እንደሚሰጠው ተስፋ ተሰጥቶት ነበር:: ይህን የሚያገኝ ከሆነም በአፀፋው በአመች ጊዜ ማለትም ሕዝብ በማይገኝበት ወቅት ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ቃል ገባ::

**§ 143**
**የፋሲካን ምግብ ለመብላት መዘጋጀት**
**(ማቴ 26÷17-19፤ ሉቃ 22÷7-13)**

ተመሳሳዩ ወንጌላት ኢየሱስ የፋሲካን እራት የበላው የኒሳን ወር በገባ በ15ኛው ቀን፣ ከመሰቀሉ በፊት በኒሳን 14 መሆኑን ያሳያሉ

(ኒሳን ከእኛ የሚያዝያ ወር ጋር ከሞላ ጐደል ተመጣጣኝ ነው):: ይሁን እንጂ አንዳንዶች ዮሐንስ 18፥28ንና 19፥14ን ሲተረጉሙ ኢየሱስ የሞተው የፋሲካ በጎች በሚታረዱበት ዕለት ኒሳን 14 ነው ይላሉ:: ይህ እውነት ከሆነ፣ በዮሐንስና በተመሳሳይ ወንጌላቱ መካከል መጣረስ አለ ማለት ነው::

ለዚህ አንዱ መፍትሔ የዮሐንስ ወንጌል ወይም ተመሳሳዮቹ ወንጌላት ከሁለት አንዳቸው ተሳስተዋል፤ ወይም በአንድ ነገር ላይ ነገረ መለኮታዊ ሐሳብ ለመመሥረት ሲባል ጽሑፉ ሆን ተብሎ ተለውጧል ብሎ ሐሳብ መሰንዘር ነው:: ይህ የቅዱስ መጽሐፍን እውነት ዝቅ ማድረግ ብቻ ሳይሆን በቂ ማስረጃም የለውም:: ሁለተኛው መፍትሄ ሁለት የተለያዩ የዘመን አቈጣጠርን መሠረት በማድረግ ለፋሲካ በዓል ሁለት እውናዊ ቀኖች አሉ የሚለው ነው:: ለምሳሌ ኢየሱስ የፀሐይን ዑደት መሠረት ያደረገውን የኤሰኔን - Essene የዘመን አቈጣጠር[23] ይከተል እንደ ነበር በማለት ጃበርት የተባለ ጸሐፊ ሐሳብ ያቀርባል፤ ወይም በኢየሩሳሌም የነበሩት አገር ጎብኝዎች በርካታ ስለ ነበሩ[24] የፋሲካ መሥዋዕትና ምግብ የማቅረቡ ሂደት ሁለት ቀን ሙሉ ፈጅቶ ይሆናል:: በዚህ መሠረት የፋሲካ በዓል ለደቀ መዛሙርቱ ሐሙስ ቀን ሲሆን፣ ለሰዱቃውያን ደግሞ ዓርብ ዕለት ነበር ማለት ነው::[25] ሆህነር የተባለው ጸሐፊ በገሊላውያንና በአይሁድ የቀን አቈጣጠር መካከል

[23] Annie Jaubert, *The Date of the Last Supper* (New Yourk: Alba House, 1965):: አመለካከቱ ካስከተለው ዐቢይ ችግሮች አንዱ የኤሰን የኮከብ ዘመን አቈጣጠር የተገኘው ከሦስተኛው ምእት ዓመት ሰነድ መሆኑ ነው::

[24] ከ Maurice Casey, "The Date of the Passover Sacrifices and Mark 14:12," *TB* 48/2 (1997): 245-247 ጋር ያነጻጽሩ::

[25] N. Walker በወንጌላቱ ላይ የሰፈሩት ዐሥራ ስድስት የሕማማት ሁናቴዎች ከሃያ አራት ሰዓት ወቅት ይልቅ ሦስት ቀንን መያዝ (መሸፈን) አለባቸው በማለት ሐሳብ ያቀርባል:: ስለዚህ በ"Pauses in the Passion Story and Their Significance for Chronology," *NovT* 6 (1963): 16-19 and "Yet Another Look at the Passion Chronology" *NovT* 6 (1963): 286-289 ላይ የመጨረሻው እራት የቀረበው ማክሰኞ ዕለት ነው የሚለውን ሐሳብ ይደግፋል::



ልዩነት እንደ ነበር ሐሳብ ያቀርባል (ፀሐይ ስትወጣ ወይም ፀሐይ ስትጠልቅ)[26]:: ስለዚህ ኢየሱስና ሌሎቹ ገሊላውያን ከአይሁድ በፊት አንድ ቀን ቀደም ብለው የፋሲካን ምግብ በልተዋል:: ሌሎች ደግሞ ልዩነቱ የተፈጠረው በፈሪሳውያንና በሰዱቃውያን ክርክር የተነሣ ነው በማለት ይከራከራሉ:: ይሁን እንጂ የቀን አቈጣጠርን መሠረት በማድረግ የቀረቡት ሐሳቦች ሁሉ አንዳቸውም የሰነድ ድጋፍ የላቸውም::

በጣም ግልጽ የሆነ ሦስተኛ መፍትሔ አለ፤ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ እውነተኛውን ፋሲካ አክብረዋል:: ዮሐንስ ይህን ያውቃል፤ የተመሳሳዮቹን ወንጌላት የጊዜና የሁኔታ ቅደም ተከተልም ያውቃል:: እንደውም የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ኢየሱስ ያከበረውን ፋሲካ ይገልጻል:: (1) ከቢታንያ ይልቅ ሙሉውን ሳምንት በቆዩበት በኢየሩሳሌም ነበር፤ (2) በምሽት ላይ የምግብ ገበታውን ተደግፈው እንደ ነበር ሥዕላዊ በሆነ መልክ ተገልጽዋል:: የበዓል ምግብ መሆኑን ነው ይህ የሚያመለክተው ፤ ደግሞም (3) የአስቆሮቱ ይሁዳ በፍጥነት መውጣቱን ደቀ መዛርቱ ሲያዩ ለፋሲካ ምግብ የቀረውን ነገር ለማሟላት ወይም ለድኾች ምጽዋት ለመስጠት የወጣ መሰላቸው:: እነዚህም የፋሲካ ምግብ ምልክቶች ናቸው:: ከዚህም የተነሣ ዮሐንስ ፋሲካ የሚለው (18፥28) *ቻጊጋይ - chagigah* ሲሆን (ዘኍ 28፥18-19)፣ የቂጣ በዓልን መግቢያ ነው:: ምን ይባል እንደ ነበር ዮሐንስ ተምታቶበት ይሆን≅ አልተምታታበትም:: በዮሐንስ ዘመን በፋሲካና (ኒሳን Nisan 14) በቂጣ በዓል (ኒሳን Nisan 15-20) መካከል የነበረው ልዩነት እምብዛም ነው:: ሁለቱም አገላለጾች በመፈራረቅ አገልግሎት ላይ ይውሉ ነበር (ማቴ 26፥17፤ ማር 14፥1:12፤ ሉቃ 2፥41፤ 22፥1፤

[26] H.W. Hoehner, *Chronlogical Aspects of the Life of Christ* (Grand Rapids: Zondervan, 1977).

Josephus, *Ant* 2.317; *Wars* **5:98**):: እንግዲህ ይህን ልዩ ምግብ ዮሐንስ ፋሲካ ብሎ መጥራቱ ፍጹም ተገቢ ነበር:: በተጨማሪም በሌላ ጊዜ ሁሉ ዮሐንስ «ፋሲካ» የሚለውን ቃል ሲጠቀም አንዱን ምግብ ብቻ ሳይሆን ጠቅላላውን የፋሲካ በዓል ማመልከቱ ነበር (ዮሐ 2፥13:23፤ 6፥4፤ 11፥55፤ 12፥1፤ 13፥1):: ስለዚህ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ኒሳን 14 የሚከበረውን አማናዊውን ፋሲካ በሉ:: በተጨማሪም ዮሐንስ ወንጌል 18፥12 ውስጥ የተመለከቱት አይሁድ አማናዊውን የፋሲካ ምግብ[27] ሳይሆን ቀሪውን ሰባት ቀን ሙሉ የሚከበረውን የቂጣ በዓል ከማክበር እንዳይከለከሉ ወደ ጲላጦስ ግቢ አንገባም አሉ::

**ማር 14፥12-16**
**ከሉቃ 22፥8፤**
**ከማቴ 26፥18 ጋር**

12የፋሲካ በግ በሚታረድበት በቂጣ በዓል
የመጀመሪያው ቀን፣ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ
ቀርበው፣ «የፋሲካ እራት የት እንድናዘጋጅልህ
ትፈልጋለህ?» አሉት::

13እርሱም ከደቀ መዛሙርት ሁለቱን (ጴጥሮስንና ዮሐንስን[ሉቃ]) እንዲህ ሲል
ላካቸው፤ «ወደ ከተማ ሂዱ፤ እንስራ ውሃ የተሸከመ ሰው ይገናኛችኋል፤
14ወደሚገባበት ቤትም ተከተሉት፤ የቤቱንም ጌታ፣ «*መምህሩ፣ (ጊዜዬ
ተቃርቦአልና[ማቴ]) ከደቀ መዛሙርቴ ጋር የፋሲካን እራት የምበላበት የእንግዳ ማረፊያ
የትኛው ነው?*» ብሎአል በሉት፤ እርሱም በሰገነቱ ላይ የተሰናዳና የተነጠፈ ሰፊ
አዳራሽ ያሳያችኋል፤ እዚያ አዘጋጁልን::

16ደቀ መዛሙርቱም ወጥተው ወደ ከተማዪቱ ሄዱ፤ ማንኛውም ነገር
ኢየሱስ እንዳላቸው ሆኖ አገኙት፤ ፋሲካውንም አሰናዱ::

በዚህ ጊዜ የኒሳን ወር 14ኛው ቀን ኀሙስ ዕለት ነበር:: የፋሲካ በዓል ዘፀአት በሚታወስበት ሰባት ቀን ሙሉ የሚከበር ሲሆን (ዘፀ ***12፥13-27፤ 23፥15፤ 34፥18፤*** ዘዳ ***16፥1-8 49፥1-2:10-12***; Philo VI, 2.41, 224 & 2.42.228) የቂጣ በዓል ተብሎም ይጠራል (Josephus, *Ant* 2.317):: በመላው ግዛት ውስጥ የሚገኙ ታማኝ አይሁዳውያን አምላኪዎች ሁሉ በኢየሩሳሌም ይሰበሰባሉ:: አንዳንዶች **100,000** የበግ መሥዋዕቶችን የሚፈጁ አንድ ሚሊየሆን የሚሆኑ አይሁድ ከተማዋን ያጨናንቁ እንደ ነበር ይገምታሉ (Butler, p. 524):: ዕርዱና የትኩስ ደም ጅረት አካባቢውን ያውድ ነበር::

እያንዳንዱ ቤት በተጠበሰ በግ ከመራራ ቅጠል ጋር በቀይ ሥር፣ በቀያቴ፣ በጦስኝ፣ በቅመም፣ በዝቃቅቤ [Butler, p. 5241] በወይንና የበጉ ሥጋ በሚጠቀስበት ወጥ በዓሉን አከበረ [ሃሮሴት - *haroset*]:: ሙሉውን ሥጋ ለመጨረስ በቂ ሰዎችን ይሰበስባሉ:: ምግብ እየተበላ ሳለ በ«ሀሌል» መዝሙር የተለዩ **(113-118)** አራት የሥርዐት የወይን ጽዋዎች ለሰዎች ይሰጡ ነበር:: ከሁለተኛው የወይን ጽዋ በኋላ ከቤተ ሰቡ ውስጥ በዕድሜ ትንሽ የሆነ ሰው የፋሲካ በዓል ለምን እንደሚከበር ይጠይቅ ዘንድ መመሪያ ይሰጠው ነበር:: ከዚያም የቤተ ሰቡ አባወራ እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ባርነት እንዴት እንዳወጣቸው የሚያወሳውን ታሪክ ያብራራል::

ደቀ መዛሙርቱ ወደ ቅድስት ከተማ የመጡት ለዚህ ዐላማ መሆኑን ያውቃሉ:: የፓለስቲና ኗሪዎች ፋሲካን እንዲበሉ

[27] ከ Carson, pp. 528-532; and B. Smith, "The Chronology of the Last Supper," *WTJ* 53 (1991): 29-45 ጋር ያነጻጸሩ:: F. Chenderlin, "Distributed Observance of the Passover: A Preliminary Test of the Hypothesis," *Biblica* 57 (1976): 1-24 በሚለው ላይ ጥንድ የሆኑ በሳል ሐሳቦችን ያቀርባል:: በመጀመሪያ ሁሉም በጎች በአንድ ቀን እንዲታረዱና በአንድ ቀን እንዲበሉ ሲደረግ ከልክ በላይ የሆኑ የፋሲካ ምግብ ተካፋዮች ሳይኖሩ አልቀረም:: ስለዚህ የፋሲካ በዓል በተከታታይ ቀናት ይከበር ዘንድ፣ «በተለያየ ምድብ የቀረበ የፋሲካ በዓል አከባበር» መኖር አለበት በማለት ሐሳቡን ያቀርባል:: ሁለተኛው ጉዳይ ይህ ከሆነ ደግሞ የአይሁድ አለቆች የፋሲካን ምግብ ለመብላት የመረጡት በዚያኑ በኒሳን 14 ቀን ሳይሆን፣ በፋሲካ ሳምንት በቅዱሱና በከፍተኛው ሰንበት ዕለት ሊሆን ይችላል::

የተፈቀደላቸው ኢየሩሳሌም ውስጥ ብቻ ነበርና (Carson, p. 534):: ስለዚህ በዓሉን ለማክበር የት ማዘጋጀት እንዳለባቸው ኢየሱስን ጠየቁት:: የውሃ መቅጃ እንስራ የያዘን ሰው ይፈልጉ ዘንድ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ላካቸው:: ይህ ሰው እንደ ታመመ አውራ ጣት ብቅ ይላል:: እንደሚታወቀው የውሃ እንስራ መሸከም «የሴት ሥራ ነው::» ቤቱ ድረስ ተከተለው በመሄድ ኢየሱስ የላይኛውን ክፍል ሊጠቀምበት እንደሚፈልግ ለቤቱ ባለቤት ይነግሩታል:: ይህ ቤት ኢየሱስ በመጀመሪያ ለዐሥራ አንዱ የተገለጠበት (ሉቃ 24÷33-36፤ ዮሐ 20÷19) የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ለጸሎት የተሰበሰበችበት (ሐሥ 1÷13-14፤ 12÷12) መንፈስ ቅዱስም በደቀ መዛሙርቱ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የወረደባቸው (ሐሥ 2÷1-4) የዮሐንስ ማለትም የማርቆስ እናት የማርያም ቤት ሊሆን ይችላል::

ደቀ መዛሙርቱ በደረሱ ጊዜ ክፍሉ ተዘጋጅቶ ስለ ነበር ቀደም ሲል የተደረሰበት ስምምነት ነበር ማለት ነው:: ወይም የቤቱ ባለቤት ለአምልኮ ወደ ኢየሩሳሌም የመጡት ምእመናን የላይኛውን ክፍል ይፈልጉት ይሆናል ብሎ አዘጋጅቶት ይሆናል፤ ይህ በዚያ ዘመን የተለመደ ነበር:: ኢየሱስ በዚያ አካባቢ ብዙዎቹን የሳምንት ቀናት ስላሳለፈ ይህን ጉዳይ ለማመቻቸት በቂ ዕድል ነበረው:: ይህ ሁሉ ደቀ መዛሙርቱን በምስጢርም ባይሆን በግላቸው ከሕዝብ ርቀው እንዲገናኙ - አበቃቸው:: በተጨማሪም ይሁዳ የት እንደ ተሰበሰቡ ለፍርድ ሸንጎው እንዳይነግር ገደበው::

**§ 144**
**በፋሲካ ምግብ ላይ የተቀሰቀሰ ግጭት**
**(ማቴ 26÷20፤ ማር 14÷17፤ ሉቃ 22÷14-16:24-30)**

(ሉቃ22) 14 ሰዓቱም በደረሰ ጊዜ ኢየሱስ ከሐዋርያቱ ጋር በማእድ ተቀመጠ፤ 15 እንዲህም አላቸው፤ «መከራ ከመቀበሌ በፊት ይህን ፋሲካ አብሬአችሁ ለመብላት በጣም እመኝ ነበር፤ 16 እላችኋለሁ፤ በእግዚአብሔር



መንግሥት የዚህ ትርጉም እስኪፈጸም ድረስ ይህን ፋሲካ ዳግመኛ አልበላም::»

ኀሙስ ዕለት ፀሐይ ከጠለቀች በኋላ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ኢየሩሳሌም ውስጥ ለብቻቸው ምናልባትም በምስጢር በሆነና የት መሆኑ ባልተገለጸ የላይኛው ክፍል ተሰበሰቡ:: ለዚህ በዓል ሲሉ በኢየሩሳሌም እንደ ተሰበሰቡት ሌሎች ቤተ ሰዎች ሁሉ እነዚህ አናሳ ወገኖችም የተቀደሰው በዓል መንፈሳዊ ቤተ ሰብ በመሆን ተሰብስበዋል (ማቴ 12÷50):: ከምድር ትንሽ ከፍ ብሎ በተዘረጋ ሰታቴ ዐይነት ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠዋል:: በጠረጴዛው ዙሪያ በግራ ጐናቸው ትራስ ላይ ተደግፈዋል:: ለኢየሱስ ይህ በዓል ከድግስ በላይ ነው:: የፋሲካ በዓልን ከማክበር እንኳን በላይ ነው:: ኢየሱስ የዘፀአት አማናዊ አካል መሆኑን ያውቃል፡- ለሕዝቡ ትድግና መሥዋዕት የሆነ የፋሲካ በግ ነው:: ይህ ምግብ አይቀሬ የወደፊት ዕጣ ፈንታውን ይዘክራል (ዮሐ 1÷29):: በትሥጉትነቱ ፋሲካን ሲያከብር ይህ የመጨረሻው ነው:: ሌላ ድግስ ይኖራል ... የሰርግ ድግስ:: ያ የሚሆነው ግን ሌላ ጊዜ ነው:: አሁን ግን፣ «ይህን ፋሲካ አብሬአችሁ ለመብላት በጣም እመኝ ነበር» በሚለው የዕብራይስጥ ፈሊጣዊ አነጋገር አብሯቸው ለመብላት የነበረውን ብርቱ ምኞት ገለጸ::



**ሉቃ 22÷24-30**

24 ደግሞም ከመካከላቸው ማን እንደሚበልጥ በእነርሱ ዘንድ ክርክር ተነሣ:: 25 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ «የአሕዛብ ነገሥታት ሕዝቦቻቸውን በጉልበት ይገዛሉ፤ በእነርሱ ላይ ሥልጣን ያላቸውም በጎ አድራጊዎች ተብለው ይጠራሉ:: 26 በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ አይሁን፤



**ደቢቁን ከእናንተ ታላቅ የሆነ እንደ ታናሽ፣ ገዥ የሆነም እንደ አገልጋይ ይሁን።**
**[27]ስለሆነ፣ በማእድ ከተቀመጠና ቆሞ ከሚያስተናግድ ማን ይበልጣል≅ በማእድ**
**የተቀመጠው አይደለምን? እኔ ግን በመካከላችሁ ያለሁት እንደ አንድ አገልጋይ ነው።**
**[28]እናንተም ሳትለዩኝ በመከራዬ ጊዜ በአጠገቤ የቆማችሁ ናችሁ፤ [29]አባቴ እኔን እንድ**
**ሾመኝ እኔም ደግሞ በመንግሥቴ እሾማችኋለሁ፤ [30]ይኸውም በመንግሥቴ ከማእዴ**
**እንድትበሉና እንድትጠጡ ደግሞም በዙፋን ላይ ተቀምጣችሁ በዐሥራ ሁለቱ**
**የእስራኤል ነገድ ላይ እንድትፈርዱ ነው።»**

[ቊ 25-27 = *ማቴ* 20÷25-28 እና *ማር* 10÷42-45፣ የክፍል 125ለ *ማብራሪያን ይመልከቱ*]

ወደ ላይኛው ክፍል እንደ ገቡ ዐሥራ ሁለቱ ከዚህ ቀደም ሁለት ጊዜ ተነሥቶ የነበረውን የክርክር ሐሳብ አሁንም ተያያዙት፡- ከእነርሱ መካከል ማን ነው የሚበልጠው? በዚህ ጉዳይ ላይ በመጀመሪያ የተከራከሩት ከዓመት በፊት ነበር (ማቴ 18÷15፤ ማር 9÷33-37፤ ሉቃ 9÷46-48፤ ክፍል 90)። የመጨረሻው ካለፈው ሳምንት ብዙ የራቀ አይደለም (ማቴ 20÷17-28፤ ማር 10÷32-45፤ ክፍል 125ለ)· 'ስቱንም ጊዜ ይህ ክርክር የተነሣው ኢየሱስ ስለ ሕማማቱ ሲናገር ወዲያውኑ ነው። ሦስቱንም ጊዜ ኢየሱስ በብርቱ ገሥጿቸዋል። ይህን ክርክር እንደገና በሰማ ጊዜ በመጠኑም ቢሆን ኀፍረት ሳይሰማቸው አልቀረም።

ዐሥራ ሁለቱ ኢየሱስን ለመከተል የሦስት ዓመት ሕይወታቸውን ለእርሱ ተጥተዋል። ይህን ለማድረግም ብዙ መሥዋዕት ከፍለዋል። እንዲህ ያለው መሥዋዕት ዋጋቢስ ሆኖ እንደማይቀር ኢየሱስ አረጋግጦላቸዋል። ሽልማት በትልቁ ይሰጣቸዋል፤ ይኸውም በመንግሥቱ ውስጥ መሪነት፣ በሚስሐዊ ግብዣ ላይ ልዩ ስፍራ፣ እንዲሁም ለእያንዳንዳቸው የፍርድ ዙፋን ነው። ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ ገና ሩቅ ነው። አሁን የተጠሩት



ሕይወታቸውን መሥዋዕት እንዲያደርጉና በአገልገሎታቸውም እንዲቀጥሉ ነው።

ይህ ፅንሰ ሐሳብ ከኢየሱስ የታወቁ ዋና ሐሳቦች ውስጥ አንዱ ነው። ዓለም ከሚያስተምረው ትምህርት ሁሉ ይጣረሳል፡- «ከፍተኛውን ስፍራ እሻ፤» «የራስህን ሥራ አከናውን፤» «እኔ አንደኛ ልሁን» ወዘተ። ክርስቲያኖች የሚንቀሳቀሱት ግን ከዚህ ልዩ በሆኑ ደንቦች ነው።

**§ 145**
**ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ**
**(ዮሐ 13÷1-20)**

ወደ ላይኛው ክፍል እንደ ገቡ ደቀ መዛሙርቱ ስለ ወደ ፊት ሹመታቸው ውጥረት ውስጥ ገቡ። ክርክሩ የተነሣው ኢየሱስ አጠገብ የሚቀመጠው ማን ነው በሚለው ጥያቄ ሳይሆን አይቀርም። ወደ ላይኛው የግብዣ ስፍራ ለመቀመጥ ከመጋፋት ይልቅ፣ ታችኛው ስፍራ ላይ መቀመጥ የሚሻል መሆኑን ኢየሱስ ከስድስት ወር በፊት ለፈሪሳውያን የሰጣቸውን ምክር (ሉቃ 14÷7-11) ያለጥርጥር ችላ ብለዋል።

ማን እንደሚበልጥ በደቀ መዛሙርቱ መካከል ለተነሣው ክርክር ኢየሱስ በቃል መልስ ሰጥቶአል (ሉቃ 22÷24-30)። አሁን ደግሞ የሚታይ መልስ ሰጠ። የመጣው በክብር ቦታ ላይ እንደሚቀመጥ ሆኖ ሳይሆን አገልጋይ ሆኖ መሆኑን ገለጸ (ሉቃ 22÷27)። የተገረሙት ደቀ መዛሙርት ይህ የቱን ያህል እውነት መሆኑን ሊማሩ ነው። ይህ የእግር አጠባ ወደ መስቀሉ መግቢያ ነው፤ ሁለቱም መንጻትን እውን ያደርጋሉ።